HUMAN RIGHTS WATCH

# “ረሃብ ቢመጣ ምን ይኮናል?”

## በኢትዮጵያ የታችኛው ኦሞ ሸለቆ ተወላጅ ሕዝቦች ላይ የተፈጸሙ በደሎች

Copyright © 2012 Human Rights Watch
All rights reserved.
Printed in the United States of America
ISBN: 1-56432-915-1
Cover design by Rafael Jimenez

ሂዩማን ራይትስ ዎች በዓለም ዙሪያ የሚገኙ ሰዎችን ሰብአዊ መብቶች ለማስጠበቅ የቆመ ነው። አድልዎን ለመከላከልና ፖለቲካዊ ነጻነትን ለማስፈን፣ ሰዎችን በጦርነት ወቅት ከሚፈጸሙ ኢሰብአዊ ድርጊቶች ለመጠበቅ እንዲሁም አጥፊዎቸ ሕግ ፊት እንዲቀርቡ ለማድረግ ከሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ሰለባዎች እና ከመብት ተሟጋቾች ጎን እንቆማለን።የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን በመመርመር የምናጋልጥ ሲሆን የጥሰቶች ፈጻሚዎችም ተጠያቂ እንዲሆኑ እናደርጋለን። መንግስታት እና ሌሎች በስልጣን ላይ የሚገኙ ሃይሎች ሰብአዊ መብቶችን የሚጥሱ አሰራሮችን በማቆም ዓለማቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሕግጋትን እንዲያከብሩ እንሞግታቸዋለን። ሕዝብና ዓለማቀፉ ሕብረተሰብ ሰብአዊ መብቶች ለሁሉም ለሚለው ዓላማ ድጋፍ ለማድረግ እንዲሳተፉ እናደርጋለን።

ሂዩማን ራይትስ ዎች ከአርባ በላይ በሚሆኑ ሀገራት ሠራተኞች ያሉት ዓለማቀፍ ድርጅት ሲሆን በአምስተርዳም፣ በቤይሩት፣ በበርሊን፣ በብራሰልስ፣ በቺካጎ፣ በጄኔቫ፣ በጎማ፣ በጆሃንስበርግ፣በለንደን፣በሎስ አንጀለስ፣ በሞስኮ፣ በናይሮቢ፣ በኒው ዮርክ፣ በፓሪስ፣ በሳን ፍራንሲስኮ፣ በቶክዮ፣ በቶሮንቶ፣ በቱኒስ፣ በዋሽንግተን ዲሲ እና በዙሪክ ቢሮዎች አሉት።

ለተጨማሪ መረጃ ድረ ገጻችንን ይጎብኙ፡ http://www.hrw.org

ሰኔ **2004** **1-56432-915-1**

# “ረሃብ ቢመጣ ምን ይኮናል?”

## በኢትዮጵያ የታችኛው ኦሞ ሸለቆ ተወላጅ ሕዝቦች ላይ የተፈጸሙ በደሎች


**የሪፖርቱ ዋና ዋና ነጥቦች ... 1**

**ሊወሰዱ የሚገባቸው ርምጃዎች ... 4**

- ለኢትዮጵያ መንግስት ... 4
- ለኬንያ መንግስት ... 5
- ለልማት አጋሮች ቡድን (ዳግ) ... 5
- በታችኛው የኦሞ ሸለቆ የንግድ ግብርና ኢንቨስት ላደረጉ እና ወደፊት ኢንቨስት ለሚያደርጉ ባለሃብቶች ... 6
- ለተባበሩት መንግስታት የተወላጅ ሕዝቦች መብቶች ልዩ ራፖረተር ... 6
- ለአፍሪካ የሰብአዊና የሕዝቦች መብቶች ኮሚሽን የተወላጅ ሕዝቦች የሥራ ቡድን ... 6

**ሪፖርቱ የተዘጋጀበት መንገድ ... 7**

**I. መንደርደሪያ ... 8**

- ካርታ 1፡ የታችኛው የኦሞ ሸለቆ ... 8
- የታችኛው የኦሞ ሸለቆ ... 9
- የታችኛው ኦሞ እና የቱርካና ሐይቅ [ሕዝቦች] የኑሮ መሠረቶች ... 9
- ካርታ 2፡ በታችኛው የኦሞ ሸለቆ የሚኖሩ ብሔረሰቦች የድንበር ወሰኖች ... 12
- ካርታ 3፡ በታችኛው የኦሞ ሸለቆ የሚካሄደው የስኳር ልማት ዕቅድ ... 13

**II. በታችኛው የኦሞ ሸለቆ ለማካሄድ የታቀደው በመስኖ የሚለማ ግብርና ... 14**

- የአካባቢ እና የማህበራዊ ተጽዕኖ ግምገማ ... 16
- የገንዘብ ምንጭ ... 18
- ትርጉም ያለውና ተገቢ ምክክር አለመደረጉ ... 18
- በኦሞ ሸለቆ በፕሮጀክቶቹ የሚነኩት ማህበረሰቦች ... 19
- ካርታ 4፡ የስኳር ልማት እርሻው በሙርሲና በክዌጉ ብሔረሰቦች በተያዙ መሬቶች ላይ የሚሰራ መሆኑን የሚያሳይ ... 21
- በቱርካና ሐይቅ ላይ የሚኖረው ተጽዕኖ ... 22

**III. በታችኛው የኦሞ ሸለቆ ከሚካሄደው ኢንዱስትሪያዊ ልማት ጋር በተያያዘ የተፈጸሙ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ... 24**

- ሕገ ወጥ እስር ... 25
- ድብደባ እና ማንገላታት ... 26
- በፍራቻ እና በማሸበር ማስተዳደር ... 26
- በኢኮኖሚ፣በማሕበራዊና በባሕል መብቶች ላይ የተፈጸሙ ጥሰቶች ... 28
  - ተገዶ መፈናቀል፣ በአንድ አካባቢ ተወስኖ መኖር እና የታችኛው ኦሞ ... 28
  - በታችኛው የኦሞ ሸለቆ የተካሄደ የመሬት ምንጠራ ... 31

**IV.** የምግብ ዋስትና እና የኑሮ መሠረቶች .......... 32
በከፊል ግብርናና ከብት ርቢ የሚተዳደሩት የቦዲ እና የሙርሲ ብሔረሰቦች .......... 32
የክዌጉ (ሙጉጂ) ብሔረሰብ .......... 35
ወደፊት የሚኖረው ሁኔታ .......... 35

**V.** ከኢትዮጵያ መንግስት እና ከለጋሾች የተሰጡ ምላሾች .......... 37

**VI.** አርብቶ አደርነት፣የመሬት ይዞታ እና የታችኛው ኦሞ ተወላጅ ሕዝቦች መብቶች .......... 40
የመሬት እና ንብረት የመያዝ መብት .......... 40
ነፃ፣ በበቂ መረጃ ላይ የተመሰረተ እና አስቀድሞ የሚሰጥ ስምምነት .......... 42
የሰብአዊ መብቶች ክትትል እና ምክክር በታችኛው ኦሞ .......... 44

ምስጋና .......... 47

አባሪ አንድ፡ሂዩማን ራይትስ ዎች ደቡብ ኦሞን አስመልክቶ ለኢትዮጵያ መንግስት የጻፈው ደብዳቤ .......... 48

አባሪ ሁለት፡ ሂዩማን ራይትስ ዎች ደቡብ ኦሞን አስመልክቶ ለጻፈው ደብዳቤ የሰጠው ምላሽ የኢትዮጵያ መንግስት .......... 51

# የሪፖርቱ ዋና ዋና ነጥቦች

በደቡባዊው የኢትዮጵያ ክፍል የሚገኘው የታችኛው የኦሞ ሸለቆ ለመድረስ እጅግ በጣም ሩቅ ከሆኑት እና ሰፊ የባሕል ስብጥር ከሚታይባቸው የምሥራቅ አፍሪካ አካባቢዎች አንዱ ሲሆን በጣም ልዩ የሆነ ስነ ምህዳራዊ ባሕሪያት ካላቸው የምድራችን ቦታዎችም አንዱ ነው።በሺዎች ለሚቆጠሩ ዓመታት አካባቢውን አቋርጠው ይጓዙ ለነበሩ ሕዝቦች እንደ መስቀለኛ መንገድ ያገለግል እንደነበረ የሚታመነው ይህ ቦታ እጅግ በጣም ጥንታዊ የሆኑ የሰው ልጅ ቅሪተ አካላትና ከሁለት ሚሊዮን ዓመታት በላይ ዕድሜ ያላቸው የሥራ መሣሪያዎች የተገኙበት ቦታ ነው። ቦታው ለዓለማችን ባጠቃላይ ያለውን ባሕላዊና መልክዓ ምድራዊ ፋይዳ ዕውቅና ለመስጠት፣ የተባባሩት መንግስታት ድርጅት የትምህርት፣የሳይንስ እና የባሕል ድርጅት (ዩኔስኮ) የዓለም ቅርስ በማለት እ.ኤ.አ. በ 1980 ሰይሞታል። የታችኛው የኦሞ ሸለቆ ከስምንት ብሔረሰቦች የተውጣጡ ከ 200,000 በላይ የሚሆን ሕዝብ የሚኖርበት ሲሆን ብሔረሰቦቹም፡ ሙርሲ፣ ቦዲ፣ ክዌጉ (ሙጉጂ)፣ ካሮ፣ ሃመር፣ ሱሪ፣ ኛንጋቶም እና ዳሰነች በመባል ይታወቃሉ። እነዚህ ሕዝቦች ሰብላቸውን ለማብቀልና የግጦሽ ሳር ለማሳደግ ከሐምሌ እስከ መስከረም ወራት በውሃ የሚሞላውን 760 ኪሎሜትር ርዝመት ያለውን የኦሞ ወንዝ ተማምነው የሚኖሩ ናቸው።

ይህ ለጉዳት ተጋላጭ የሆነ የአካባቢ ሥነ ምህዳር እና የእነዚህ ሕዝቦች የአኗኗር ዘይቤ ጊቤ ሶስት በመባል በሚታወቀውና በኦሞ ወንዝ ላይ በመገንባት ላይ በሚገኘው ግዙፍ የሃይል ማመንጫ ግድብ እና ከዚያ ጋር ተያይዞ ለማስፋፋት በታቀደው ሰፊ የመስኖ ግብርና ምክንያት አደጋ እየተጋረጠበት ነው። የኢትዮጵያ መንግስት ሰፊ የኢኮኖሚ ልማት ዕቅድ አካል የሆነው የጊቤ ሦስት ግድብ ግንባታ ከ 1998 ዓ.ም ጀምሮ በመገንባት ላይ ሲሆን ከ 2005 ዓ.ም ጀምሮ ሥራ ይጀምራል ተብሎ ይጠበቃል። ጊቤ ሦስት ሰማንያ ሚሊዮን ለሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ እጅግ ተፈላጊ የሆነውን የሃይል አቅርቦት ለማማንጨትና ለጎረቤት ሃገራትም ለመላክ ታስቦ ከሚሰሩት በርካታ ግድቦች ውስጥ አንዱ ሲሆን በቁመቱ ከአፍሪካ ተወዳዳሪ አይኖረውም። ይሁንና ግድቡ ዋጋ እየተከፈለበት ነው። ጊቤ ሦስት በስፍራው የሚኖረውን ሕብረተሰብ ባህላዊና ማህበራዊ አኗኗር እንዲሁም አካባቢውን በከፍተኛ ሁኔታ መንካቱ የማይቀር ነው። በዚህም ምክንያት ከአካባቢ ጥበቃ እና ከተወላጅ ማህበረሰቦች መብቶች ተሟጋቾች ትችት ሲሰነዘርበት ቆይቷል።

ብዙም ትኩረት ያልተሰጠው ጉዳይ ግን በጊቤ ሦስት ግድብ ወንዝ የታችኛው ክፍል መንግስት ለመስራት ያቀደው ሰፊ የመስኖ ግብርና ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ ምንም ዓይነት ዕቅድ ይፋ ያልተደረገ ሲሆን ምንም የተጽዕኖ ግምገማ አልተካሄደም። ለግድቡ ከተደረጉ የተጽዕኖ ግምገማ ጥናቶች በአንዱም ላይ የመስኖ ሥራ ዕቅድ ስለመኖሩ የተጠቀሰ ነገር የለም። የልማት ሥራዎቹ በአካባቢው ነዋሪ ማህበረሰብ እና በኑሮ መሠረታቸው ላይ ስለሚያስከትለው ውጤትም እንዲሁ። ሂዩማን ራይትስ ዎች ያገኛቸው የመንግስት ካርታዎች እንደሚያሳዩት የመስኖ ሥራውና የግብርና ልማቱ የኦሞ ሸለቆን ሰፊ ክልል የሚነኩ ናቸው። የሂዩማን ራይትስ ዎች ጥናት በተጨማሪ እንዳረጋገጠው ከጊቤ ሦስት ግድብ ጋር ተያይዘው ለሚሰሩት ሰፋፊ የመስኖ ልማቶች ቦታ ለማስለቀቅ ሲባል የኢትዮጵያ መንግስት ማስፈራራት፣ሃይልና ሕገ ወጥ እስርን በመጠቀም የአካባቢውን ተወላጅ ማህበረሰቦች ለዘመናት ከኖሩበት የታችኛው የኦሞ ሸለቆ ለቀው እንዲወጡ እያደረገ ነው።

በግንቦት እና በሰኔ ወራት 2003 ዓ.ም ሂዩማን ራይትስ ዎች ኢትዮጵያ ውስጥ ባካሄደው ጥናት ላይ ተመስርቶ የተዘጋጀው ይህ ሪፖርት የኢትዮጵያ መንግስት በኦሞ ወንዝ የታችኛው ክፍል (ግርጌ) በ 245,000 ሄክታር (600,000 ኤከር ወይም 950 ስኩዌር ማይል) መሬት ላይ ለማካሄድ ያቀደውን በመስኖ የሚለማ የመንግስት የስኳር ልማት፣የ100,000 ሄክታር የግል የንግድ ግብርና፣ትልልቅ የመንገድ መሠረተ ልማት እና የነዳጅ ዘይት ፍለጋ ሥራ የሚዘረዝር ነው። ሪፖርቱ ይህ ዕቅድ በታችኛው የኦሞ ሸለቆ በሚኖሩት 200, 000 ተወላጅ ነዋሪዎችና 90 በመቶ የሚሆነውን ውሃውን ከኦሞ ወንዝ በሚያገኘው ኬንያ ውስጥ በሚገኘው በቱርካና ሐይቅ ዙሪያ በሚኖሩ ሌሎች 300,000 ኬንያውያን ሕይወት ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ተጨባጭ እና ከሰብአዊ መብቶች ጋር የተያያዙ ውጤቶች ይዘግባል። የመንግስት ምንጮች የስኳር ልማቱ ከ 150,000 በላይ ለሚሆኑ ሠዎች የሙሉ እና የገሚስ ጊዜ የሥራ እድል እንደሚፈጥር ቢናገሩም አሁን በአካባቢው የሚኖሩት ነዋሪዎች ግን ወደሌሎች አካባቢዎች ሄደው መስፈር እና አማራጭ የኑሮ መሠረቶች ማግኘት አለባቸው።500,000 የሚሆኑ ሰዎች የኑሮ መሠረት አደጋ ላይ እንደሚወድቅ፣ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ከመኖሪያቸው እንደሚፈናቀሉ እና የሚኖረውን አናሳ ሃብት ለማግኘት በሚደረግ ፉክክር ምክንያት በአካባቢው የጎሳ ግጭቶች ሊጨምሩ እንደሚችሉ ተጨባጭ ስጋት አለ።

በ 2003 ዓ.ም ሂዩማን ራይትስ ዎች የአካባቢ ባለስልጣናት እና የጸጥታ ሃይሎች ሕገ ወጥ እስርና አካላዊ ጥቃት መፈጸማቸውን፣ እንዲሁም የተወላጅ ነዋሪዎችን ንብረቶች መውሰዳቸውን ወይም ማውደማቸውን አረጋግጧል። ነዋሪዎቹ እንደሚሉት የጦር ሃይል አባላት ከስኳር ልማቱ ጋር ተያይዞ የሚነሱ ተቃውሞዎችን ለማፈን እና ነዋሪዎችን ለማስፈራራት መንደሮቹን በየጊዜው ይጎበኙ ነበር። እንደአካባቢው ነዋሪዎች ገለጻ ከሆነ ለስኳር ልማቱ ሙሉ ድጋፍን ከመግለጽ ያነሰ

ማናቸውም ነገር ድብደባን፣ማስፈራራትን ወይም እስርን ያስከትላል። በተጨማሪም በታችኛው የኦሞ ሸለቆ በከፊል ግብርናና ከብት ርቢ የተሰማሩ ማህበረሰቦች ለሂዩማን ራይትስ ዎች እንደተናገሩት የከብቶቻቸውን ቁጥር መቀነስ እንደሚኖርባቸው፣ በአንድ አካባቢ መስፈር እንዳለባቸውና በኦሞ ወንዝ ያላቸውን ተጠቃሚነትም ሊያጡ እንደሚችሉ በመንግስት ወኪሎች ተነግሯቸዋል። እነዚህ ሁሉ ነገሮች ለነዋሪዎቹ የኑሮ መሠረት እና የምግብ ዋስትና እጅግ ወሳኝ ናቸው። ወታደሮችም በየጊዜው ከብቶቻቸውን ሰርቀው ይወስዳሉ ወይም ይገድላሉ።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የመሠረተ ልማት አውታሮች ግንባታ እና የመሬት ምንጠራ ከኦሞ ወንዝ ምስራቃዊ ዳርቻ በሚገኘው የቦዲ አካባቢ የተጀመረ ሲሆን በአካባቢው የሚገኙ ማሳዎች ተመንጥረዋል፣ የግጦሽ መሬቶች ጠፍተዋል እንዲሁም የነዋሪዎቹ የኑሮ መሠረቶች ወድመዋል። የመንግስት ካርታዎች እና ሌሎች የአካባቢው ምንጮች እንደሚያሳዩት ይህ በታችኛው የኦሞ ሸለቆ ለማካሄድ ከታሰበው ሰፊ የለውጥ ስራ ገና የመጀመሪያው ክፍል ብቻ ነው።

እነዚህ ለውጦች የሚካሄዱት ምንም ትርጉም ያለው ምክክር ሳይደረግ፣ ስምምነት ሳይኖርና ነዋሪዎቹ ለሚያጡት መሬት፣ የኑሮ መሠረቶች፣ የምግብ ዋስትና እና ለኑሯአቸው እጅግ አስፈላጊ የሆኑ ሃብቶች ካሳ ሳይከፈል ነው። ይህ ደግሞ ብሔራዊና ዓለማቀፍ የሰብአዊ መብቶች መርሆችን የሚጥስ ነው። በተጨማሪም በሰፊው የሚካሄደውን የመስኖ የንግድ ግብርና ልማት እና የጊቤ ሦስት ግድብ ግንባታ ጥምር ውጤት ተከትለው በአካባቢው የሚከሰቱት ከፍተኛ ለውጦች ከዚህ ቀደም በታችኛው የወንዙ ክፍል በተለይም በቱርካና ሐይቅ ላይ ስለሚከተለው ተጽእኖ ተደርሶበት የነበረውን መደምደሚያ ውድቅ የሚያደርጉ ናቸው። ምክንያቱም ከዚህ በፊት የተሰራው የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ የመስኖ ግብርናው በዚህ ስፋት የሚካሄድ ስለመሆኑ የጠቀሰው ነገር ባለመኖሩ ነው።

ዓለማቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሰነዶች፣ የተባበሩት መንግስታት የተወላጅ ሕዝቦች መብቶች ድንጋጌ፣ እንደ የአፍሪካ የሰብአዊና የህዝቦች መብቶች ኮሚሽን ያሉ አህጉራዊ ተቋማት እንዲሁም በየጊዜው እየጨመሩ የመጡት በፍርድ ቤቶችና በእነዚህ ተቋማት የሚሰጡ ውሳኔዎች ተወላጅ ማህበረሰቦች ለዘመናት ከኖሩባቸው መሬቶች ተገደው እንዳይፈናቀሉ የሚያስችሏቸውን መብቶች መጠበቅ አስፈላጊ መሆኑን የሚያረጋግጡ ናቸው። በእነዚህ መርሆች መሰረት ተወላጅ የመሬት ባለይዞታዎች በመሬታቸው ላይ የባለቤትነት መብት ያላቸው ሲሆን ከመሬታቸው ሊነሱ የሚችሉትም ጉዳዩን በተገቢው ሁኔታ ተረድተው ስምምነታቸውን ተጠይቀው ሲስማሙ ብቻ ነው። ለሚያጡት መሬትም ተመጣጣኝ የካሳ ክፍያ ሊከፈላቸውና አማራጭ የኑሮ መሠረቶች ሊመቻቹላቸው ይገባል። ይሁንና እጅግ አናሳ የመደበኛ ትምህርት ያላቸው የታችኛው የኦሞ ሸለቆ ተወላጅ ነዋሪዎች በእነዚህ የልማት ዕቅዶች ላይ ሃሳባቸውን ለመግለጽ ዕድል አግኝተዋል ለማለት አይቻልም፤ በመሬታቸው ላይ የይዞታ ዋስትና እና ምዝገባም የላቸውም።

በዚህ ምትክ ገዢው የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ግንባር (ኢሕአዴግ) በታችኛው የኦሞ ሸለቆ ለሚኖሩ ተወላጅ ማህበረሰቦች የኑሮ ዘይቤ ዋጋ እንደማይሰጥና አርብቶ አደርነት ከደቡብ ኢትዮጵያ ቀስ በቀስ እንዲጠፋ ለማድረግ ያለውን እቅድ በይፋ ገልጿል። ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በጥር 2003 የደቡብ ኦሞ ዞን ዋና ከተማ በሆነችው ጂንካ ላይ ባደረጉት ንግግር እንደገለጹት "ምንም እንኳ ይህ የታችኛው ኦሞ አካባቢ በስልጣኔ ወደኋላ የቀረ ቢሆንም፤ የፈጣን ልማት ምሳሌ ይሆናል።" ብለዋል።

የኢትዮጵያ የውጭ አጋሮች በአሁኑ ወቅት በታችኛው ኦሞ በመካሄድ ላይ ስላለው የልማት እንቅስቃሴና ከዚሁ ጋር ተያይዞ በመፈጸም ላይ ስላሉት በደሎች ያላቸው ዕውቀት ውሱን ይመስላል።በአካባቢው ምንም መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት የማይንቀሳቀስ ሲሆን የተወላጅ ማህበረሰቦቹ አባላት ከመጤዎች ጋር በተለይም ከውጭ ዜጎች ጋር እንዳይነጋገሩ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸዋል።

የኢትዮጵያ መንግስት የልማት እንቅስቃሴዎቹ ከብሔራዊና ዓለማቀፍ የሰብአዊ መብቶች መርሆዎች ጋር በተጣጣመ መልኩ መካሄድ እስኪችሉ ድረስ  ከመስኖ ግብርናው እና ከስኳር ልማቱ ጋር ተያይዘው የሚካሄዱ የመሬት ምንጣሮና የመንገድ ስራዎችን እንዲያቆም ሂዩማን ራይትስ ዎች ጥሪውን ያቀርባል። ሰዎችን ከመኖሪያ አካባቢያቸው አንስቶ ወደሌሎች አካባቢዎች የማስፈር ስራ ዓለማቀፍና የኢትዮጵያ ሕጎችን ያከበረ መሆን አለበት። መሬትን መውረስ (የካሳ ክፍያ ፈጽሞም ቢሆን) የመጨረሻ አማራጭ መሆን ያለበት ሲሆን መፈጸም ያለበትም ሕጉን ተከትሎ ብቻ መሆን ይኖርበታል። የኢትዮጵያ መንግስት የመስኖ ግብርና እንቅስቃሴው፣ የጊቤ ሦስት ግድብ ግንባታ እና ሌሎች በታችኛው ኦሞ የሚካሄዱ የልማት እንቅስቃሴዎች በታችኛው ኦሞ እና በቱርካና ሐይቅ ላይ የሚያስከትሉትን አካባቢያዊና ማህበራዊ ጥምር ተጽእኖዎች የሚዳስስ ግምገማ ማካሄድ አለበት። የልማት እንቅስቃሴዎቹ በኬንያው የቱርካና ሐይቅ እና በአካባቢው በሚኖሩ ኬንያውያን የኑሮ መሠረት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ የሚያስከትሉ በመሆኑ፣ የተሟላ የተጽዕኖ ግምገማ እንድታካሄድ ኬንያ ኢትዮጵያ ላይ ግፊት ማድረግ አለባት።

የኢትዮጵያ ፌደራል መንግስት የክልሉ ወታደራዊና የፖሊስ ሃይሎች የተወላጅ ማህበረሰቦቹን መብቶች እንዲያከብሩ ትዕዛዝ ማስተላለፍ ያለበት ሲሆን በሁሉም ደረጃ የሚገኙና በታችኛው ኦሞ በተፈጸሙ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ተሳትፈው የተገኙ የአስተዳደርና ወታደራዊ ባለስልጣናት ላይ የስነስርዓት እርምጃ መውሰድና ለፍርድ እንዲቀርቡ ማድረግ አለበት። በተጨማሪም መንግስት በታችኛው ኦሞ ተጨማሪ ኢንዱስትሪያዊ ልማት ከማካሄዱ በፊት ከዓለማቀፍ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ከለጋሽ ማህበረሰቡ ጋር በመተባበር ለተወላጅ ነዋሪዎች አማራጭ የኑሮ መሠረቶችን ማመቻቸት በሚያስችሉ ስልቶች ላይ ትርጉም ያለው ውይይት ማድረግ መጀመር አለበት።

የታቀዱ የልማት ሥራዎችን አስመልክቶ የኢትዮጵያ መንግስት ከኦሞ ሸለቆ ተወላጅ ነዋሪዎች ጋር በሚያደርጋቸው ውይይቶች በሙሉ የንብረት መብት፣ የልማት መብት እንደዚሁም አስቀድሞ በሚገኝ በቂ መረጃ ላይ ተመስርቶ የሚሰጥ ነፃ ስምምነት፣ ምክክርና የካሳ ክፍያ መሠረታዊ መርሆች መሆን አለባቸው። ይህ ሳይደረግ ቢቀር የአፍሪካ የሰብአዊና የሕዝቦች መብቶች ኮሚሽን ከዚህ ቀደም በኬንያ የሚገኙ የኢንዶሮይ ተወላጅ ማህበረሰቦችን መብቶች አስመልክቶ ያስቀመጣቸውን መርሆች እዚህም ማጽናት አለበት።

ሂዩማን ራይትስ ዎች በተጨማሪም የዓለም ባንክን ጨምሮ የኢትዮጵያ ለጋሽ ሀገራት ተገቢው ማህበራዊና የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ እንዲካሄድ ግፊት እንዲያደርጉ አጥብቆ ይጠይቃል። አሁን ያሉና ወደፊት የሚመጡ ባለሃብቶችም ለኮርፖሬት ማህበራዊ ሃላፊነት ምርጥ ተሞክሮዎች ተገዢ መሆን፣የተፈጸሙ የመብቶች ጥሰቶች ተጣርተው መፍትሔ እስኪሰጣቸው ድረስም የመሬት ባለቤትነት ውዝግብ ባለባቸውና የግዳጅ ሠፈራ በሚካሄድባቸው አካባቢዎች ኢንቨስት ከማድረግ መታቀብ ይኖርባቸዋል።

# ሊወሰዱ የሚገባቸው ርምጃዎች

## ለኢትዮጵያ መንግስት

- የመስኖ ግብርና ዕቅዱ በሚያስከትለው የአካባቢና ማህበራዊ ተጽዕኖ ላይ ጥናት እስኪደረግ እና የመልሶ ማስፈር ስራ በኢትዮጵያ ሕግ እና በዓለማቀፍ ምርጥ ተሞክሮዎች መሠረት መከናወን እስኪችል ድረስ በታችኛው የኦሞ ሸለቆ የሚካሄዱ የመልሶ ማስፈር ዕቅዶችን ባስቸኳይ እንዲያቆም።

- የዩኔስኮ የዓለም ቅርስ ኮሚቴ ያቀረባቸውን ሃሳቦች በተለይም "በሁሉም የግድብ ሥራዎችና ከዚህ ጋር ተያይዞ በኦሞ ወንዝ ላይ በሚካሄደው የመስኖ ግብርና ላይ የተሰሩ የግምገማ ጥናቶችን እንዲያቀርብ" የሚለውንና "ከዓለም ቅርስ ኮሚቴ እና ከዓለማቀፍ የተፈጥሮ ጥበቃ ህብረት (አይዩሲኤን) የተውጣጣ የልዑካን ቡድን የጊቤ ሦስት ግድብ የቱርካና ሐይቅ ባለው ሁለንተናዊ እሴት ላይ የሚያስከትለውን ተጽዕኖ ለመገምገም እንዲችል ግብዣ እንዲያደርግ እንዲሁም በኦሞ አካባቢ ሊሰሩ የታቀዱ ሌሎች የሃይድሮ ኤሌክትሪክና ተያያዥ ሰፋፊ የመስኖ ግብርና ልማቶችን አስመልክቶ የተሟላ መረጃ እንዲያቀርብ" የሚለውን እንዲቀበል።

- በሁሉም ደረጃ የሚገኙና በታችኛው ኦሞ በተፈጸሙ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ተሳትፈው የተገኙ የአስተዳደርና ወታደራዊ ባለስልጣናት ላይ የስነስርዓት እርምጃ እንዲወስድና ለፍርድ እንዲቀርቡ እንዲያደርግ።

- ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን በመፈጸም በዓለማቀፍ ሕግ እና በኢትዮጵያ ሕገ መንግስት የተረጋገጡትን የታችኛው ኦሞ ተወላጅ ሕዝቦች መብቶች በፍጥነት እንዲያስከብር፡
    - o የታችኛው ኦሞ ሕዝቦች በመሬታቸው ላይ ሊገፈፉ የማይችሉ መብቶች ያሏቸው መሆኑን እና ለዘመናት በይዞታቸው ስር አድርገው ሲጠቀሙበት በኖሩት መሬት ላይ ላላቸው የንብረት ባለቤትነት መብት እውቅና በመስጠት ፤
    - o በተለይ ለአርብቶ አደሮች የጋራ የግጦሽ ክልልን የሚያካትት የመሬት ይዞታ ዋስትናን የሚያረጋግጥ የይዞታ ምዝገባ ስርዓት በመዘርጋት፣
    - o የአካባቢውን ነዋሪዎች ከመሬት መወረስ በመጠበቅ እና፣
    - o እውነተኛ የምክክር እና የካሳ ክፍያ ስርዓት በመዘርጋት።

- በተጨማሪም መንግስት በታችኛው ኦሞ ተጨማሪ ኢንዱስትሪያዊ ልማት ከማካሄዱ በፊት ከዓለማቀፍ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ከሲጋሽ ማህበረሰቡ ጋር በመተባበር ለተወላጅ ነዋሪዎች አማራጭ የኑሮ መሠረቶችን ማመቻቸት በሚያስችሉ ስልቶች ላይ ትርጉም ያለው ውይይት ማድረግ መጀመር አለበት። እነዚህ ስልቶች በተቻለ መጠን የተወላጅ ሕዝቦችን ዘመን ያስቆጠረ የአኗኗር ዘይቤ በማክበርና እነዚህ ወገኖች በበቂ መረጃ ላይ የተመሰረተ እንዲሁም ምንም ዓይነት ርምጃ ከመወሰዱ በፊት የሚሰጡትን ነፃ ስምምነት የማክበርን ግዴታ የኢትዮጵያ መንግስት በአካባቢው ያቀደውን የልማት ግብ ለማሳካት ባለው ፍላጎት መካከል ያለውን ሚዛን ለመጠበቅ የሚያስችሉ መሆን አለባቸው ።

- በታችኛው ኦሞ የሚካሄዱ የግብርና ልማት እንቅስቃሴ ዕቅዶች ከዓለማቀፍ ምርጥ ተሞክሮዎችና ከኢትዮጵያ ሕግ (የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ አዋጅ ቁጥር 299/94) ጋር የተጣጣመ እና ሰፊ፣ ግልጽነት ያለው እንዲሁም በዓለማቀፍ ደረጃ ሊረጋገጥ የሚችል የአካባቢና ማህበራዊ ተጽእኖ ግምገማ እንዲያካሂድ። ይህም የሚከተሉትን ያካተተ እንዲሆን፡
    - o ይፋ የተደረጉት የልማት ሥራዎች ማለትም የጊቤ ሦስት፣ አራት እና አምስት፣ የመስኖ ሥራ ዕቅዶች እንዲሁም የመንገድ መሠረተ ልማቶች በታችኛው የኦሞ ሸለቆ እና በቱርካና ተፋሰስ በሚኖሩ ተወላጅ ሕዝቦች የኑሮ መሠረት እና ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ መብቶች ላይ የሚያስከትሉትን ጥምር ተጽዕኖ የሚተነትን።
    - o በፕሮጀክቱ ሳቢያ ሊጨምር ከሚችለው ሃብትን ለመያዝ የሚደረግ ፉክክር ጋር ተያይዞ ሊከሰት የሚችለውን ግጭት እና የግጭቱን ባሕርይ ከግምት ውስጥ ያስገባ፣ የግጭት ተጋላጭነት ግምገማን።

- o የአካባቢው ተወላጅ ማህበረሰቦችን ልዩ ሁኔታና ፍላጎት የሚያንጸባርቅ እንዲሁም በዓለማቀፍና በኢትዮጵያ ሕጎች መሠረት በበቂ መረጃ ላይ የተመሰረተና መሬታቸው ከመወሰዱና ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት ነጻ ስምምነታቸውን የመግለጽ መብታቸውን ያከበረ ትርጉም ያለው ውይይት ማካሄድን።

- የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ሕግ፣ የመገናኛ ብዙሃንና የመረጃ ነፃነት ሕግ እንዲሁም የፀረ ሽብርተኝነት ሕግ መሻር ወይም ከኢትዮጵያ ሕገ መንግስትና ከዓለማቀፍ መርሆች ጋር የተጣጣሙ እንዲሆኑ ማሻሻል እንደዚሁም ነፃ የሰብአዊ መብቶች መርማሪዎች እና መገናኛ ብዙሃን በታችኛው ኦሞ አካባቢ ያለገደብ እንዲንቀሳቀሱ መፍቀድ።

## ለኬንያ መንግስት

- የጊቤ ግድቦችና በታችኛው ኦሞ የሚካሄደው የመስኖ ግብርና ልማት በቱርካና ሐይቅ እና በኬንያ ዜጎች ላይ የሚያስከተሉትን ጥምር ተጸዕኖ የሚመለከት አዲስ ግልጽነት ያለውና ሊረጋገጥ የሚችል የአካባቢ፣ ማህበራዊና የግጭት አደጋ ግምገማ እንዲያካሂድ የኢትዮጵያ መንግስት ላይ ግፊት ማድረግ።

- ከኢትዮጵያ መንግስት እና ከሚመለከታቸው የቱርካና ሐይቅ አካባቢ ተወላጅ ነዋሪዎች ጋር የኑሮ መሠረት መብቶቻቸውን ጨምሮ ያሏቸው መብቶች በሚከበሩበት ሁኔታ ላይ እንዲሁም በቱርካና እና በታችኛው ኦሞ አካባቢዎች ግጭቶችን መከላከል በሚቻልባቸው ስልቶች ላይ መወያየት።

- ከዓለማቀፍ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና ከለጋሽ ሃገራት ጋር በመተባበር አማራጭ የኑሮ መሠረቶችን አስመልክቶ ኬንያ ውስጥ በቱርካና ሐይቅ አካባቢ ከሚኖሩ ተወላጅ ማህበረሰቦች ጋር ትርጉም ያለው ውይይት ማካሄድ።

## ለልማት አጋሮች ቡድን (ዳግ)

- የኢትዮጵያ መንግስት የግብርና ልማት ዕቅዶቹና በታችኛው የወንዙ ክፍል የሚያስከትሉትን ጥምር ተጽዕኖ የሚዳስስ ተገቢውን የማህበራዊና የአካባቢ ተጽዕና ግመገማ እንዲያካሂድ እንዲሁም የአካባቢው ተወላጅ ሕዝቦች ላሏቸው የመሬት ይዞታ ዋስትና፣ የምክክር፣ነጻና በበቂ መረጃ ላይ ተመስርቶ የሚሰጥ ስምምነትን የመግለጽ እና የካሳ ክፍያ መብቶች እውቅና እንዲሰጥ ግፊት እንዲያደርጉ።የኢትዮጵያ መንግስት ከብሔራዊ ሕጎቹና እና በዓለማቀፍ ደረጃ ካሉበት የሰብአዊ መብቶች ግዴታዎቹ ጋር በተጣጣመ መልኩ እና ተገቢና ግልጽነት ባለው መልኩ መካሄድ እስኪችሉ ድረስ ቀጣይ የመልሶ ማስፈር እንቅስቃሴዎችን እንዲያቆም ግፊት እንዲያደርጉ።

- በዕርዳታ የሚሰጡት ገንዘብ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ በታችኛው ኦሞ አካባቢ የሚካሄድን ሕገ ወጥ የመሬት መውረስ ለመደገፍ መዋል አለመዋሉን ለማረጋገጥ ነጻ እና ጥልቀት ያለው ማጣራት እንዲካሄድ እንዲያደርጉ።

- የሚሰጡት ማናቸውም ዓይነት ድጋፍ ማለትም የገንዘብ (ቀጥተኛም ሆነ ቀጥተኛ ያልሆነ የበጀት ድጋፍ)፣ የዲፕሎማቲክ ወይም የቴክኒክ ድጋፍ ከታችኛው ኦሞ ተወላጅ ማህበረሰቦች ላይ የዓለማቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሕግን በመጣስ በተወረሰ መሬት ላይ የሚካሄድን የልማት እንቅስቃሴ ለማገዝ እንዳልዋለ እንዲያረጋግጡ።

- የካርታ ዝግጅትንና የመሬት ባላቤትነትን ወሰን ክለላ ሥራን ጨምሮ በከፊል ግብርናና ከብት ርቢ የሚተዳደሩ የአካባቢው ተወላጅ ማህበረሰቦችን የመሬት ይዞታ ዋስትና ስርዓት ወቅቱን በጠበቀ መንገድ ስራ ላይ ለማዋል የሚያስችል ድጋፍ እንዲሰጡ።

- የታቀዱት የልማት ሥራዎች ተግባራዊ ከመደረጋቸው በፊት መንግስት ከአካባቢው ተወላጅ ማህበረሰቦች ጋር አማራጭ የኑሮ መሠረቶችን ማመቻቸትን አስመልክቶ ውይይት እንዲያደርግ በኢትዮጵያ መንግስት ላይ ግፊት እንዲያደርጉ።

- ኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አዋጅ፣ የመገናኛ ብዙሃንና የመረጃ ነጻነትን አዋጅ እንዲሁም የፀረ ሽብርተኝነትን አዋጅ እንድታሻሽል ወይም እንድትሽር በይፋ ጥሪ እንዲያቀርቡ።

- የኢትዮጵያ መንግስት የሚያካሂዳቸው የመልሶ ማስፈር እንቅስቃሴዎች በተገቢና ግልጽነት ባለው መንገድ እንዲሁም ከብሔራዊ ሕጎቹ እና ከዓለማቀፍ የሰብአዊ መብቶች ግዴታዎቹ ጋር በተጣጣመ መልኩ የሚካሄዱ መሆኑን እስኪያሳይ ድረስ የመሬት መወረስ ስጋት ሊያስከትሉ የሚችሉ አዳዲስ መርሃ ግብሮችን ከመደገፍ እንዲታቀቡ።

## በታችኛው የኦሞ ሸለቆ የንግድ ግብርና ኢንቨስት ላደረጉ እና ወደፊት ኢንቨስት ለሚያደርጉ ባለሃብቶች

- በዚህ ሪፖርት የተዘረዘሩት የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች እስኪገቱና መፍትሔ እስኪሰጣቸው ድረስ፣ የታችኛው ኦሞ አካባቢ ተወላጅ ነዋሪዎች ነጻ እና በበቂ መረጃ ላይ ተመስርቶ አስቀድሞ የተሰጠ ስምምነት በሌለበት ሁኔታ በተገኘ አወዛጋቢ መሬት ላይ በሚካሄድ የግብርና ልማት እንቅስቃሴ ላይ ከመሰማራት እንዲታቀቡ።

## ለተባበሩት መንግስታት የተወላጅ ሕዝቦች መብቶች ልዩ ራፖረተር

- በኢትዮጵያ የተወላጅ ሕዝቦች የሰብአዊ መብቶች ያለበትን ሁኔታ ለመገምገም እንዲችል የኢትዮጵያ መንግስት የጉብኝት ፈቃድ እንዲሰጠው እንዲጠይቅ።

## ለአፍሪካ የሰብአዊና የሕዝቦች መብቶች ኮሚሽን የተወላጅ ሕዝቦች የሥራ ቡድን

- በኢትዮጵያ የተወላጅ ሕዝቦች የሰብአዊ መብቶች ያለበትን ሁኔታ ለመገምገም እንዲችል የኢትዮጵያ መንግስት የጉብኝት ፈቃድ እንዲሰጠው እንዲጠይቅ።

# ሪፖርቱ የተዘጋጀበት መንገድ

ይህ ሪፖርት የተዘጋጀው የሂዩማን ራይትስ ዎች መርማሪዎች በግንቦት እና ሰኔ 2003 ዓ.ም ለአራት ሳምንታት ኢትዮጵያ ውስጥ ባደረጓቸው 35 ቃለ ምልልሶች ላይ በመመስረት ነው። ቃለ ምልልሶቹ የተካሄዱት በሪፖርቱ ውስጥ የተዘረዘሩት የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች በተፈጸሙ በሦስት ሳምንታት ጊዜ ውስጥ ነው።

ቃለ መጠይቅ ከሰጡ ሰዎች መካከል የማህበረሰብ መሪዎች፣ አርሶ አደሮች፣ አርብቶ አደሮች፣ ተማሪዎች፣ የስነ ሰብዕ ጥናት ባለሙያዎች፣ የሃይማኖት ሰዎች፣ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሠራተኞች ይገኙባቸዋል። እነዚህ ሰዎች በታችኛው ኦሞ ከሚኖሩ የሙርሲ፣ የቦዲ፣ የሃመር፣ የሱሪ፣ የካሮ፣ እና የኛንጋቶም ተወላጅ ማህበረሰቦች የተውጣጡ ናቸው። ማንነታቸው እንዳይገለጽ የጠየቁ በርካታ የመንግስት ሠራተኞችም በቃለ መጠይቁ ተሳትፈዋል። በተጨማሪም ሂዩማን ራይትስ ዎች ምሁራንን፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተሚጋቾችን፣ እንዲሁም ስለታችኛው ኦሞ እውቀት ያላቸውን ሌሎች ግለሰቦችና ድርጅቶችን አነጋግሯል።

በመስከረም ወር 2004 ዓ.ም ሂዩማን ራይትስ ዎች ከዋና ዋና የለጋሽ ሀገራት/ድርጅቶች ተወካዮች እና ከሂዩማን ራይትስ ዎች ጋር ለመነጋገር ፈቃደኛ ከሆኑ የኢትዮጵያ መንግስት ባለስልጣናት ጋር አስር ሌሎች ቃለ ምልልሶችን አድርጓል።የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ባለስልጣናት አስተያየት ለመስጠት ፈቀደኛ ያልሆኑ ሲሆን የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስትሩ ደግሞ ቃለ መጠይቅ ለማድረግ ለቀረበላቸው ጥያቄ ምላሽ ሳይሰጡ ቀርተዋል። የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ሚኒስትሩ በረከት ስምኦን ደግሞ የሂዩማን ራይትስ ዎች መርማሪ ኢትዮጵያን ከለቀቀ ከሳምንት በኋላ ምላሽ ሰጥተዋል።

በቃለ መጠይቁ የተሳተፉ ሁሉም ወገኖች ስለ ቃለ መጠይቁ ዓላማ፣ በፈቃደኝነት የሚካሄድ ስለመሆኑ፣ እንዲሁም መረጃው ስለሚሰበሰብበትና ጥቅም ላይ ስለሚውልበት ሁኔታ ማብራሪያ የተሰጣቸው ሲሆን ቃለ መጠይቁን ለማድረግ ስምምነታቸውን በቃል ገልጸዋል። ተሳታፊዎቹ ምንም ዓይነት ክፍያ አልተከፈላቸውም።

በሰኔ ወር 2003 የተደረገውን የመስክ ጉብኝት ተከትሎ በአካባቢው ከሚንቀሳቀሱ አስተባባሪዎች፣ ከተጎጂዎች እንዲሁም አካባቢውን ከጎበኙ ሰዎች ጋር ግንኙነቶች ተደርገዋል። በተጨማሪም በመስክ ጥናት የተገኙትን መረጃዎች የሚያጠናክርና በህዳርና ታህሳስ ወራት 2004 ዓ.ም በታችኛው ኦሞ ነዋሪ ከሆኑ ሰዎች ጋር የተደረጉ ቃለ ምልልሶችን የያዘ የቪዲዮ ምስል ሂዩማን ራይትስ ዎች ለማግኘት ችሏል።

በቃለ መጠይቁ የሚሳተፉ ሰዎችን ለማግኘት ሂዩማን ራይትስ ዎች ልዩ ልዩ የግንኙነት መስመሮቹን የተጠቀመ ሲሆን የተወሰደው ናሙና በጾታ፣ በዕድሜ፣ በብሄር ተዋጽኦና በአካባቢ ተመጣጣኝ ውክልናን የሚያሳይ እንዲሆን ጥረት ተደርጓል። ቃለ መጠይቆቹ ለደህንነት በማያሰጉና ወጣ ባሉ ቦታዎች፣ በአብዛኛው በመንደሮች ውስጥ ባሉ መኖሪያ ቤቶች የተካሄዱ ሲሆን በእንግሊዝኛ፣ በአማርኛ እና አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ በአካባቢው ያሉ አስተርጓሚዎችን በመጠቀም በአካባቢው ከሚነገሩት በርካታ ቋንቋዎች በአንዱ ተካሂደዋል።

የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አዋጅ፣ የፀረ ሽብርተኝነት አዋጅ፣ በመገናኛ ብዙሃን ነጻነት ላይ የተቀመጠው ገደብ፣ የተለዩ ሃሳቦችን ለማስተናገድ ያለው የፈቃደኝነት ማጣትና በአጠቃላይ በኢትዮጵያ የሰፈነው የማወከብና የፍርሃት ድባብ በውጭ ሀገር ዜጎችም ሆነ በኢትዮጵያውያን ግለሰቦችና ድርጅቶች የሚደረግን የሰብአዊ መብቶች ምርምራ እና ክትትል ስራ እጅግ ፈታኝ አድርጎታል። ባለፉት ጥቂት ዓመታት ከዓለማቀፍ መርማሪዎች ጋር የተገናኙ በደንብ የሚታወቁ ኢትዮጵያውያን ሳይቀሩ ለሕገ ወጥ እስር እና ፖለቲካዊ መነሾ ላላቸው ክሶች ተዳርገዋል።

በሰፈነው የፍርሃት ድባብና በቃለ መጠይቅ ተሳታፊዎች ደህንነት ላይ ሊደርስ በሚችለው ከባድ መዘዝ ሳቢያ ደህንነትታቸውን እና ምስጢራዊነትን በጠበቀ መልኩ ቃለ መጠይቅ የሚሰጡ ሰዎችን የማፈላለግ እና የመለየት ሥራ አስቸጋሪ ነው። በቃለ መጠይቁ የተሳተፉ አብዛኞቹ ሰዎች በመንግስት ሊወሰድባቸው የሚችለውን የበቀል ርምጃ አስመልክቶ ስጋታቸውን ገልጸዋል፤ እነዚህ ስጋቶች ደግሞ ትክክለኛ ናቸው። ስለዚህ በእነዚህ ስጋቶች ምክንያት እና በሰብአዊ መብቶች የአሰራር መርሆች መሠረት ለዚህ ሪፖርት ዝግጅት ቃለ መጠይቅ የሰጡ ግለሰቦችን እና ማህበረሰቦችን ስሞች፣ ቀኖች እና ሌሎች መለያ ሊሆኑ የሚችሉ ጠቋሚዎችን በግለሰቦቹ ወይም በሚወክሉት ማህበረሰብ ላይ መንግስት የበቀል ርምጃ ሊወስድ የሚችልበትን ዕድል ለመቀነስ ሲባል ሂዩማን ራየትስ ዎች ከመግለጽ ተቆጥቧል።

# I. መንደርደሪያ

## ካርታ 1፡ የታችኛው የኦሞ ሸለቆ




© ጆን ኤመርሰን/ሂዩማን ራይትስ ዎች

## የታችኛው የኦሞ ሸለቆ

በኢትየጵያ የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የሚገኘው የታችኛው ኦሞ ሸለቆ በምድር ላይ እጅግ ሰፊ የሥነ ሕይወትና የባሕል ስብጥር ከሚገኝባቸው ቦታዎች አንዱ ሲሆን ከመሃል ሀገር በጣም ርቀ የሚገኝና በልማት ወደኋላ የቀረ አካባቢ ነው።ከኬንያ እና ከደቡብ ሱዳን ጋር የሚዋሰነው የታችኛው ኦሞ እና የኦሞ ወንዝ በሚፈስበት ተጎራባቹ የቱርካና ሐይቅ የሚገኙት ብሔራዊ ፓርኮች እ.ኤ.አ. ከ1980 እና 1997 ጀምሮ በቅደም ተከተል በዩኔስኮ በዓለም ቅርስነት የተመዘገቡ ናቸው።

በታችኛው ኦሞ የሚኖሩት 200,000 የሚሆኑ ሕዝቦች[1] ከስምንት ተወላጅ ማህበረሰቦች የተውጣጡ ናቸው። መንገዶችና የመሠረተ ልማት አውታሮች ውሱን ናቸው፤ ያሉት የጤና ተቋማትና ትምህርት ቤቶች ቁጥርም በጣም ጥቂት ነው። በመንግስት እና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የሚሰጡ አገልግሎቶች አሉ ማለት አይቻልም። በርከት ያለ ቁጥር ያላቸው ተወላጅ ማህበረሰቦች ከሚኖሩባቸው ሌሎች የኢትዮጵያ አካባቢዎች ለየት ባለ ሁኔታ በታችኛው የኦሞ ሸለቆ ወጣ ብለው በሚገኙ ዋና ዋና ከተሞች የሚኖሩት ተወላጅ ያልሆኑ ሕዝቦች ቁጥር አነስተኛ ነው።ስለሆነም ተወላጅ ማህበረሰቦቹ ስለ ሰፊ የኢንዱስትሪ ልማት ያላቸው ተሞክሮ ውሱን ነው።[2]

አብዛኞቹ ተወላጅ ማህበረሰቦች አርብቶ አደሮች ወይም በከፊል ግብርናና ከብት ርቢ[3] ላይ የተሰማሩ ሲሆን በተለያዩ ብሔረሰቦች አባላት መካከል እጥረት ባለበት የግጦሽ መሬት እና በውሃ ሳቢያ አነስተኛ ግጭቶች በየጊዜው ይከሰታሉ።[4] እያንዳንዱ ማህበረሰብ አነስተኛ ቁጥር ያለው ሲሆን ብዙዎቹም ከተጎራባች ማህበረሰቦች ወይም ከመንግስት ጋር በየጊዜው አይገናኙም። እስካሁን ድረስ መንግስት አካባቢውን ለማልማት የነበረው ትኩረት ብሔራዊ ፓርኮችን እና ቱሪዝምን በማስፋፋት ላይ ያተኮረ ነበር።[5] የኦሞ ብሔራዊ ፓርክ በ 1950 ዎቹ መጨረሻ፣ የማጎ ብሔራዊ ፓርክ ደግሞ በ 1960 ዎቹ አጋማሽ ላይ ተቋቁመዋል።

## የታችኛው ኦሞ እና የቱርካና ሐይቅ [ሕዝቦች] የኑሮ መሠረቶች

ምግብና የኑሮ መሰረት የማግኘት፣ የልማት እና ንብረት የማፍራት መብቶች አርብቶ አደሮችን ጨምሮ ለሁሉም ተወላጅ ማህበረሰቦች በዓለማቀፍ ደረጃ እና በኢትዮጵያ ሕገ መንግስትም የተረጋገጡ መብቶች ናቸው።[6]

*ሔስኦጂኣርሊኤሔች* አማካሪዎች የተባለ ድርጅት ለአውሮፓ የኢንቨስትመንት ባንክ ሰርቶ በ ግንቦት ወር 2002 ባጠናቀቀው ነጻ ጥናት ላይ እንደገለጸው 48 በመቶ የሚሆነው የታችኛው ኦሞ ሕዝብ በወንዙ ፍሰት ለሚካሄድ ግብርና ወይም የግጦሽ

---

1 ስምንቱ ተወላጅ ሕዝቦች ሙርሲ፣ሱሪ፣ከዌጉ፣ዳሰነች፣ኛንጋቶም፣ካሮ፣ሃመር እና ቦዲ በመባል ይታወቃሉ።ሌሎች በርካታ ብሄረሰቦች በዙሪያው የሚኖሩ ሲሆን እነዚህ ስምንቱ ግን በመስኖ ልማቱ በዋነኛነት የሚነኩት ናቸው።ስለ ተወላጅ ሕዝቦቹ ጠቅለል ያለ መረጃ እና የጊቤ ሦስት ግድብ በኑሮ መሠረታቸው ላይ ስለሚያስከትለው ተጽዕኖ ኢንተርናሽናል ሪቨርስ “Facing Gibe 3: Indigeneous Communities of Ethiopia’s Lower Omo Valley,” በሚል ርዕስ እ.ኤ.አ. በጃንዋሪ 2009 ያወጣውን ዘገባ በ http://www.internationalrivers.org.files/attached-files/loweromovalleyfinal.pdf (ጁን 29/2011 የታየ) ይመልከቱ። በተጨማሪም የአፍሪካ ልማት ባንክ “Gibe lll Hydroelectric Power Project Environmental and Social Impact Assessment,” 2009, http://www.afdb.org/fileadmin/uploads/afdb/Documents/Project-and-Operations/Gibe%2011_EIA_%20Executive%20Summary%20EBJK%2006-08-06.pdf (ዲሴምበር 13/2011 የታየ)

2 እንደ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ እና ጋምቤላ ባሉ ሌሎች ቆላማ አካባቢዎች ከደጋማ አካባቢዎች ሰዎች መጥተው መስፈራቸው ከረጅም ጊዜ ጀምሮ የተለመደ ነው።ይህ ከደጋማ አካባቢዎች ወደ ቆላማ አካባቢዎች የሚደረግ የሕዝቦች ሰፈራ በታችኛው ኦሞ ብዙም አልተካሄደም።

3 የአርብቶአደርነት ትርጓሜ በሰፊው የሚለያይ ቢሆንም ሁሉም ትርጓሜዎች ግን ከብት ማርባትን እና አንድ ዓይነት ከቦታ ቦታ የመዘዋወር ገጽታ ያለው በመሆኑ ላይ የሚያተኩሩ ናቸው። ከፊል አርብቶ አደርነት እና ግብርና ደግሞ አርብቶ አደርነትንና በአንድ ቦታ ላይ በመስፈር የሚሰራ ግብርናን ጥምር ባሕሪያት የያዘ ነው። ብዙዎቹ የታችኛው ኦሞ ተወላጅ ነዋሪዎች በከፊል ግብርናና ከብት ርቢ ላይ የተሰማሩ ሲሆን ከብት ከማርባት በተጨማሪ በኦሞ ወንዝ ዳርቻ እና በሌሎች ለም መሬቶች ላይ እህል ያበቅላሉ። በአርብቶ አደርነት ትርጓሜ ላይ ተጨማሪ ማብራሪያ ለማግኘት አይሲዩኤን ያወጣውን “Definitions for WISP,” 2006, http://data.iucn.org/wisp/pastoralism-definitions.html ይመልከቱ

4 ፋርም አፍሪካ፣ “Integrated Patoralist Project, South Omo,” 2012, http://www.farmafrica.org.uk/ethiopia/integrated-pastoralist-project (ኦገስት 18/2011 የታየ)

5 ቴሪ ሃታዌይ፣ “Ethiopia’s Endangered Lower Omo Valley, “ ጃንዋሪ 2009፣ http://www.internationalrivers.org/en/node/2794 (ጁላይ 13/2011 የታየ)

6 የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት ቁጥር 1/1995፣ አንቀጽ 40፣41 እና 43

ሳር ለማብቀል በኦሞ ወንዝ ላይ ሙሉ በሙሉ ተማምኖ የሚኖር ነው።[7] ይህም በየዓመቱ ከሐምሌ እስከ መስከረም ወራት ባለው ጊዜ በመምጣት ለእርሻ ተስማሚ የሆነ ለም እና እርጥብ አፈር ትቶ የሚሄደውን ጎርፍ በመከተል ወቅታዊ ግብርና የሚያካሂዱትን የቦዲ፣ የሙርሲ፣ የክዌጉ፣ የካሮ፣ የኛንጋቶም እና የዳሰነች ብሔረሰቦች ይጨምራል። የዳሰነች ብሔረሰብ አባላት በተጨማሪም በደረቅ ወራት የሚጠቀሙበትን የግጦሽ መሬት ለማልማት ዓመታዊውን ጎርፍ ይፈልጉታል።[8] ጥናቱ በወንዙ ዳርቻዎች የግብርና ሥራን ከሚሰሩት ሕዝቦች ጋር የንግድ ግንኙነት ያላቸውን እና በዚህም ምክንያት በተዘዋዋሪ መንገድ በኦሞ ወንዝ ላይ ጥገኛ የሆኑትን ሕዝቦች ያካተተ አይደለም።

አንድ የሙርሲ ብሔረሰብ ተወላጅ እንደተናገሩት፡

> የኦሞ ወንዝ ሕይወታችን ነው፤ ኑሮአችንን ለመምራት በከፍተኛ ሁኔታ የምንተማመነው በወንዙ ነው። የኑሮአችን መሠረት እንደመሆኑ ሕይወትን ከወንዙ ውጭ ማሰብ አንችልም።ስለዚህ አንድ ሰው ሕይወቱ ፍጹም አደጋ ላይ እንደሆነ ሲነገረው ሊሰማው የሚችለውን ስሜት መገመት ይቻላል።[9]

በታችኛው ኦሞ የሚኖሩት አብዛኞቹ ህዝቦች በተወሰነ ደረጃ በከብት ማርባት ላይ የተሰማሩ ናቸው። የኢትዮጵያ መንግስት እነዚህ ሕዝቦች የአርብቶ አደርነት የኑሮ ዘይቤአቸውን እንዲተዉ ያለው ፍላጎት ከማንም የተደበቀ አይደለም።አርብቶአደሮች የሕይወት ዘይቤአቸውን ወደ ቋሚ ግብርና እንዲለወጡ መገፋፋት ኢትዮጵያ ውስጥ ከረጅም ጊዜ ጀምሮ ሲደረግ የነበረ ነው።[10] በ 1998 የወጣው የኢትዮጵያ የአርብቶ አደር ልማት ፖሊሲ ከቦታ ቦታ በመዘዋወር የሚኖሩ አርብቶ አደሮች በፈቃደኝነት ወደቋሚ ግብርና እንዲሸጋገሩ በማድረግ ኑሮአቸውን በቋሚ ግብርና እና በቅጥር ሠራተኝነት እንዲመሩ ስለማስቻል ይናገራል።[11] በወቅቱ የግብርና እና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ሚኒስትር ደ ኤታ የነበሩት  አበራ ደሬሳ መንግስት ስለ አርብቶ አደርነት ያለውን አመለካከት ለቢቢሲ ሲገልጹ እንደተናገሩት፡

> ዞሮ ዞሮ አርብቶ አደሮች ባሉበት ሁኔታ መቅረታቸውን ብዙም የምንደግፈው ነገር አይደለም። የሥራ ዕድሎችን በመፍጠር የኑሮ መሠረታቸውን ማሻሻል አለብን። አርብቶ አደርነት በራሱ ዘላቂነት የለውም። ያለውን ሁኔታ መቀየር እንፈልጋለን።[12]

በኢትዮጵያ የአርብቶ አደር አካባቢዎች የሚሰራው ሥራ ዋነኛ ዓላማ "የከብቶችን ከቦታ ቦታ ዝውውር ለመቀነስ፣ወቅትን ተከትሎ በሚደረግ የሰዎችና የከብቶች ከቦታ ቦታ ዝውውር ላይ ከተመሰረተ የሕይወት ዘይቤ ይልቅ በአንድ ቦታ በመስፈር የሚካሄድን ቋሚ የጥምር ግብርና ልማት ለማበረታታት የታለመ ነው።"[13] በደረቅና ከፊል ደረቅ በሆኑ አካባቢዎች የሚካሄድ አርብቶ አደርነት ከብቶች ዓመቱን ሙሉ ሊግጡ የሚችሉት ሳር እና ውሃ የሚገኝበት ሰፊ መሬትን ይፈልጋል። ይህ የአኗኗር ዘይቤ ኢትዮጵያ ለታችኛው ኦሞ ካላት የልማት ዕቅድ ጋር የሚጣጣም አይደለም። ምክንያቱም ይህ ዕቅድ መሬትን በሰፊው ለመጠቀም ሲባል የግጦሽ መሬቶችን እና በጅረቶች አካባቢ የሚበቅልን አነስተኛ ጫካ መመንጠርን የሚያካትት በመሆኑ ነው።

---

7 ኤስኦጂአርኢኤኤች አማካሪዎች "Independent Review and Studies regarding the Environmental and Social Impact for the Gibe 111 Hydroelectric Project," ግንቦት 2009 ሂዩማን ራይትስ ዎች ዘንድ የሚገኝ

8 ስለታችኛው ኦሞ ተወላጅ ሕዝቦች የኑሮ መሠረቶች ተጨማሪ ማብራሪያ ለማግኘት ዩኤስኤይድ፣ "SNNPR Ethiopia Livelihood Profiles," ጃንዋሪ 2006 ይመልከቱ። http://www.dppc.gov.et/Livelihoods/Downloadables/Regional%20review.pdf በተጨማሪም የደለል ግብርና ተብሎ የሚታወቀው የእርሻ ስራ ዓመታዊ ጎርፍ በሚያገኙት የኦሞ ወንዝ ዳርቻዎች ይካሄዳል።የጎርፉ ውሃ ሲቀንስ ጎርፉ ባመጣው ርጥብና ለም የአፈር ደለል ላይ እርሻው ይጀመራል።

9 ይህ ጥቅስ የተወሰደው የኢትዮጵያ መንግስት በሚያዝያ 2003 የጊቤ ሦስት ግድብ የሚሰራበትን አካባቢ ለአርብቶ አደሮች ባስጎበኘበት ወቅት ካወጣው ሪፖርት ከገጽ 5-6 ነው። http://www.gibe3.com.et

10 የአፍሪካ የሰብአዊና የሕዝቦች መብቶች ኮሚሽን "Report of the African Commission's Working Group of Experts on Indigenous Populations/Communities" 28th ordinary session, 2005, http://pro169.org/res/materials/en/identification/ACPHR%20REport%20on%20indigenous%20populations-communities.pdf (ሴፕቴምበር 4/2011 የታየ)

11 የኢትዮጵያ መንግስት የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር "በአርብቶ አደር ልማት ፖሊሲ ላይ የተሰጠ መግለጫ" 1994

12 የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ሚኒስትር ደ ኤታ አበራ ዴሬሳ ከቢቢሲ ጋር ታህሳስ 7፣ 2003 ያደረጉት ቃለ ምልልስ http://www.bbc.co.uk/news/business-11991926

13 ኤ.ሙሉጌታ እና ቲ.ሃግማን "Governing Violence in the Pastoralist Space: Karrayu and state notions of cattle raiding in the Ethiopian Awash Valley" Afrika Focus 21(2): 71-87, 2008 http://www.nccrr-north-south.unibe.ch/publications/Infosystem/Online%20Dokumente/Upload/2008_Mulugeta_Hagmann_Governing%20violence.pdf (ኦገስት 3/2011 የታየ)

አሁን ያለውን የአርብቶ አደር የኑሮ ዘይቤ የኢኮኖሚ ልማት በደረቅ ወቅት የግጦሽ መሬት ላይ ከሚፈጥረው ጫና ጋር አጣጥሞ ማስኬድ ያለምንም ጥርጥር ከሰሜናዊ አፍሪካ ከሴኔጋል እስከ ሱዳን ድረስ በሳህል አካባቢ ያሉ የምስራቅና የሰሜን አፍሪካ ሀገራት የሚጋፈጡት ትልቅ ፈተና ነው። ሆኖም ግን በአርብቶ አደር አካባቢዎች የሚደረግ የልማት ስራ በተፈጥሮው ፈታኝ መሆኑ ቢታወቅም ኢትዮጵያ ግን አርብቶ አደርነት ለሚኖረው እምቅ ኢኮኖሚያዊ አቅም እውቅና የሚሰጡ እና ለአርብቶ አደር ልማት ስርዓት ቁልፍ የሆኑ የጋራ እና ባህላዊ የመሬት ይዞታ መብቶችን የሚያረጋግጡ ሌሎች አማራጮችን ከመፈተሽ ይልቅ መፍትሔ ሊሆኑ የሚችሉ ሀሳቦችን ሁሉ አርብቶ አደሮችን ወደቋሚ የኑሮ ዘይቤ ማሸጋገር ላይ ብቻ ማተኮሯን ቀጥላለች።[14]

ከአርብቶ አደርነት በአንድ ቦታ ተወስኖ ወደመኖር የሕይወት ዘይቤ ሽግግርን ለማምጣት በሌሎች የኢትዮጵያ ክልሎች የተደረጉ ሙከራዎች (ለምሳሌ በምስራቃዊ ኢትዮጵያ የአዋሽ ሸለቆ[15]) ስምምነት ሳይኖር እና በቂ ዝግጅት ሳይደረግ በሃይል ከላይ ወደታች የወረዱ በመሆናቸው ምክንያት በርካታ ያልታሰበባቸው አደጋዎችን አስከትለዋል።[16]


---

14 ፒተር ዲ. ሊትል እና ሌሎች “Policy Options for Pastoral Development in Ethiopia and Reactions from the Regions: Report Number 4, Pastoral Economic Growth and Development,” ኦክቶበር 2010

15 ሂዩማን ራይትስ ዎች “Waiting Here for Death”: Forcede Displacement and Villagization in Ethiopia’s Gambella Region, ጃንዋሪ 2012፣ http://hrw.org/reports/2012/01/16/waiting-here-death እና አያሌው ገብሬ፣ “When Pastoral Commons are Privatised: Resource Deprivation and Changes in Land Tenure Systems among the Karrayu in the Upper Awash Valley Region of Ethiopia,” የ 16ኛው ዓለማቀፍ የኢትዮጵያ ጥናት ጉባዔ ሪፖርት 2009


16 “ከላይ ወደታች” የሚወርድ ልማት ማለት በበላይ አካላት ቁጥጥር እና አመራር የሚካሄድና በሚቀረጽበት ጊዜም ሆነ በሌላ በየትኛውም ደረጃ ተጠቃሚዎቹ ትርጉም ባለው መልኩ የማይሳተፉበት የልማት ሞዴል ነው።

## ካርታ 2፡ በታችኛው የኦሞ ሸለቆ የሚኖሩ ብሔረሰቦች የድንበር ወሰኖች




ይህ ካርታ የተዘጋጀው ከሙርሲ ኦንላይን (www.mursi.org) በተገኘ መረጃ ላይ በመመስረት ነው። የብሔረሰብ ወሰኖቹ በግምት የተሰሩና ለማሳያነት ብቻ እንዲውሉ የታሰቡ ናቸው። ©2011 ማሞት የካርታ ሥራ/ሂዩማን ራይትስ ዎች

## ካርታ 3፡ በታችኛው የኦሞ ሸለቆ የሚካሄደው የስኳር ልማት ዕቅድ




ይህ ካርታ የተዘጋጀው ሂዩማን ራይትስ ዎች ካገኛቸው የኢትዮጵያ መንግስት ካርታዎች ላይ በተገኙ መረጃዎች ላይ በመመስረት ነው።ካርታው የሚያሳየው የታችኛውን የኦሞ ወንዝ ክፍል በማቋረጥ የኦሞ እና የማጎ ብሔራዊ ፓርኮችን መሃል ለመሃል ሰንጥቆ እስከ ቱርካና ሐይቅ የሚዘልቀውን ከ 200 ኪሎሜትር በላይ ርዝመት ያለው የመስኖ መስመር ነው።ካርታው በተጨማሪም ለንግድ ግብርና ልማት ለግል ባለሃብቶች የተሰጡና በሊዝ ለማከራየት ተዘጋጅተው የተቀመጡ መሬቶችን ያሳያል።በተጨማሪም በሁለቱም የኦሞ ወንዝ ዳርቻዎች ብሎክ አንድ ሁለትና ሦስት ተብሎ ለስኳር ልማት የተከለለ ሰፊ የመሬት ክልልን ያሳያል።ይህ መሬት ከጥንት ጀምሮ የሙርሲ፣የቦዲ እና የክዌጉ ብሔረሰብ አባላት በይዞታቸው ስር አድርገው ሲጠቀሙበት የነበረ ነው።©2011 ማሞት የካርታ ሥራ/ሂዩማን ራይትስ ዎች

## II. በታችኛው የኦሞ ሸለቆ ለማካሄድ የታቀደው በመስኖ የሚለማ ግብርና

የኢትዮጵያ መንግስት በታችኛው የኦሞ ሸለቆ እና በዚያ በሚኖሩ ሕዝቦች የኑሮ ሁኔ ላይ ከፍተኛ ለውጥ ለማምጣት ሰፊ ዕቅድ አለው። የሃይድሮኤሌክትሪክ ልማት፣ በመስኖ የሚለማ የንግድ ግብርና በተለይም የስኳር ልማት እንዲሁም ከፍተኛ የመንገድ ስራ መሠረተ ልማቶች እና የነዳጅ ዘይት ፍለጋ ስራ በአካባቢው ሊሰሩ እንደታቀዱ ከሚታወቁት ዕቅዶች ውስጥ ይገኛሉ። ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በጥር ወር 2003 እንደተናገሩት፡

> በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት በዚህ ዞን የሚሰራ በጣም ትልቅ የመስኖ ፕሮጀክትና ተያይዘው የሚሰሩ የግብርና ልማቶች ይኖራሉ።ቃል እገባላችኋለሁ፣ ይህ አካባቢ በስልጣኔ ወደኋላ በመቅረቱ የሚታወቅ ቢሆንም የፈጣን ልማት ምሳሌ ይሆናል።[17]

ይሁንና እስካሁን ድረስ ከፕሮጀክቱ ጋር የተያያዙ የአካባቢ እና ማህበራዊ ተጽዕኖ ግምገማ ዕቅድ ይፋ አልተደረገም። ከአካባቢው ተወላጅ ሕዝቦችም ጋር በሃይል ሊጫንባቸው የታሰቡትን ለውጦች አስመልክቶ ምንም ዓይነት ትርጉም ያለው ወይይት አልተደረገም። የመስኖ ፕሮጀክቱ ተጀምሮ በደንብ በመካሄድ ላይ ሲሆን ነዋሪዎችም ከመኖሪያቸው እንዲለቁ እየተደረገ ነው።

ሂዩማን ራይትስ ዎች ያገኛቸው የመንግስት ካርታዎች እንደሚያሳዩት እ.ኤ.አ. ከ2008[18] ጀምሮ የኢትዮጵያ መንግስት 450,000 ሄክታር የሚደርስ በታችኛው የኦሞ ሸለቆ የሚገኝ መሬት ለንግድ ግብርና የመደበ ሲሆን ይህም በመንግስት ባለቤትነት ለሚካሄደው የመስኖ የስኳር ልማት[19] የተመደበውን 245,000 ሄክታር የሚጨምር ነው።ዕቅዱ ከኦሞ ወንዝ የምእራብ እና የምስራቅ ዳርቻዎች ትይዩ የሚያልፉ ከ200 ኪሎሜትር በላይ ርዝመት ያላቸው የመስኖ መስመሮች፣ከ750 ኪሎሜትር በላይ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች እና ስድስት የስኳር ማምረቻ ፋብሪካዎችን ግንባታ የሚጨምር ነው።[20] ሌሎች በአካባቢው ከታቀዱ ልማቶች መካከል ክልሉን እንደ ሞምባሳ-ናይሮቢ-አዲስ አበባ ኮሪዶር ካሉ ክፍለ አህጉራዊ የትራንስፖርት መረቦች ጋር ለማገናኘት ታስቦ የታቀደው የምስራቅ-ምዕራብ እና የሰሜን-ደቡብ የመንገድ መሠረተ ልማት ይገኝበታል።[21] በተጨማሪም የነዳጅ ዘይት ፍለጋ እንቅስቃሴ ከኬንያ ድንበር አጠገብ በታችኛው ኦሞ ደቡባዊ ክፍል በኛንጋቶም እና ዳሰነች አካባቢዎች በመካሄድ ላይ ይገኛል።በዚህ አካባቢ ያለው ባህልና የተፈጥሮ ሃብት ከፍተኛ ጫና ያርፍበታል ተብሎ ይጠበቃል።[22] ኢትዮጵያ በተጨማሪም የጊቤ አራትና አምስት ግድቦችን በኦሞ ሸለቆ የታችኛው ክፍል የመስራት ዕቅድ አላት።[23]

---

[17] ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ 13ኛው ዓመታዊ የአርብቶ አደሮች ቀን በደቡብ ኦሞ ጂንካ ውስጥ በተከበረበት ዕለት፣ ጥር 17 ቀን 2003፣ www.murs.org/pdf/Meles%20Jinka%20speech.pdf (ጁላይ 23, 2011 የታየ)

[18] ይህ መረጃ ሂዩማን ራይትስ ዎች በመጋቢት እና በሰኔ ወራት 2003 ባገኛቸው የመንግስት ካርታዎች እና በመሬት ኢንቨስትመንተ ውሎች ላይ የተመሠረተ ነው።።ብዙዎቹ ውሎች በግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ድረ ገጽ http://www.eap.gov.et/index.php?q+=node/835 ላይ ይገኛሉ

[19] ይህ መረጃ ሂዩማን ራይትስ ዎች በሰኔ ወር 2003 ባገኛቸው የመንግስት ካርታዎች ላይ የተመሰረተ ነው። የመንግስት የሆነው ኩራዝ ስኳር ኮርፖሬሽን ዳይሬክተር ጄነራል አባይ ፀሐዬ ከ 1999-1997 ድረስ የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስትር የነበሩ ናቸው። ይህ የሚኒስቴር መስሪያ ቤት በሃገሪቱ የፖሊስ እና የደህንነት ስራን ይቆጣጠራል።ግለሰቡ አሁንም የጠቅላይ ሚኒስትሩ የጸጥታ እና የኢንተለጀንስ አማካሪ ናቸው። የሕዝባዊ ወያኔ ሃርነት ትግራይ (ሕወሃት) መስራች አባልም ናቸው።

[20] ቸሬ እናውጋው፣ደርቤ ደክሲዎስ እና ግርማ ቲመር፣ “Existing Challenges: Plantation Development versus Wildlife Conservation in the Omo-Tana-Mago Complex” የኢትዮጵያ ዱር አራዊት ጥበቃ ባለስልጣን፣ ሴፕቴምበር 2010

[21] አብነት አሰፋ፣ “Omo River Bridge Caves in Mid-Construction” አዲስ ፎርቹን ሜይ 8, 2011

[22] 29,465 ኪሎ ሜትር የሚረዝመው የነዳጅ ዘይት እና ጋዝ ፕሮጀክት በአፍሪካ አይል ኮርፖሬሽን (30 በመቶ)፣ቱሎው አይል (50 በመቶ)፣እና ዋይት ናይል (20 በመቶ)በጋራ ባለቤትነት የተያዘ ነው። ይህ ውል ባለቤቶቹ ቢያንስ 500 ኪሎሜትር የርደት እና አንድ የጥልቅ ጉድጓድ ቁፋሮ ፍለጋ እንዲያካሂዱ ያስገድዳል። አፍሪካ አይል ኮርፖሬሽን፣ “ኢትዮጵያ”፣ http://www.africaoilcorp.com/s/Ethiopia.asp?ReportHD=352253 ከአፍሪካ አይል ኮርፖሬሽን በቅርብ ጊዜ የተገኘ መረጃ 1018 ኪሎሜትር በርደት የሚሰራ የፍለጋ እንቅስቃሴ በ2012 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ይጠናቀቃል ተብሎ እንደሚጠበቅና የጉድጓድ ፍለጋ ስራ ደግሞ በ2012 ሁለተኛ ግማሽ ዓመት እንደሚጀመር ያሳያል።አፍሪካ አይል ኮርፖሬሽን ሌሎች አራት የነዳጅ ፍለጋ ውሎች በኦጋዴን ያሉት ሲሆን ይህ አካባቢ የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃነት ግንባር ለረጅም ጊዜ የቆየ የሽምቅ ውጊያ የሚያካሂድበት ነው።ሂዩማን ራይትስ ዎች በዚህ ውጊያ ውስጥ የጦር ወንጀሎች እና በሰብአዊ ፍጡር ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች መፈጸማቸውን የሚያሳዩ መረጃዎችን አሰባስቦአል። ሂዩማን ራይትስ ዎች “Collective Punishment:War Crimes and Crimes Against Humanity in the Ogaden area of Ethiopia’s Somali Region” በሚል ርዕስ በ ጁን 2008 ያወጣውን ሪፖርት http://www.hrw.org/reports/2008/06/11/collective-punishment ላይ ይመልከቱ

[23] ጂን ባልቦአ፣ “China, Ethiopia strike $ 1.9 B hydroelectric deal” Shanghai Daily, ጁላይ 17, 2009

እንደ መንግስት ምንጮች ገለጻ ከሆነ እነዚህ ልማቶች ከ 150,000 በላይ የሙሉ እና የገሚስ ጊዜ ሥራዎችን እንደሚፈጥሩ ይጠበቃል።[24] ይሁንና በታችኛው የኦሞ ሸለቆ የሚገኘው አብዛኛው መሬት በከፊል ግብርናና ከብት ርቢ ኑሮአቸውን በሚገፉ ተወላጅ ማህበረሰቦች የተያዘ ነው (ካርታ 2ን ይመልከቱ)። እንደካርታዎቹ ከሆነ አሁን በአካባቢው የሚኖሩት ነዋሪዎች ወደሌላ አካባቢ ሄደው መስፈርና ኑሮአቸውን ለመምራት የሚያስችላቸው አማራጭ የኑሮ መሠረት ማግኘት እንደሚኖርባቸው ግልጽ ነው።

የመልሶ ማስፈር ሥራ በኢትዮጵያ ያለው ታሪክ መልካም የሚባል አይደለም። በሌሎች የኢትዮጵያ ክልሎች መንግስት እ.ኤ.አ ከ 2010 መጨረሻ ጀምሮ በአራት የተለያዩ ክልሎች የሚገኙ 1.5 ሚሊዮን የሚደርሱ አርብቶ አደሮችን፣ ከፊል አርብቶ አደሮችን እና ከቦታ ቦታ በመዘዋወር መሬት የሚያርሱ ወገኖችን "የመንደር ምስረታ/ሰፈራ" በሚባለው ፕሮግራሙ ቋሚ በሆኑ መንደሮች እንዲሰፍሩ እያደረገ ነው።[25] *"ሞትን እዚሁ መጠበቅ":የግዳጅ ማፈናቀልና ሰፈራ በኢትዮጵያ የጋምቤላ ክልል* በሚል ርዕስ በቅርቡ ሂዩማን ራይትስ ዎች ያወጣው ሪፖርት እንደሚያሳየው በዚያ ክልል የተደረጉት የመልሶ ማስፈር ስራዎች በፈቃደኝነት ላይ ያልተመሰረቱ፣ይሚላሉ ተብሎ ቃል የተገቡ የመሠረተ ልማት ተቋማትና አገልግሎቶች ያልተሚሉባቸው እንዲሁም የጦር ሃይሉ በሰላማዊ ዜጎች ላይ የተለያዩ በደሎችን ሲፈጽም የተስተዋለባቸው ነበሩ።[26]

በታችኛው ኦሞ ከሚካሄደው የስኳር ልማት ጋር ተያይዘው የሚካሄዱት የመልሶ ማስፈር እንቅስቃሴዎች የፌደራል መንግስቱ በሚያካሂደው የሰፈራ ፕሮግራም ውስጥ የተካተቱ አይደሉም።ይሁንና በቅርቡ የተደመጡ የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ሪፖርቶች በታችኛው ኦሞ የሚካሄዱትን የመልሶ ማስፈር እንቅስቃሴዎች የሰፈራው አካል እንደሆኑ አድርገው ማቀረብ ጀምረዋል።[27] ለምሳሌ ያህል በኢትዮጵያ የመንግስት መገናኛ ብዙሃን የወጣ ሪፖርት እ.ኤ.አ በ2010 እና 2011 ብቻ 10,995 የሚሆኑ አርብቶአደር ቤተሰቦች በደቡብ ኦሞ ዞን ሰላማጎ ወረዳ[28] እንዲሰፍሩ መደረጉንና ሌሎች 20,000 ቤተሰቦችም በ2011 እና 2012 ሊሰፍሩ ፕሮግራም የተያዘላቸው መሆኑን ያመለክታል።[29] በመከተል በየካቲት 2004 የወጣ ሌላ የመንግስት መገናኛ ብዙሃን ሪፖርት ደግሞ በተያዘው የበጀት ዓመት መንግስት 10,300 ፈቃደኛ አርብቶ አደሮችን በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በተለይም በደቡብ ኦሞ ዞን መልሶ ለማስፈር ዕቅድ መያዙን ይገልጻል። ሪፖርቱ በተጨማሪም "ፕሮግራሙ የሃገሪቱን አርብቶ አደር አካባቢዎች የልማት ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ መንግስት በከፍተኛ ጥንቃቄ የቀየሰው ሰፊ የመልሶ ማስፈር መርሃ ግብር ስልት አካል ነው። ሁሉም የሰፈራ ፕሮግራሙ ተጠቃሚዎች አስፈላጊው የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መሠረተልማቶች የተሟሉላቸው መሆኑን" ያትታል።[30] የኢትዮጵያ ለጋሾች ከሰፈራ ፕሮግራሙ ጋር የተያያዙ አገልግሎቶች አለመኖራቸውን አስመልክተው ስጋታቸውን ገልጸዋል።[31] እነዚህ ስጋቶች በታችኛው ኦሞ የሚካሄደውን የመልሶ ማስፈር እንቅስቃሴ የሚመለከቱ መሆን ይኖርባቸዋል።

ስለዕቅዶቹ በርግጠኝነት የሚታወቀው ጉዳይ የመስኖ መስመሮቹ እና የስኳር ልማቱ በሚነካቸው አካባቢዎች በአሁኑ ጊዜ የሚኖሩት ማህበረሰቦች በኦሞ ወንዝ ያላቸውን ተጠቃሚነት በከፊል ወይም በሙሉ እንደሚያጡ ነው። ይህም የኑሮ መሠረታቸውን እና የከፊል ግብርናና ከብት ርቢ የሕይወት ዘይቤአቸውን ለከፋ አደጋ የሚያጋልጥ ነው።በግንቦት ወር 2003 የስኳር ልማቱን በሚመለከት በሃና ከተማ በተካሄደ ሕዝባዊ ስብሰባ ላይ የተሳተፉ አንድ ሰው በዚያ የሆነውን ሲያስታውሱ፡

> መንግስት አብዛኛውን መሬት እንደሚወስድና ሕዝቡን በትልልቅ መንደሮች እንደሚያሰፍር፣ለጠቅላላው
> የቦዲ ሕዝብ የመስኖ መስመሩን ተከትሎ የሚመሰረቱ አምስት መንደሮች እንደሚኖሩ ባለስልጣናቱ ግልጽ

---

24 ይህ ፕሮጀክት የመንግስት የአምስቱ ዓመት "የዕድገት እና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ" አካል ሲሆን በ2006/2007 የስኳር ምርትን ከ 300,000 ቶን ወደ 2,300,000 ቶን ለማሳደግ ያለመ ነው።አሁን ያለው የስኳር ፍጆታ 500,000 ቶን ሲሆን ጉድለቱ ከውጭ የሚገባ ነው።ቸሬ እናውጋው፣ደርቤ ደክሲዎስ እና ግርማ ቲመር (ከላይ የግርጌ ማስታወሻ 20 ላይ የተጠቀሰውን ይመልከቱ)

25 ዊሊያም ዳቪሰን፣ "Ethiopia plans ambitious resettlement of people buffeted by East African drought" ክርስቲያን ሳይንስ ሞኒተር፣ ኦገስት 1,2011, http://www.csmonitor.com/World/Africa/2011/0801/Ethiopa-plans-ambitious-resettlement-of-people-buffeted-by-East-Africa-drought (ኦገስት 1,2011 የታየ)

26 ሂዩማን ራይትስ ዎች፣ "Waiting Here for Death"

27 "State to Villagize  over 20,200 pastoralist household," ዋልታ ኢንፎርሜሽን ማዕከል ዲሴምበር 26,2011 http://www.waltainfo.com/index.php?option=com_content&view=article&id=1111:state-to-villagize-over-20000-pastoralist-households&catid=52:national-news&itemid=291 (ዲሴምበር 28, 2011 የታየ)። ስለሰፈራው ወይም "ጋርዮሽ" ቀደም ብለው በመንግስት የወጡ መግለጫዎች የተቀሱት አራቱን ማለትም ጋምቤላ፣አፋር፣ቤኒሻንጉል ጉሙዝ እና ሶማሌ ክልሎችን ብቻ ነበር። ለተሟላ ማብራሪያ "Waiting Here for Death" ይመልከቱ

28 ወረዳ የአካባቢ አስተዳደር ነው

29 "State to Villagize  over 20,200 pastoralist household," ዋልታ ኢንፎርሜሽን ማዕከል

30 "SNNPR plans to benefit a hundred thousand pastoralists", ዋልታ ኢንፎርሜሽን ማዕከል, ፌብሯሪ 27, 2012, http://www.waltainfo.com/index.php?option=com_content&view=article&id=2076:snnpr-plans-to-benefit-a-hundred-thousand-pastoralists&catid=52:national-news&Itemid=291 (ፌብሯሪ 28, 2012 የታየ)

31 ሂዩማን ራይትስ ዎች ከብሪታንያ፣ከኔዘርላንድስ፣ከስዊድን፣ከኖርዌይ፣ከዩናይትድስቴትስ እና ከዓለም ባንክ ዲፕሎማቶች ጋር ያደረገው ቃለ መጠይቅ ጥር-የካቲት 2004

> አድርገዋል።ሰፋሪዎቹን በስኳር እርሻ ልማቶቹ እንዲሰሩ አበረታትተዋቸዋል።በቀን 70 ብር እንደሚከፈላቸውም ተነግሯል።[32]

የአካባቢው ነዋሪዎች ለሂዩማን ራይትስ ዎች እንደተናገሩት የቦዲ ብሄረሰብ አባላት ቢያንስ በሦስት የተለያዩ የሰፈራ ጣቢያዎች እንዲሰፍሩ ተደርገዋል።የዐይን ምስክሮች እንደገለጹትም የመልሶ ማስፈር እንቅስቃሴው እስከ የካቲት ወር 2004 ድረስ እየተካሄደ ነበር።[33]

## የአካባቢ እና የማህበራዊ ተጽዕኖ ግምገማ

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን በ1997 ዓ.ም "የአካባቢ እና የማህበራዊ ተጽዕኖ ግምገማ" ፤ "ተጨማሪ የታችኛው ተፋሰስ ተጽዕኖ ጥናት" እና ሁለት ቅጽ ያለው ለጊቤ ሦስት ግድብና ውሃ ማጠራቀሚያ የመልሶ ማስፈር የድርጊት መርሃ ግብር አሰርቷል።[34] እነዚህ ሰነዶች ይፋ የተደረጉት የግድብ ግንባታ ሥራው ከተጀመረ ከሦስት ዓመታት በኋላ በጥር 2001 ዓ.ም ነው። ጥናቶቹ ሰፋፊ የመስኖ ግብርና ሥራዎቹና ሊሰሩ የታቀዱት የጊቤ አራትና አምስት ግድቦች በታችኛው የተፋሰሱ ክፍል ሊኖራቸው የሚችለውን ተጽዕኖ ከግምት ውስጥ ያስገቡ አልነበሩም። የመልሶ ማስፈሩ የድርጊት መርሃ ግብር ለኤሌክትሪክ ማስተላለፊያ መስመሮች፣ ለመንገድ ቅየሳና ከጊቤ ሦስት ግድብ ጀርባ ለሚሰራው የውሃ ማጠራቀሚያ ሲባል ከመኖሪያቸው ስለሚፈናቀሉና ወደሌሎች አካባቢዎች ስለሚሰፍሩ 2278 ዜጎች ብቻ የሚናገር ነበር።[35] የመልሶ ማስፈሩ የድርጊት መርሃ ግብር በአሁኑ ወቅት ከጊቤ ሦስት ግድብ ግርጌ በሚገኙ የስኳር ልማት ሥራ በሚካሄድባቸው አካባቢዎች በመከናወን ላይ ያለውን መልሶ ማስፈር የሚጨምር አይደለም።

የኤሌክትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን ያሰራው ይኸው የተጸዕኖ ግምገማ ከተለያዩ ወገኖች ትችት ተሰንዝሮበታል።አፍሪካን ሪሶርስስ ግሩፕ የተባለ ጉዳዩ ያሳሰባቸው ኤክስፐርቶችን[36] ያካተተ ጥምረት በጊቤ ሦስት ግድብ ምክንያት የሚመጡ ያላቸውን ዋና ዋና ተጽኖዎች ዘርዝሯል። ከእነዚህም መካከል ወደ ቱርካና ሐይቅ የሚፈሰው ውሃ መጠን መቀነስ፣[37] በኢትዮጵያና በኬንያ የሚኖሩ ሕዝቦች የኑሮ መሠረቶች ላይ የሚደርሰው ጥፋት፣የግጦሽ መሬትና ውሃ ለማግኘት በሚደረግ ፉክክር ምክንያት የጎሳ ግጭቶች ሊጨምሩ ስለመቻላቸው፣በታችኛው የተፋሰሱ ክፍል አካባቢያዊ የስነምህዳር ስርዓት ላይ ስለሚደርሰው ሰፊ ጥፋት እና በደቡብ ኦሞ ወንዝ እና በመላው የኦሞ ሦስትዮሽ/ዴልታ/ የሰፈሩ ሕዝቦች የሚያካሂዷቸው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች መጥፋትና ይህንን ተከትሎ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ከፊል ግብርናና ከብት ርቢ ላይ የተሰማሩ ወገኖች የሚደርስባቸውን የኢኮኖሚ ድቀት የሚጨምር ነው።[38]

የአፍሪካ ልማት ባንክ ያሰራውና በኋላ ሾልኮ የወጣ አንድ ጥናት ፕሮጀክቱ አስቀድሞ ምክክር ያልተደረገበት መሆኑን ይተቻል፡

> በግድብ ግንባታው በጣም የሚጎዱት ወገኖች እና መንደሮች የግድብ ስራው በሚጸድቅበት፣ፈቃድ በሚሰጥበትና ለስራው አስፈላጊ የሆነው ገንዘብ በሚለቀቅበት በየትኛውም ወቅት ተሳትፎአቸውን

---

32 ሂዩማን ራይትስ ዎች ከአንድ የታችኛው ኦሞ ነዋሪ ጋር ያደረገው ቃለ ምልልስ፣ታችኛው ኦሞ፣ ሰኔ 10, 2003

33 ሂዩማን ራይትስ ዎች የታችኛውን ኦሞ ከጎበኘ ሰው ጋር ያደረገው ቃለ ምልልስ

34 የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን፣ "Environmental and Social Impact Assessment", ጃንዋሪ 2009 እና "Resettlement Action Plan: Dam and Reservoir Area", ጃንዋሪ 2009, www.gibe3.com.et (ኤፕሪል 2, 2012 የታየ)

35 በሰፈራው የድርጊት መርሃ ግብር መሠረት ይህ ከግድቡ አካባቢ 744፣ ከኤሌክትሪክ ማሰራጫ መስመሮቹ 490 እንዲሁም ከመንገድ ግንባታው 1044 ሰዎችን የሚጨምር ነው።

36 የአፍሪካ ሪሶርስስ ዎርኪንግ ግሩፕ "ከዩናይትድ ስቴትስ፣ ከአውሮፓ እና ከምስራቃዊ አፍሪካ የተውጣጡ፣ኢትዮጵያን ጨምሮ በአፍሪካ ቀንድ በሚካሄዱትልልቅ የውሃ ግድቦች፣የተፋሰስ ልማት ምርምርና ፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ሰፊ ልምድ ያላቸው ምሁራንና አማካሪዎችን ያካተተ ስብስብ ነው።በአካባቢው የሙያ ስራን ማካሄድ ባለው ፖለቲካዊ አንድምታ ምክንያት የዚህ ቡድን አባላት ማንነታቸውን ይፋ ማድረግ አልመረጡም።" አፍሪካ ሪሶርስስ ግሩፕ "Commentary on the Environmental,Socioecnomic and Human Rights impacts of the Proposed Gibe 111 Dam in the Lower Omo River Basin", ጃንዋሪ 2009, http://www.arwg-gibe.org/uploads/ARWG_COMMENTARY›GIBE_111_DAM.downstreamEIA.pdf (ኦገስት 1/2011 የታየ)

37 የኬንያው የቱርካና ሐይቅ በዓለም ትልቁ የበረሃ ሐይቅ ሲሆን 80 በመቶ የሚሆነውን ውሃውን የሚያገኘው ከኦሞ ወንዝ ነው። የአፍሪካ ሪሶርስስ ዎርኪንግ ግሩፕ እንደሚለው የሐይቁ የውሃ መጠን ከ10-20ሜትር ዝቅ ሊል ይችላል።ይህ ደግሞ የኑሮ መሠረታቸውን በሐይቁና ውስጡ ባለው ሐብት ላይ ያደረጉ 300,000 ኬንያውያንን ሕይወት ለአደጋ የሚያጋልጥ ነው። የአፍሪካ ሪሶርስስ ዎርኪንግ ግሩፕ፣ "Commentary on the Environmental,Socioecnomic and Human Rights impacts of the Proposed Gibe 111 Dam in the Lower Omo River Basin", ጃንዋሪ 2009, http://www.arwg-gibe.org/uploads/ARWG_COMMENTARY›GIBE_111_DAM.downstreamEIA.pdf

38 ዝኒ ከማሁ

> እንዲያሳዩ የሚያስችላቸው በቂ ሕጋዊ ውክልና ያገኙ አይመስልም። የማጽደቁና ፈቃድ የመስጠቱ ሂደትም ቢሆን የጊቤ ሦስትን ፕሮጀክት ከመተግበር ጋር ተያይዞ እንጂ ራሱን ችሎ የተሰራ አልነበረም።[39]

የኤሌክትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን ያካሄደው የተጽዕኖ ግምገማ በመደምደሚያው "እንዲወሰዱ የተጠየቁት ርምጃዎች በሙሉ ተግባራዊ ከተደረጉ፣ በጊቤ ሦስት የሀይድሮአሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ፕሮጀክት ምክንያት ልማዳዊ የአኗኗር ዘይቤአቸው የሚታወክባቸው ብሔረሰቦችም ሆነ ጎሳዎች አይኖሩም።ስለዚህ ለተወላጅ ሕዝቦች ልማት የሚባል ምንም ዓይነት ዕቅድ አስፈላጊ አይሆንም።"[40] ይላል።

ይህ አባባል የወንዙን ውሃ ፍሰት በታችኛው ክፍል ዓሳ በማጥመድና ከብት በማርባት የሚተዳደሩትን ማህበረሰቦች በማይጎዳ መልኩ በትክክል በመቆጣጠር ላይ የተመሰረተ ነው።ይሁን እንጂ ይህ የመስኖ መስመሮቹና የስኳር ልማቱ የሚያስከትሉትን ተጽዕኖ ከግምት ውስጥ ያስገባ አይደለም። መንግስት በቅርቡ ዩኔስኮ ፕሮጀክቱን በሚመለከት ላነሳቸው ስጋቶች በሰጠው ምላሽ እንኳን፣ በግድቡ ምክንያት "የመንገዶች፣የጤና ጣቢያዎች፣የትምህርት ቤቶችና የሌሎች ልማቶችን አቅርቦቶች ጨምሮ የሚመጡ አንዳንድ ባህላዊና የአኗኗር ዘይቤ ለውጦች በርግጥ ይኖራሉ።"[41] በማለት ይገልጻል። እነዚህ ለውጦች መደረግ ያለባቸው ምክክር ከተደረገ፣የካሳ ክፍያ ከተጸመ፣በበቂ መረጃ ላይ ተመስርቶ የሚሰጥ ስምምነት ከተገኘ በኋላ  እንዲሁም የልማት አጋሮች ቡድን (ዳግ) ለኢትዮጵያ መንግስት እንዲተገብረው በሰጠው መመሪያ መሠረት ነው።[42] የኤሌክትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን ግምገማ በዚህ ሁኔታ ለተወላጅ ሕዝቦች የሚሆን ዕቅድ አስፈላጊ አይደለም ሲል መደምደሙ ትልቅ ግድፈት ነው።

የኤሌክትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን ግምገማ ስለንግድ ግብርና የጠቀሰው አንድ ነገር ቢኖር "የመስኖ ስራ ሊኖር ስለመቻሉ" እና "ወደፊት ሊመጣ ስለሚችለው የንግድ እንቅስቃሴ" ብቻ ነው።[43] ስለታችኛው ተፋሰስ የተደረገው ጥናት፣ እንደ ስኳር ልማቱ ያለ በመንግስት የሚካሄድ ሰፊ የግብርና ልማት የሚያስከትለውን ተጽዕኖ መናገር ግምት ብቻ ይሆናል በማለት ሳያካትተው ቀርቷል፡

> የታቀደው ሰፊ የንግድ ግብርና ልማት በርግጠኝነት ሰፊ ለጥ ያለ መሬት ባለበት ከኦሞ ወንዝ ሦስትዮሽ አጠገብ በሚገኘው የዳሰነች ወረዳ ሜዳማ አካባቢ የሚሰራ ነው።አሁን ባለበት ደረጃ የኢንቨስትመንቱ መጠን ምንያህል ሊሆን እንደሚችል ከግምት ያለፈ ሃሳብ መስጠት አይቻልም። ይሁንና ለውይይት ያህል ቢያንስ 5000 ሄክታር መሬት እንደሚለማና ልማቱም የጥጥ ልማት ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል።[44]

ሆኖም ግን ከአንድ ዓመት በኋላ ሂዩማን ራይትስ ዎች ባገኛቸው ያልታተሙ የመንግስት ካርታዎች (ከላይ ይመልከቱ) ላይ ለሚታየው የስኳር ልማት የሚሆን 245,000 ሄክታር መሬት መንግስት መመንጠር ጀመረ። ወንዙ የቱርካና ሐይቅን የሚቀላቀልበት የኦሞ ወንዝ ሦስትዮሽ የዳሰነች ወረዳ አሁን የስኳር ልማት ከሚካሄድባቸው አካባቢዎች ራቅ ያለ ነው። በተጨማሪም የኤሌክትሪክ ኮርፖሬሽን የተጽዕኖ ግምገማ "የሚለማው ቢያንስ 5000 ሄክታር ነው" ቢልም የመንግስት ሰነዶች እንደሚያሳዩት በወረዳው 76,409 ሄክታር መሬት ለግብርና ኢንቨስትመንት ዝግጁ ተደርጓል።[45] የመንግስት ካርታዎች እንደሚያሳዩት ከተዘጋጀው መሬት ውስጥ ከ 18,000 ሄክታር በላይ እስከ 2003 ዓ.ም. አጋማሽ ድረስ ባለው ጊዜ ለአልሚዎች ተሰጥቷል።

መንግስት በቅርቡ ባወጣው መግለጫ እንደገለጸው የኤሌክትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን የተጽዕኖ ግምገማ "የሚካሄደው ሰፊ የመስኖ ስራ ተጽዕኖ እንደሚኖረው ጠቁሞ ነበር፣" ነገር ግን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ያወጣው መግለጫ እንደሚለው "መስኖ ዋና ምክንያት አይደለም።"[46] በርግጥ ግን መስኖ በነዋሪዎቹ የኑሮ መሠረት እና በአካባቢው አቀማመጥ ላይ መሠረታዊ ለውጥ የሚያስከትል ትልቅ ምክንያት ነው።

---

39 አንቶኒ ሚቸል፣ "Gilgel Gibe 111 dam Ethiopia: technical,engineering and economic feasibility study report", ኤፕሪል 15, 2009 ለአፍሪካ ልማት ባንክ የቀረበ፣ http://www.slideshare.net/anthony_mitchell/gilgel-gibe-111-hydroelectric-dam-ethiopia-technical-engineering-and-economic-feasibility-study-report (ኤፕሪል 2, 2012 የታየ)

40 የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን፣ "Gibe 111 ESIA Additional Study on Downstream Impact," ገጽ 165

41 "የዩኔስኮ የዓለም ቅርስ ኮሚቴ እና ግልገል ጊቤ ሦስት"፣ A Week in the Horn of Africa, የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ሴፕቴምበር 2, 2011

42 ሂዩማን ራይትስ ዎች፣ "Waiting Here for Death", አባሪ 11 ይመልከቱ

43 የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን፣ "Gibe 111 ESIA Additional Study on Downstream Impact," ገጽ 191

44 ዝኒ ከማሁ ገጽ 192

45 የኢትዮጵያ የፌደራል ግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር፣ "The Best Opportunity in SNNP South Omo" ኦክቶበር 2010

46 የኢትዮጵያ የፌደራል ግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር፣ "The Best Opportunity in SNNP South Omo"

ለማጠቃለል፣በጊቤ ሦስት ላይ የተሰራውን የአካባቢ እና ማህበራዊ ተጽዕኖ ግምገማ ስፋት፣ጥልቀት፣ጥራት ያለው እና ነፃ መሆን በመጠራጠር የሚተቹ በርካታ ወገኖች አሉ።ግምገማው የመስኖ ግብርና ልማት ሊካሄድ እንደሚችል ከመግለጽ ባለፈ ልማቱ የሚያስከትለውን የአካባቢ እና ማህበራዊ ተጽዕኖ አልዳሰሰም። ሂዩማን ራይትስ ዎች እስከሚያውቀው ድረስ የኢትዮጵያ ሕግ ይህ እንዲደረግ የሚጠይቅ ቢሆንም የስኳር ልማቱን የሚመለከት አንድም የአካባቢ እና የማህበራዊ ተጽእኖ ግምገማ አልተካሄደም።

## የገንዘብ ምንጭ

ኢትዮጵያ የአፍሪካ ልማት ባንክ፣የዓለም ባንክ እና የአውሮፓ ኢንቨስትመንት ባንክ የጊቤ ሦስት ግድብ ስራን በገንዘብ እንዲደግፉ አቅርባ የነበረውን ጥያቄ በሰኔ 2002 አንስታለች።[47] ለዚህ ደግሞ ምክንያቱ አልተገለጸም።[48] የአውሮፓ ኢንቨስትመንት ባንክ በኋላ ባወጣው መግለጫ "አማራጭ የገንዘብ ምንጭ ተገኝቷል።"[49] ብሏል። በግንቦት ወር 2002 ዓ.ም. ኢትዮጵያ እና ዶንግፋንግ ኤሌክትሪክ ኮርፖሬሽን የተባለው ግዙፍ የቻይና የሃይድሮ ፓወር ኩባንያ ለጊቤ ሦስት ልማት የሚውል የ450 ሚሊየን ዶላር ስምምነት ተፈራርመዋል።ይህም የግንባታውን ወጪ ለመሸፈን ከቻይና የኢንዱስትሪና የንግድ ባንክ[50] በብድር የሚገኘውን 420 ሚሊየን የአሜሪካ ዶላር የሚጨምር ነው።[51]

በቅርብ የወጡ የመገናኛ ብዙሃን ዘገባዎች እንደሚየሳዩት የሕንዱ ኤግዚም ባንክም ለብሔራዊ የስኳር ኢንዱስትሪ የሚውል 640 ሚሊየን የአሜሪካ ዶላር ብድር ለኢትዮጵያ መንግስት አቅርቧል። ይህ ብድር ከሚያስቀምጣቸው ቅድመ ሁኔታዎች ውስጥ አንዱ ለቁሳቁስ እና አገልግሎቶች ግዢ ከሚውለው ገንዘብ ቢያንስ 75 በመቶ የሚሆነው ከሕንድ ለሚገዙ ቁሳቁስ እና አገልግሎቶች መዋል አለበት የሚል ነው።[52] ሌሎች የመገናኛ ብዙሃን ዘገባዎች ደግሞ ሕንድ የቴክኒክ ድጋፍ ለማድረግ እና በሕንድና በኢትዮጵያ ስኳር ኮርፖሬሽን መካከል የቴክኖሎጂ ዕውቀት ሽግግር ለማድረግ ቁርጠኛ መሆኗን ዘግበዋል። የኢትዮጵያ ስኳር ኮርፖሬሽን የኩራዝ ስኳር ኢንዱስትሪን ጨምሮ በሃገሪቱ የሚካሄዱ የስኳር ልማቶችን ስራ የሚመራ የመንግስት ድርጅት ነው።[53]

## ትርጉም ያለውና ተገቢ ምክክር አለመደረጉ

በጊቤ ሦስት ግንባታ ከሚነኩ ወገኖች ጋር ምክክር ስለመደረጉ በልዩ ልዩ የአካባቢና የማህበራዊ ተጸዕኖ ግምገማ ሰነዶች[54] ላይ የተገለጸ ቢሆንም፣ በመስኖ በሚካሄደው የስኳር ልማት ከሚነኩ ማህበረሰቦች ጋር ግን ብዙም ትርጉም ያለው ምክክር አልተደረገም። በዚህ ፈንታ መንግስት በስኳር ልማቱ መደሰታቸውን ያልገለጹ ነዋሪዎችን ማስፈራራትና ማዋከብን መርጧል።

ለምሳሌ ያህል በታችኛው የኦሞ ክልል በሚገኙ የቦዲ ብሔረሰብ አባላት መኖሪያ አካባቢዎች በመጋቢት 2003 ዓ.ም ስብሰባ ተካሂዶ ነበር። የስብሰባው ተሳታፊዎች መንግስት ሰለስኳር ልማት ስላለው ዕቅድ ከተገለጸላቸው በኋላ በልማቱ የሚነኩትን ወገኖች ለማግኘት ሙከራ ተደርጎ ነበር። እነዚህ ስብሰባዎች በሃና ከተማ የተካሄዱ ሲሆን የፌደራል፣የክልልና የወረዳ ባለስልጣናት ተሳትፈውበታል።የፖሊስ እና የጦር ሃይል አባላት ቁጥርም ከፍተኛ ነበር።[55] በመጀመሪያ እነዚህን መሰል

---

47 የአፍሪካ ልማት ባንክ፣ "Federal Democratic Republic of Ethiopia Country Strategy Paper 2011-2015," ኤፕሪል 2011, http://www.afdb.org/fileadmin/uploads/afdb/Documents/Project-and-Operations/Ethiopia-2011-2015%20CSP%20ENG1.pdf (ኤፕሪል 2,2012 የታየ)

48 ዝኒ ከማሁ። የዓለም ባንክ ኢትዮጵያ ጥያቄዋን ስላነሳችበት ምክንያት በይፋ ያለው ነገር የለም

49 የአውሮፓ ኢንቨስትመንት ባንክ ጊቤ ሦስት የሚያስከትለውን ተጽዕኖ የሚፈትሹ በርካታ ጥናቶች አሰርቷል።የኢትዮጵያ መንግስት ያቀረበውን የፋይናንስ ጥያቄ ባንኩ መመልከቱን ያቆመው "የኢትዮጵያ መንግስት አማራጭ የገንዘብ ምንጭ በማግኘቱ እንጂ በጥናቱ በተገኘው ውጤት ምክንያት አይደለም" ብሏል።የአውሮፓ ኢንቨስትመንት ባንክ፣ "European Investment Bank's clarification of involvement in Gibe 3 project and Commitment to East African energy sector," ጁላይ 19, 2010

50 እስከ ማርች 2009 ድረስ የቻይና የኢንዱስትሪ እና ንግድ ባንክ በዓለም ትልቁ ባንክ ነበር

51 ኢንተርናሽናል ሪቨርስ፣ "China's Biggest Bank to Support Africa's Most Destructive Dam," ሜይ 13, 2010, http://www.internationalrivers.org/2010513/china%E2%80%99s-biggest-bank-support-africa%E2%80%99s-most-deatructive-dam (ጁላይ 6,2011 የታየ)

52 "Exim Bank To Adjust Sugar Industry Rehabilitation In Ethiopia," የሕንድ ኢምፖርት ኤክስፖርት ባንክ ጋዜጣዊ መግለጫ፣ ጁን 10,2012

53 "India offers expertise to modernize sugar industry in Ethiopia," ኤምኤስኤን ኒውስ ኢንዲያ፣ ኤፕሪል 12, 2011 እና "India offers Sugar Technology to Ethiopia," የሕንድ መንግስት ማስታወቅያ ቢሮ ጋዜጣዊ መግለጫ 71583, ኤፕሪል 11, 2011

54 ለምሳሌ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን "Environmental and Social Impact Assessment," ጃንዋሪ 2009 እና "Resettlement Action Plan: Dam and Reservoir Area," የሚለውን ይመልከቱ

55 ሂዩማን ራይትስ ዎች ከታችኛው ኦሞ ነዋሪ ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ ቁጥር 14 ሰኔ 2003

ስብሰባዎች ለሁሉም ክፍት የነበሩ ሲሆን በቅርብ ጊዜ የተካሄዱት ስብሰባዎች ግን በመንግስት የተመረጡ ሰዎች ብቻ የተሳተፉባቸው ነበሩ።[56] ተሳታፊዎቹም አበል ይከፈላቸው ነበር።[57] በተወሰኑት ስብሰባዎች ላይ የሙርሲ እና የክዌጉ ብሔረሰብ አባላት የሆኑ ሰዎች ተሳታፊዎች ነበሩ።[58]

በቅርብ በተደረጉት የምክክር ስብሰባዎችም ሕገወጥ እስር ለመፈጸምና ሃይል ለመጠቀም መዛት እንዲሁም ተወላጅ ማህበረሰቦቹን የማስገደድ ተግባር ቀጥሏል።[59] ለምሳሌ አንድ የአካባቢው ነዋሪ በቦዲ አካባቢ በጥቅምት ወር 2004 ተካሂዶ ስለነበረ ስብሰባ ሲናገሩ፣

> የመንግስት ባለስልጣናት የቦዲ ብሔረሰብና የአጎራባቹን የጭሪም ብሔረሰብ አባላት ከየመኖሪያ መንደሮቻቸው እንዲሰበሰቡ ካደረጉ በኋላ ስለሸንኮራ አገዳ ፕሮጀክትና ስለሰፈራ ትልቅ ስብሰባ ተደረገ። ከስብሰባው በኋላ የቦዲ እና የጭሪም ብሔረሰብ አባላቱን የሚሰፍሩበትን ስፍራ ሊያሳዩአቸው ወሰዷቸውና ከዚያን ጊዜ በኋላ በቋሚነት እዚያ እንደሚኖሩ ነገሯቸው። ቦታውን ካዩ በኋላ የቦዲ እና የጭሪም ብሔረሰቦች አባላቱ እዚያ መኖር እንደማይፈልጉ በመግለጽ ወደየቤታቸው ተመለሱ…
>
> ጥቅምት 26 ቀን 2004 መንግስት እንደገና የቦዲ ብሔረሰብ አባላትን ሃና በተባለ ቦታ ለስብሰባ ጠራ። ረጅም ጊዜ ከፈጀ ስብሰባ በኋላ የቦዲ ብሔረሰብ አባላቱ ፕሮጀክቱን እንደማይቀበሉ ገለጹ።መንግስትም ቦዲዎቹ እንዲስማሙ ማግባባቱ እየታከተው መጣ።ከዚያም የጸጥታ ሃይሎችን በመጥራት ቦዲዎቹ ስብሰባው ላይ እንዳሉ እንዲከበቡ አደረገ።ተከበውም ቢሆን ወጣቶቹ ፈርተው በፕሮጀክቱ ወደመስማማት አልመጡም።ከዚያም የጸጥታ ሃይሎቹ አራት ወጣቶችን ወስደው እስር ቤት አስገቧቸው።[60]

ሌሎቹ የምክክር ስብሰባዎች የተካሄዱት ደግሞ በ2003 ኢጋማሽ የመንግስት ባለስልጣናት የሙርሲዎች መኖሪያ የሆኑትን ሃይለውሃ እና ሞይዞ መንደሮች በጎበኙበት ወቅት ነው። በዚህ ጊዜ ሙርሲዎቹ ከዚያ በኋላ ወደ ኦሞ ወንዝ ዳርቻዎች እንዳይሄዱ የተነገራቸው ሲሆን መንግስት ያመጣቸውን ቅጾችም በጣታቸው እንዲፈርሙ ተደርገዋል።ብዙም የተማሩ ባለመሆናቸው ሙርሲዎቹ ቅጾቹ ምን እንደሚሉና ስምምነታቸውን የገለጹትም በምን ጉዳይ ላይ እንደነበር አላወቁም።[61]

ከከተሞች ወጣ ባሉ አካባቢዎች ስለስኳር ልማቱም ሆነ ስለአማራጭ የኑሮ መሠረት ከማህበረሰቡ ጋር ትርጉም ያለው ምክክር ስለመደረጉ ሂዩማን ራይትስ ዎች ያገኘው ማስረጃ የለም። የመንግስትን የልማት ዕቅዶች በሚመለከት በክልሉ ባጠቃላይ የመረጃ ክፍተት ያለ ሲሆን በፕሮጀክቶቹ ከሚነኩት የማህበረሰቡ ክፍሎች ጋር የተደረጉት ምክክሮችም በጣም አናሳ ናቸው። እነዚህ ማህበረሰቦች ስለሰፋፊ የኢንዱስትሪ ልማቶች የቀደመ ተሞክሮ የሌላቸው ከመሆኑም በላይ ስለሁኔታውም መንግስትን መጠየቅ ይፈራሉ።ምክክር አስፈላጊ ስለመሆኑ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የተወላጅ ሕዝቦች ድንጋጌ አንቀጽ 10፣ በኢትዮጵያ ሕገ መንግስት፣ በአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ አዋጅ ቁጥር 299/1994 እና በሌሎችም ሕጎች ተደንግጓል።[62]

## በኦሞ ሸለቆ በፕሮጀክቶቹ የሚነኩት ማህበረሰቦች

የኢትዮጵያ መንግስት መረጃ ባለመስጠቱ ምክንያት በመስኖ ግብርናው ምክንያት ለሚነኩት የታችኛው ኦሞ ተወላጅ ማህበረሰቦች አማራጭ የኑሮ መሠረቶችን ለማቅረብ የታቀደ ነገር ስለመኖር አለመኖሩ በግልጽ የሚታወቅ ነገር የለም። እነዚህ ማህበረሰቦች የኑሮ መሠረታቸውን ያጡት በውዴታ አይደለም።ተወላጅ ማህበረሰቦቹ ስለዚህ ጉዳይም ሆነ ዘላቂ ወደሆነ አማራጭ የኑሮ መሠረት ስለመሸጋገር አስተያያታቸው የሚሰማበት ሁኔታ የለም።

---

56 ሂዩማን ራይትስ ዎች ያደረገው የኢሜይል ግንኙነት፣ መጋቢት 2004

57 ሂዩማን ራይትስ ዎች ያደረገው የኢሜይል ግንኙነት፣ ታህሳስ 2004

58 ዝኒ ከማሁ

59 ሂዩማን ራይትስ ዎች ከታችኛው ኦሞ ነዋሪ ጋር ያደረገው የኢሜይል ግንኙነት፣ ጥቅምት 20፣ህዳር 8,2003 እና ጥር 30,2004

60 ሂዩማን ራይትስ ዎች ከታችኛው ኦሞ ነዋሪ ጋር ያደረገው የኢሜይል ግንኙነት፣ ጥቅምት 20

61 ሂዩማን ራይትስ ዎች ከታችኛው ኦሞ ነዋሪ ጋር ያደረገው የኢሜይል ግንኙነት፣ ህዳር 2003

62 የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት፣ አዋጅ ቁጥር 1/1987። የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ አዋጅ ቁጥር 299/1994፣ http://ethiopian-law.com/federal-laws/substantive-law-legislations/human-rights-and-governance/environmental-law/226-environmental-impact-assessment-proclamation-no-2992002.html?start=1

ለሂዩማን ራይትስ ዎች በጻፈው ደብዳቤ የኢትዮጵያ መንግስት እንደገለጸው በታችኛው ኦሞ የሚካሄደው ልማት የሥራ እድሎችንና የመሬት ኪራይን ይጋብዛል።[63] ይሁንና በከፊል ግብርናና ከብት ርቢ የተሰማሩት የአካባቢው ነዋሪዎች በትልልቅ የንግድ እርሻዎች ላይ መስራት ወይም መሬቶቻቸውን በኪራይ መስጠት ላይፈልጉ ስለመቻላቸው እንዲሁም ስላሏቸው አማራጮች የተሰጣቸው መረጃ አናሳ እንደሆነ ምንም የተገለጸ ነገር የለም።

ሂዩማን ራይትስ ዎች ያገኛቸው የመንግስት ካርታዎች እንደሚያሳዩት በመንግስት ሊካሄድ የታሰበው የእርሻ ልማት የሱሪ፣ የቦዲ፣ የሙርሲ፣የከዌጉ፣ የኛንጋቶም እና የካሮ ብሔረሰብ አባላት ከረጅም ጊዜ ጀምሮ ይዘዋቸው በኖሩት መሬቶች ላይ የሚሰራ ሲሆን የመስኖ መስመሮቹም የእነዚህን ማህበረሰቦች ይዞታዎች አቋርጠው የሚያልፉ ናቸው። ሆኖም ግን ለሂዩማን ራይትስ ዎች በጻፈው ደብዳቤ የኢትዮጵያ መንግስት "ፕሮጀክቱ የሚካሄድባቸው በደቡብ ኦሞ የተመረጡት አካባቢዎች ከሰው መኖሪያዎች የራቁ ናቸው።"[64] በማለት ይገልጻል።መንግስት ሲቀጥልም "ይህ ሙሉ በሙሉ ሰዎች የማይኖሩበት መሬት ነው። ሰዎች ለቀው እንዲወጡ ወይም እንዲፈናቀሉ የተደረገበት ሁኔታ የለም።" ብሏል።ይህ ደግሞ የታችኛውን ኦሞ ሸለቆ መኖሪያቸው አድርገው የሚኖሩትን 200,000 ዜጎች ከምንም

አለመቁጠር ነው።[65] የቦዲ ብሔረሰብ አባል የሆኑ አንዲት ሴት ሲናገሩ፣

> መንግስት እዚህ ማንም የለም ይላል። ወዴት ሄዱ?ይህንን መሬት በጣም ለረጅም ጊዜ ስንመነጥር ነበር። ትንሽ ልጅ እያለሁ ከማግባቴ በፊት እዚህ ነበርኩ።አባቴም ሴት አያቴም የሚያርሱት እዚህ ነበር። አሁንም እኔ እያረስኩት ነው።እንደማሽላው እዚሁ ነው ያደግነው።አያት ቅድመአያቶቼ እዚህ ነው የሞቱት፤የማሽላ ዘር እንደምናበቅለው እኔም ተዘርቼ የበቀልኩት እዚህ ነው።እዚሁ ነው ያለሁት፤ የምበላውም ከዚሁ መሬት ነው። መንግስት እዚህ ማንም የለም እያለ ለምን ደገኞቹን ኢትዮጵያውያን ይልካል?[66]


63 የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስትር ሽፈራው ተክለማርያም ለሂዩማን ራይትስ ዎች የጻፉት ደብዳቤ፣ታህሳስ 9,2004። የመሬት ኪራዩ በመሬት ባለይዞታ አርሶአደሮች እና በንግድ ኩባንያዎቹ መካከል የተወሰኑ ምርቶችን በአርሶ አደሮች መሬት ላይ ለማምረት የሚደረግ ውል ነው።

64 ዝኒ ከማሁ

65 አኑፓማ ቻንድራሴካራን፣ "Investment in Ethiopia farming face criticism from activists," ላይቭሚንት፣ ሴፕቴምበር 5, 2011

66 በቪዲዮ የተቀረጸ ምስክርነት ቁጥር 3፣ ሂዩማን ራይትስ ዎች ዘንድ የሚገኝ

## ካርታ 4፡ የስኳር ልማት እርሻው በሙርሲና በክዌጉ ብሔረሰቦች በተያዙ መሬቶች ላይ የሚሰራ መሆኑን የሚያሳይ




ይህ ካርታ የተሰራው ስለኳር ልማቱ መረጃ በያዙትና ሂዩማን ራይትስ ዎች ባገኛቸው የኢትዮጵያ መንግስት ካርታዎች ላይ በመመስረት ነው።የሙርሲና የክዌጉ ብሔረሰቦች ከረጅም ጊዜ ጀምሮ ሲጠቀሙበት የነበረውን የመሬት ይዞታ የሚያሳየው ደግሞ ከሙርሲ ኦንላይን (www.mursi.org) የተገኘ ነው።እዚህ ላይ ይህ መረጃ የቦዲ፣የኛንጋቶም፣የዳሰነች፣የካሮ እና የሱሪ ብሄረሰቦች የሚጠቀሙበትንና የስኳር ልማቱ ሊካሄድ የታቀደበትን ይዞታ የሚያሳይ እንዳልሆነ ማስታወስ ያስፈልጋል።ይህ ካርታ የሚያሳየው ከ52 (58 በመቶ) ከሚሆኑት የሙርሲና የክዌጉ ብሄረሰቦች መንደሮች ውስጥ 30 ው ለስኳር ልማት ተብሎ በተከለለው ወይም መንግስት ለግብርና ኢንቨስትመንት እየሸጠው ባለው መሬት ክልል ውስጥ እንደሚገኙ፣ሙርሲዎችና ክዌጉዎቹ እህል ለማብቀል ከሚጠቀሙባቸው 157 (73 በመቶ) መሬቶች ውስጥ 114ቱ መንግስት ለስኳር ልማት በከለለው ወይም ለግብርና ኢንቨስትመንት እየሸጠው በሚገኘው ክልል ውሰጥ እንደሚገኙ ነው።©2011 ማሞት ማፒንግ/ሂዩማን ራይትስ ዎች።

## በቱርካና ሐይቅ ላይ የሚኖረው ተጽዕኖ

የጊቤ ሦስት የሃይድሮ ኤሌክትሪክ ሃይል ልማት ካስነሳቸው ስጋቶች አንዱ በኬንያው የቱርካና ሐይቅ ላይ የሚያስከትለው ተጽዕኖ ነው። በቱርካና ሐይቅ አካባቢ የቱርካና፣ ሳምቡሩ፣ ዳሰነች፣ሬንዲሌ፣ ኤልሞሎ፣ እና ገብራ ማህበረሰቦችን ጨምሮ ኑሮአቸውን በከፊል ግብርናና ከብት ርቢ ላይ መስርተው የሚኖሩ በግምት 300,000 ሕዝቦች ይገኛሉ። የእነዚህ ሕዝቦች ኑሮ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በቱርካና ሐይቅ ላይ ጥገኛ ነው።እነዚህ በከፊል ግብርናና ከብት ርቢ የሚተዳደሩ ሕዝቦች ኑሮአቸውን ዓሳ በማጥመድና በቱርካና ሐይቅ እና በገባሮቹ ዳርቻዎች ላይ ያለውን መሬት በማረስ ይደጉማሉ።[67] የቱርካና ሐይቅ በዓለም ትልቁ የበረሃ ሐይቅ ሲሆን ከሐይቁ ውሃ ከ80 በመቶ በላይ የሚሆነው ለም አፈር ይዞ ከሚፈሰው የኦሞ ወንዝ የሚገኝ ነው።[68]

የአፍሪካ ልማት ባንክ በጊቤ ሦስት ላይ እ.ኤ.አ በሚያዝያ 2010 ያስጠናው ጥናት በግድቡ ግንባታና ስራ ላይ መዋል ምክንያት የሐይቁ የውሀ መጠን በከፍተኛ ሁኔታ ይቀንሳል፣አሁን ያለው ወቅት የጠበቀ የጎርፍ ፍሰት ይቀራል፣ከላይ በሚሰራው የውሃ ማጠራቀሚያ ምክንያት በንጥረ ነገሮች የበለጸገው አፈር ይቀራል፣የውሃው ጨዋማነት ይጨምራል፣የሐይቁ የኬሚካል ሚዛን ይዛባል እንዲሁም ደረጃቸው ወደፊት የሚታወቅ ሌሎች ተጽዕኖዎች ይከሰታሉ።[69] ይህም የመስኖ ግብርና ዕቅዱ የሚያስከትላቸው ተጨማሪ ተጽዕኖዎች ከግምት ውስጥ ሳይገቡ ነው።

የስኳር (ሸንኮራ አገዳ) ሰብል ከፍተኛ መጠን ያለው ውሃን የሚፈልግ እና በደንብ እንዲያድግ ብዙ ዓይነት ኬሚካሎች የሚያስፈልጉት ነው። 245,000 ሄክታር በመስኖ የሚለማ የስኳር ልማት በኬንያው የቱርካና ሐይቅ ውሃ መጠንና ጥራት ላይ የሚያስከትለውን ተጽዕኖ የሚፈትሽ ጥናት አለመኖሩ ከፍተኛ ስጋትን የሚፈጥር ጉዳይ ነው። የመስኖ ግብርናው፣ የጊቤ ሦስት ግድብ እና ሌሎች ይፋ የተደረጉት የልማት ሥራዎች በቱርካና ሐይቅ ላይ የሚኖራቸውን ጥምር ተጽዕኖ የሚዳስስ ምንም ጥናት የለም።

የመስኖ ግብርናው እና የጊቤ ሦስት ግድብ ጥምር ተጽዕኖ ወደቱርካና ሐይቅ የሚፈሰውን የውሃ መጠን በመቀነስ፣ ለተፈጥሮ ሃብት የሚደረግ ፉክክርን በመጨመርና የግጭቶችን የመከሰት እድል በመጨመር በሐይቁ ሥነ ምህዳር እና ይህንን ሥነ ምህዳር ተማምነው ኑሮአቸውን በመሰረቱ ሕዝቦች ህልውና ላይ ከፍተኛ እና ሊቀለበስ የማይችል ጉዳት ያደርሳል የሚል ስጋት አለ። በመስኖ የሚካሄደው ግብርና ከተፋሰሱ ግርጌ በቱርካና ሐይቅ ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ተጽዕኖ ለመረዳት የሚያስችል አስፈላጊውን ጥናትም ሆነ ግምገማ ኢትዮጵያ አላካሄደችም።ሊካሄድ የታቀደውን የመስኖ ግብርና ልማት ስፋት የሚመለከት መረጃ ያለ ቢሆንም፣ በየካቲት ወር 2004 ዓ.ም የወጣው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአካባቢ ፕሮግራም ሪፖርት እንኳን የግብርና ልማቱ በቱርካና ሐይቅ ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ተጨማሪ ተጽዕኖ አልዳሰሰም።[70]

በሰኔ ወር 2003 ዓ.ም የዩኔስኮ የዓለም ቅርስ ኮሚቴ የዓለም ቅርስ በሆነው የቱርካና ሐይቅ ላይ ሊደርስ የሚችለውን ተጽዕኖ በመገንዘብ ኢትዮጵያ የጊቤ ሦስትን ግንባታ እንድታቆም ሀሳብ አቅርቧል። የዓለምን ባሕላዊና የተፈጥሮ ቅርሶች ጥበቃ በሚመለከተው ስምምነት አንቀጽ 6 መሰረት ኢትዮጵያ "በሌላ የስምምነቱ ፈራሚ ሃገር የግዛት ክልል ውስጥ በሚገኝ ባሕላዊ ወይም የተፈጥሮ ቅርስ ላይ ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል እርምጃ እያወቀች ከመውሰድ መቆጠብ" አለባት።[71] ኮሚቴው በተጨማሪም "የጊቤ አራት እና የጊቤ አምስት ግድቦች ግንባታ እና በመስኖ የሚካሄዱት ሰፋፊ እርሻዎች በቱርካና ሐይቅ ሁለንተናዊ እሴት ላይ ሊያስከትሉ ስለሚችሉት ጥምር ተጽዕኖ ያለውን ስጋት የገለጸ ሲሆን፣ኢትዮጵያ በኦሞ ወንዝ ላይ ሊሰሩ የታቀዱት ሁሉም ግድቦችና ተያይዘው የሚሰሩት የመስኖ ግብርና ስራዎች ሊያስከትሉ የሚችሉትን የተጽዕኖ ግምገማ እንድታቀርብ" ጠይቋል። ከዚህም ሌላ "ኢትዮጵያ በኦሞ ወንዝ ላይ ሊሰሩ የታቀዱ ሌሎች የሃይድሮኤሌክትሪክ ልማቶችና ተያይዘው የሚሰሩ ሰፋፊ የመስኖ ስራዎችን የሚመለከት ዝርዝር መረጃ እንድታቀርብ"[72] ኮሚቴው ተይቋል።

---

67 ኢንተርናሽናል ላይቭሰቶክ ሪሰርች ኢንስቲትዩት፣ "Livelihood diversification opportunities for pastoralists in Turkana, Kenya," 2008

68 አር. ሪኬትስ እና ቲ. ጆንሰን፣ "Climate Change in the Turkana basin as deduced from a 4000 year long 8018 record," Earth and Planetary Science Letters, vol. 142 (1996) ገፅ 7-17

69 የአፍሪካ ልማት ባንክ ግሩፕ "Hydrological impacts of Ethiopia's Omo basin on Kenya's Lake Turkana Water Level and Fisheries of Gibe 111 on Lake Turkana,"
http://www.friendsoflaketurkana.org/images/docs/report_nov_2010_s_avery_turkana_small_file.pdf (ጁን 2011 የታየ)

70 የተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ፕሮግራም፣ "Ethiopia's Gibe 111 Dam: Its Potential Impact on Lake Turkana Water Levels," የተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ፕሮግራም የቅድመ ማስጠንቀቂያና ግምገማ ክፍል፣ ፌብሯሪ 2012

71 የተባበሩት መንግስታት የትምህርት የሳይንስ እና የባሕል ድርጅት(ዩኔስኮ)፣ የዓለም ባሕላዊና ተፈጥሮአዊ ቅርሶችን ለመጠበቅ የተደረገ ስምምነት፣ ኖቬምበር 16,1972፣ http://www.unhcr.org/refworld/docid/4042287a4.html , (ጁላይ 25,2011 የታየ) አንቀጽ 6። ኢትዮጵያ ስምምነቱን ጁላይ 6,1977 አጽድቃለች።

72 የዩኔስኮ የዓለም ቅርስ ኮሚቴ፣ "Decisions adopted by the World Heritage Committee at its 35th session," ጁላይ 7,2011፣ http://unesdoc.unesco.org/images/0018/001899/189993e.pdf (ጁላይ 25,2011 የታየ)

በምላሹም የኢጥዮጵያ መንግስት የጊቤ ሦስትን ፕሮጀክት የሚደግፍና  በዩኔስኮ ለተነሱት ስጋቶች ምላሽ የሚሰጥ ነጻ የአካባቢና የማህበራዊ ተጽዕኖ ግምገማ  ማካሄዱን ገልጾ “የዩኔስኮ የዓለም ቅርስ የሆነው የታችኛው የኦሞ ሸለቆ በጣም ወደታች ወርዶ የሚገኝ በመሆኑ በግድቡ ግንባታ የሚነካ አይሆንም”[73] ብሏል። ከላይ እንደተብራራው በጊቤ ሦስት የተጽዕኖ ግምገማ ላይ የሚሰነዘሩ በርካታ ትችቶች ያሉ ሲሆን፣ የስኳር ልማቱ በቱርካና ሐይቅ ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ተጽዕኖ የሚዳስስ ምንም ግምገማ አልተካሄደም።

ኬንያ ለዩኔስኮ በሰጠችው ይፋዊ ምላሽ ተገቢው የተጽዕኖ ግምገማ አለመካሄዱን ያመለከተች ሲሆን “እስካሁን ድረስ የጊቤ ሦስት ፕሮጀክት የዓለም ቅርስ በሆነው የ[ቱርካና ሐይቅ] ላይ ሊያደርስ የሚችለውን ጉዳት ለማቃለል የሚያስችሉ ርምጃዎች ስለመኖራቸው የስምምነቱ ፈራሚ በሆነችው ኢትዮጵያ የቀረበ በቂ ሳይንሳዊ ማረጋገጫ የለም።”[74] በማለት ገልጻለች።

73 “UNESCO World Heritage Committee and Gilgel Gibe 111,” A Week in the Horn, የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ሴፕቴምበር 2,2011

74 የኬንያ መንግስት፣ “State Party Report in Response to the World Heritage Committee Decision WHC 35 COM 7B.3,” ፌብሯሪ 1,2012

# III. በታችኛው የኦሞ ሸለቆ ከሚካሄደው ኢንዱስትሪያዊ ልማት ጋር በተያያዘ የተፈጸሙ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች

በታችኛው ኦሞ በሚካሄደው የንግድ ግብርና ልማት ላይ የአካባቢው ነዋሪዎች የሚያነሱት ተቃውሞ መንግስት ያለውን ሰፊ የልማት አጀንዳ ለመተግበር በሚሞክርበት ጊዜ በአካባቢው ውጥረትና የሰብአዊ መብቶች ጥሰት እያስከተለ ነው።

ከላይ እንደተገለጸው በዛሬይቱ ኢትዮጵያ በሰብአዊ መብቶች ጉዳይ ላይ ምንም ዓይነት ጥናት ማካሄድ እጅግ አስቸጋሪ ነው። በግንቦትና ሰኔ 2003 ዓ.ም በኢትዮጵያ ምርመራ ባካሄደበት ወቅት ሂዩማን ራይትስ ዎች በታችኛው ኦሞ ሸለቆ ከሚኖሩ ስድስት ብሔረሰቦች የተውጣጡ እማኞችና የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች የተፈጸሙባቸው ሰዎችን አግኝቶ አነጋግሮአል። በዚህ ወቅት በተሰራው የምርመራ ሥራ የተደረሰባቸው ግኝቶች በግንቦት ወር 2004 ከአካባቢው ከተሰባሰቡ እና ከኢትዮጵያ ውጭ ከተሰበሰቡ ተጨማሪ መረጃዎች ጋር እንዲገናዘቡ ተደርደዋል።

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች የኢትዮጵያ መንግስት የልማት እቅዶቹን ለማስፈጸም እየፈጸማቸው ያሉትን አስገዳጅ እና ከሕግ ያፈነገጡ እጅግ ሰሜትን የሚያደፈርሱ ድርጊቶች በአጭሩ የሚያሳዩ ናቸው። ይህ ሪፖርት በታችኛው የኦሞ ሸለቆ ከሚካሄደው የልማት ሥራ ጋር ተያይዞ የሚነሱ ዋና ዋና የሰብአዊ መብቶች ስጋቶችን እንደማሳያ የሚዘረዝር እንጂ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታውን ስዕል ሙሉ በሙሉ የሚያሳይ አይደለም። ሂዩማን ራይትስ ዎች በዚህ ሪፖርት የተዘረዘሩትን በደሎች ስፋት እና ደረጃ የሚያሳይ ተአማኒነት ያለው ተጨማሪ ምርመራ መካሄዱን በጽኑ የሚደግፍ ሲሆን የኢትዮጵያ መንግስትም ነጻ መርማሪዎች በአካባቢው ያለ ገደብ እንዲንቀሳቀሱ ድጋፍ እንዲያደርግ ጥሪውን ያቀርባል።

የስኳር ልማቱ መካሄድ በጀመረበት የታችኛው ኦሞ ሸለቆ ሰሜናዊ ክፍል የሚኖሩት የሙርሲ እና የቦዲ ብሔረሰብ አባላት ለሂዩማን ራይትስ ዎች በ2004 እንደገለጹት ከሚያዝያ ወር 2003 መጀመሪያ ጀምሮ የፌደራል መከላከያና የፖሊስ አባላት ወደ አካባቢው በመሄድ በመንደሮቹ ነዋሪዎች ላይ እስር፣ድብደባ እና ማስፈራራት ፈጽመዋል። ነዋሪዎቹ እንዳሉት ከሂዩማን ራይትስ ዎች ጋር ከመገናኘታቸው ከ2003 አስቀድሞ ከወራት በፊት ወታደሮቹና የፖሊስ አባላት ከላይ የተጠቀሱትን በደሎች ይፈጽሙ ነበር። ሂዩማን ራይትስ ዎች በጎበኛቸው የቦዲ እና የሙርሲ መንደሮች ያለው ሁኔታም ተመሳሳይ ነው።

አንድ የሙርሲ ብሔረሰብ አባል በመንደራቸው የሆነውን ሲናገሩ፡

> ዝናብ እስካልዘነበ እና መንገዱ እስካልተበላሸ ድረስ በየቀኑ ይመጣሉ። ሲመጡም በአራትና በአምስት መኪኖች ሆነው ከ 20 እስከ 60 የሚደርሱ ወታደሮች ሆነው ነው። 'ወደ ዙሪያ አካባቢው እያመለከቱ ይህንን ቦታ ለስኳር ልማት እንፈልገዋለን ስለዚህ እናንተ እዚያ መሆን አይኖርባችሁም። እዚሁ ብቻ ቆዩ። ስለስኳር ምን ታስባላችሁ?' ይሉናል። እኛም 'አናውቅም' ወይም 'አንፈልገውም' እንላለን። ይህ ግን ትክክለኛው መልስ አይደለም። ከዚያም ይመቱናል ወይም እስር ቤት ይወስዱናል።[75]

ሌላ የሙርሲ ተወላጅ በሌላ መንደር የተፈጸመውን ሲገልጹ፡

> በዘጠኝ መኪኖች የተጫኑ ወታደሮች መጡ። ወደመንደሩ የተለያዩ አካባቢዎች እየሄዱ ነዋሪዎቹን ወደ ጫካው እየተከተሉ መቷቸው። 'ስለዚህ ሸንኮራ አገዳ ንገረኝ' ይሉ ነበር። መልካም ነገር ካልተናገርን እዚያው መንደሩ ውስጥ መቆየት እንዳለብን ይነግሩናል።ይመቱናል፣ይደበድቡናል።ዱላ፣ ጠመንጃ እና የሚያደነዝዝ መሳሪያ አላቸው።በየቀኑ ይመጣሉ።ከዚህ በፊት ችግር ሲኖር የሚመጡት ተራ ፖሊሶች ነበሩ።እነሱ አይማቱም ነበር።ወታደሮቹ ግን የተለዩ ናቸው፤በጣም መጥፎ ናቸው።የሆነውን ሁሉ በዐይኔ አይቻለሁ።[76]

---

75 ሂዩማን ራይትስ ዎች ከታችኛው ኦሞ ነዋሪ ጋር ያደረገው ቃለ ምልልስ ቁጥር 8፣ ግንቦት 26,2003

76 ቁጥር 15፣ ግንቦት 27,2003

ሂዩማን ራይትስ ዎች አካባቢውን ከጎበኘ ከሰኔ ወር 2003 በኋላ በደሎቹና ማስፈራራቱ እየተባባሰ እንደመጣ የአካባቢው ነዋሪዎች እና የታችኛው ኦሞን የጎበኙ ሰዎች ይናገራሉ።[77] ነዋሪዎች እንዳሉት የመንግስት ሰዎች በሕዝባዊ ስብሰባዎች ላይ የሚናገሯቸው እና የጦር ሃይል አባላቱ በየጊዜው ሲመጡ የሚናገሯቸው ነገሮች መንግስት ነዋሪዎችን ከስኳር ልማቱ አካባቢ ለማንሳት ሀሳብ እንዳለው የሚጠቁሙ ናቸው።[78]

ለስኳር ልማቱ የሚሆን መሬት ምንጣሮ እና የመሠረተ ልማቶች ግንባታ ከሰሜን አካባቢዎች ጀምሮ ወደ ደቡብ እየተካሄደ ነው።ሪፖርት ከተደረጉት ጥሰቶች ውስጥ አብዛኞቹ የተፈጸሙት በቦዲ፣ በሙርሲ እና በክዌጉ አካባቢዎች ነው። በተከሎች የተሸፈኑ መሬቶችን መመንጠሩና የመንገዶችና የካምፖች ግንባታ እንደቀጠለ ነው። ሂዩማን ራይትስ ዎች ከነዋሪዎች ጋር ባደረጋቸው ቃለ ምልልሶች እንደተረዳው፣ የመንግስት እና የጦር ሃይል ባለስልጣናት ነዋሪዎቹ በኦሞ ወንዝ ያላቸው ተጠቃሚነት እንደሚቀር፣ በቤተሰብ ሁለት ወይም ሦስት ከብቶች ብቻ በማስቀረት የከብቶቻቸውን ቁጥር መቀነስ እንደሚኖርባቸውና በአንድ አካባቢ መስፈር እንደሚኖርባቸው ነግረዋቸዋል።[79]

የቦዲ ብሔረሰብ አባል የሆኑ አንዲት ሴት ሁኔታው ያስከተለውን ብስጭት እና የሰፈራ ዕቅዱን አስመልክቶ ግልጽ መረጃ አለመኖሩን እንደሚከተለው ያጠቃልሉታል፡

> እኔ በኦሞ እና በከብቶች ተማማኜ የምኖር ሰው ነኝ። በሰፈራ ጣቢያዎች ከብቶቹ እንዲኖሩ ይፈቀዳል ወይስ የት ነው የሚሆኑት? የሰፈራ ጣቢያውስ የት ነው? ስለሰፈራ ጣቢያው የሰማችሁት ነገር ካለ ንገሩን፣ የት ነው አሉ? ተነሱ፣ተነሱ፣ ተነሱ ይሉናል። እኛ ቦዲዎች የትም አንሄድም። አንገታችንን እዚሁ ይቁረጡት እንጂ እዚሁ ነው የምንቆየው። እዚሁ እንኖራለን፤ ከብቶቻችንም የአያቶቻችን ከብቶች የጋጡትን ሣር ይግጣሉ።[80]

## ሕገ ወጥ እስር

በተለያዩ መንደሮች የሚኖሩ አስር እማኞች እንደገለጹት ወደ መንደሮቹ የመጡ የፌደራል መንግስት ጦር ሃይል አባላት የቦዲ እና የሙርሲ ብሄረሰብ አባላት የሆኑ ሰዎችን በዘፈቀደ አስረዋል። እማኞቹ እንደገለጹት እስሩን የሚፈጽሙት ወታደሮች ለእስሩ የተለያዩ ምክንያቶችን ያቀርባሉ፤ ይሁንና የስኳር ልማቱን መቃወም በተደጋጋሚ የሚጠቅሱት ተጨማሪ ምክንያት ነው።[81]

ታስረው ከሚቆዩት ብዙዎቹ በጣም ፈጣን በሆነ የፍርድ ሂደት ጥፋተኛ ይባላሉ። አንዳንድ ውሳኔዎች በታሰሩ በ24 ሰዓት ውስጥ ይሰጡ ነበር።[82] አንዳንድ ነዋሪዎች እንደሚሉት አንዳንድ እስረኞች በእስር ላይ እያሉ ከባድ ድብደባ ሰለሚፈጸምባቸው ቤተሰቦቻቸው እንዳይጠይቋቸው ተከልክለው ነበር።[83] የተካሰሾች ዘመዶች የሆኑ ሰዎች ለሂዩማን ራይትስ ዎች እንደነገሩት ተከሳሾቹ ጠበቃ አልነበራቸውም፤ የጋራ መግባቢያ ቋንቋ ባለመኖሩም ለተከሰሱበት ጉዳይ መከላከያ መልስ ለማቅረብ ይቅርና በፍርድ ሂደቱ ወቅት ብዙዎች መግባባት የሚችሉበት ሁኔታ አልነበረም።[84] ይሁንና የእነዚህን ክሶች እውነተኝነት ለማረጋገጥ ሂዩማን ራይትስ ዎች በአካባቢው ያሉ እስር ቤቶችን መጎብኘት አልቻለም። ባለስልጣናቱ ፈቃድ ሰጥተው የነበረ ቢሆንም፣በአካባቢው አቀማመጥ አስቸጋሪነት እና በነበረው ከባድ ዝናብ ምክንያት ጉብኝቱን ማድረግ አልተቻለም። ሆኖም ግን የኢትዮጵያ ባለስልጣናት የአካባቢው ነዋሪዎች ያነሷቸውን ክሶች ማጣራት አለባቸው።

በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል እና በፌደራል መንግስቱ የሚገኙ ሁለት ምንጮች ተመሳሳይ ሕገ ወጥ እስሮች በኦሞ ወንዝ ምዕራባዊ ዳርቻ በሚገኘው የሱሪ አካባቢም ይፈጸም እንደነበር ለሂዩማን ራይትስ ዎች ገልጸዋል።[85]

---

77 ሂዩማን ራይትስ ዎች ከታችኛው ኦሞ ነዋሪ ጋር ያደረገው ቃለ ምልልስ እና የኢሜይል ግንኙነት፣ ሐምሌ እና ነሐሴ 2003

78 ሂዩማን ራይትስ ዎች ከታችኛው ኦሞ ነዋሪ ጋር ያደረገው ቃለ ምልልስ፣ ግንቦት-ሰኔ 2003

79 ሂዩማን ራይትስ ዎች ከታችኛው ኦሞ ነዋሪ ጋር ያደረገው ቃለ ምልልስ፣ ግንቦት-ሰኔ 2003

80 በቪዲዮ የተቀረጸ ምስክርነት ቁጥር 4፣ ሂዩማን ራይትስ ዎች ዘንድ የሚገኝ

81 ሂዩማን ራይትስ ዎች ከታችኛው ኦሞ ነዋሪ ጋር ያደረገው ቃለ ምልልስ፣ሰኔ 2003

82 ሂዩማን ራይትስ ዎች ከታችኛው ኦሞ ነዋሪ ጋር ያደረገው የኢሜይል ግንኙነት፣ ሰኔ 2003

83 ሂዩማን ራይትስ ዎች ከታችኛው ኦሞ ነዋሪ ጋር ያደረገው ቃለ ምልልስ እና የኢሜይል ግንኙነት፣ ግንቦት-ሰኔ 2003

84 ሂዩማን ራይትስ ዎች ከታችኛው ኦሞ ነዋሪ ጋር ያደረገው ቃለ ምልልስ ቁጥር 14፣ ግንቦት 26, 2003

85 ሂዩማን ራይትስ ዎች ከታችኛው ኦሞ ነዋሪ ጋር ያደረገው ቃለ ምልልስ ቁጥር 15 እና 16፣ ግንቦት 2003

ወደአካባቢው ተጉዞ የነበረ አንድ የሙርሲ ብሔረሰብ ሰው ይህንን አባባል የሚያጠናክር መረጃ ሰጥቷል።[86] ሂዩማን ራትስ ዎች አካባቢውን ከጎበኘ በኋላ በቦዲ፣ በሱሪ እና በሙርሲ አካባቢዎች ሕገ ወጥ እስሮች መፈጸም መቀጠላቸውን የታመኑ ምንጮች ገልጸዋል።[87]

በጥቅምት ወር 2004 አካባቢውን ለጎበኘ አንድ ሰው አንድ የሙርሲ ብሔረሰብ አባል እንደነገሩት፡

> አንዳንዶቹ እስረኞች በጂንካ፣ አንዳንዶቹም በባስኬቶ ሌሎቹም በወላይታ እስር ቤቶች ታስረዋል። አንዳንዶቹ ምንም ሳያጠፉ ነው የታሰሩት። ብዙ ሰዎች ታስረዋል... ባለፉት ጊዜያት መንግስት እንደዚህ አያስረንም ነበር። አንድ ሰው ሰው ገድሎ እንደሆነ ሙርሲዎች በራሳቸው ባሕላዊ መንገድ ጉዳዩን ይፈቱታል... አሁን ግን በስኳር ልማቱ ምክንያት ልማቱን የማይፈልጉ ሰዎች እየታሰሩ ነው።[88]

## ድብደባ እና ማንገላታት

በቦዲ እና በሙርሲ አካባቢዎች የሚገኙ መንደሮች ነዋሪዎች ለሂዩማን ራይትስ ዎች እንደነገሩት ወታደሮች ወደ መንደሮቹ በመጡ ቁጥር ለማስፈራራት በሚመስል ሁኔታ ነዋሪዎችን ይደበድባሉ።

በመንደሩ የሚኖሩ አንድ የሙርሲ ተወላጅ ሲናገሩ፡

> ይመጡና "ስኳር አትፈልጉም?" ይላሉ፤ ከዚያም በጠመንጃ ሰደፍ ይመቱናል። "ይህ የመንግስት መሬት ነው። የእናንተ አይደለም።" ይላሉ።[89]

ሌላ የሙርሲ ተወላጅ ለሂዩማን ራይትስ ዎች እንደገለጹት የመንደሮቹን ነዋሪዎች ለማጥቃት ወታደሮቹ ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ሃይል ያላቸው ማደንዘዣ ሽጉጦች ይጠቀማሉ፡

> ማደንዘዣውን ሁሌም ይጠቀማሉ፤አንድ ጊዜ ወታደሮቹ አንዱን ሰው "ስለ ስኳር ምን ታስባለህ?" ብለው ጠየቁት። "አላውቅም.... አላውቅም፤" ብሎ መለሰ። "አታውቅም?" ብለው አደነዘዙት።[90]

ነዋሪዎቹ ወታደሮቹን ምን ያህል እንደሚፈሩ የሚያሳይ አንድ ምሳሌ ለመጥቀስ፤ የሂዩማን ራይትስ ዎች መኪና ወደ አንድ የታችኛው ኦሞ መንደር ሲቃረብ ነዋሪዎቹ ወደ ጫካው ሸሽተው ሄዱ። በኋላ የሸሹበትን ምክንያት ለሂዩማን ራይትስ ዎች መርማሪ ሲናገሩ መኪናው እንደተለመደው ወታደሮቹን ጭኖ የመጣ መስሎአቸው ነው። ሂዩማን ራይትስ ዎች የታችኛውን ኦሞ አካባቢ በ2003 ከጎበኘበት ጊዜ በኋላ የጦር ሃይሉ የቦዲ እና የሙርሲ ተወላጆችን መደብደብና ማጥቃት መቀጠሉን የሚያሳዩ ተአማኒነት ያላቸው የዐይን እማኝ ዘገባዎች ወጥተዋል።[91]

## በፍራቻ እና በማሸበር ማስተዳደር

> መንግስት እንደ ቡልዶዘር ነው። የልማት ፕሮጀክቶቹን የሚቃወም ማንኛውም ሰው ከሚንቀሳቀስ ቡልዶዘር ፊት እንደቆመ ሰው ይጨፈለቃል።
> --አንድ የታችኛው ኦሞ ነዋሪ የደቡብ ክልል ዋና ከተማ ከሆነችው አዋሳ የመጡ የፖሊስ አዛዥ በሰኔ ወር 2003 ሃና ከተማ ተካሂዶ በነበረው ሕዝባዊ ስብሰባ ላይ ከተናገሩት ውስጥ የጠቀሰው።[92]

---

86 ሂዩማን ራይትስ ዎች ከታችኛው ኦሞ ነዋሪ ጋር ያደረገው የኢሜይል ግንኙነት ፣ሐምሌ 9, 2003

87 ሂዩማን ራይትስ ዎች ከታችኛው ኦሞ ነዋሪ ጋር ያደረገው የኢሜይል ግንኙነት፣ ሐምሌ እና ነሃሴ 2003

88 በቪዲዮ የተቀረጸ ምስክርነት ቁጥር 16፣ ታህሳስ 2004፣ ሂዩማን ራይትስ ዎች ዘንድ የሚገኝ

89 ሂዩማን ራይትስ ዎች ከታችኛው ኦሞ ነዋሪ ጋር ያደረገው ቃለ ምልልስ ቁጥር 4፣ ግንቦት 26,2003

90 ሂዩማን ራይትስ ዎች ከታችኛው ኦሞ ነዋሪ ጋር ያደረገው ቃለ ምልልስ ቁጥር 15፣ ግንቦት 27,2003

91 ሂዩማን ራይትስ ዎች ከታችኛው ኦሞ ነዋሪ ጋር ያደረገው ቃለ ምልልስ እና የኢሜይል ግንኙነት፣ታህሳስ እና ጥር 2004

92 በስብሰባው ላይ የተገኙ የማህበረሰቡ አባል ለሂዩማን ራይትስ ዎች እንደነገሩት፣ግንቦት 25,2003

በታችኛው ኦሞ የሚካሄደውን ልማት በመቃወም የሚነሳ ተቃውሞ ለማፈን መንግስት፣ የፖሊስና የጦር ሃይሉ ባለስልጣናት ማስፈራራትን፣ ዛቻን እና ሕገ ወጥ እስርን እየተጠቀሙ ናቸው።ይህ ዘዴ ተቃውሞን ለመግታት መንግስት በስፋት የሚጠቀምበት ነው።[93]

ብዙዎቹ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች የሚፈጸሙት በአደባባይ እና በግልጽ ነው። ይህም ለስኳር ልማቱ ዕቅድ ሙሉ ድጋፉን የማይሰጡ በሙሉ የሚጠብቃቸው ተመሳሳይ ዕጣ እንደሆነ ለማሳየት ነው። ነዋሪዎች እተፈጸመባቸው ያለው የሃይል ጥቃት በጣም ያስፈራቸዋል። አንድ የቦዲ ብሄረሰብ ተወላጅ እንደገለጹት፡

> በስኳር [ልማት] ላይ ከመንግስት ጋር የማይስማሙ ሰዎች አሉ፤ ነገር ግን መንግስት በሃይል አስገድዶ በሌላ ቦታ ሊያሰፍራቸው እንደሚችል በመፍራት ብዙም አይናገሩም። እዚህ መንግስትን በጣም ነው የምንፈራው። ስጋትህን ከገለጽህ፣ እስር ቤት መግባትህ ነው።[94]

በመንግስት ውስጥም ቢሆን የልማት እቅዱን አስመልክቶ የሚነሱ የተለዩ ሃሳቦች በትዕግስት አይታለፉም። አንድ የፌደራል መንግስት ሠራተኛ ሲናገር፡

> በሕገ መንግስቱ መሠረት የአካባቢውን ነዋሪዎች ማማከር ያስፈልጋል የሚል ሃሰብ ሰነዘርኩ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የታችኛውን ኦሞ በሚመለከት በሚደረግ ስብሰባም ሆነ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት እንዳልሳተፍ ተደረገ። በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የሚሰጠው በጥቂት ሠዎች ነው፤ ስለዚህ አንድ ዕቅድ እስከሚተገበርበት ጊዜ ድረስ ስለ ዕቅዱ ማንም ሰው አያውቅም።[95]

በመፈጸም ላይ ስላሉት የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች እና የንግድ ግብርናው በዘላቂ የወደፊት ሕይወታቸውና የኑሮ መሰረታቸው ላይ ስለሚያስከትለው ተጽእኖ ያላቸውን ጥልቅ ስጋት ነዋሪዎቹ ለሂዩማን ራይትስ ዎች ገልጸዋል። ስለ ሰፈራ፣ የከብቶችን ቁጥር ስለመቀነስ እና በኦሞ ወንዝ ላይ ያላቸውን ተጠቃሚነት ስለማጣት ጭምጭምታዎች ሰምተዋል፤ነገር ግን የተረገው እዚህ ግባ የማይባል ምክክር ግን ነዋሪዎቹ ማብራሪያ ከየት እንደሚያገኙና በጉዳዩ ላይ የሚኖራቸውን የተለየ ሃሳብ የት እንደሚገልጹ እንዳያውቁ ስላደረጋቸው ከፍተኛ መደናገር ተፈጥሮአል።[96]

የስኳር ልማቱን በሚመለከት የተሰራ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ እንኳን ለሕዝብ እይታ እና ምክክር መቅረቡን ቀርቶ ግምገማው ተሰርቶ በኢትዮጵያ የአካባቢ ጥበቃ ኤጀንሲ መጽደቁን የሚያሳይ አንድም ማስረጃ ሂዩማን ራይትስ ዎች ማግኘት አልቻለም። ሕጉ ግን ይህ መደረግ እንዳለበት ይገልጻል።[97]የኢትዮጵያ መንግስት ለሂዩማን ራይትስ ዎች በጻፈው ደብዳቤ ለማመላከት እንደሞከረው ለግድቡ የተሰራው አሁን ያለው የተጽዕኖ ግምገማ የስኳር ልማቱንም ያካትታል።[98] ከላይ እንደታየው ይህ ግምገማ ግን የስኳር ልማቱን ያካተተ አይደለም።

በአካባቢው ከሚንቀሳቀሱ የሙብት ተሚጋቾች የወጡ የቅርብ ጊዜ ዘገባዎች እንደሚያመለክቱት የቦዲ ብሔረሰብ አባላት የሆኑ አምስት ሰዎች በስኳር ልማቱ መኪኖች ተጨፍልቀው የሞቱበትን ጨምሮ በርካታ አደጋዎች ደርሰዋል።[99] እነዚህ አደጋዎች ድንገተኛ አልነበሩም ለማለት የሚያስችል ማስረጃ ባይኖርም በቦዲ ብሄረሰብ አባላትና ከመሃል ሃገር በመጡት

---

[93] የሂዩማን ራይትስ ዎችን "One Hundred Ways of Putting Pressure": Violations of Freedom of Expression and Association in Ethiopia, ማርች 2010 http://www.hrw.org/reports/2010/03/24/one-hundred-ways-puttung-pressure ይመልከቱ

[94] የሂዩማን ራይትስ ዎች ቃለ ምልልስ ቁጥር 12፤ ታችኛው ኦሞ፣ ግንቦት 24,2003

[95] ሂዩማን ራይትስ ዎች ከፌደራለ የመንግስት መስሪያ ቤት ሠራተኛ ጋር ያደረገው ቃለ ምልልስ ቁጥር 16፣ግንቦት 14,2003

[96] የሂዩማን ራይትስ ዎች ቃለ ምልልስ ቁጥር 12፤ ታችኛው ኦሞ፣ ግንቦት/ሰኔ 2003

[97] በግብርና ኢንቨስተሮቹና በኢትዮጵያ መንግስት መካከል የሚደረጉት ስምምነቶች ኢንቬስተሩ ስምምነቱ ስራ ላይ በዋለ በሦስት ራት ጊዜ ውስጥ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ እንዲያቀርብ ይጠይቃል።(አንቀጽ 4(1)(መ))። በታችኛው ኦሞ አካባቢ ባሉ መሬቶች ላይ ከተፈጸሙት ይህንን መሰል ዉሎች መካከል ስድስቱ በዚትዮጵያ መንግስት 'አግሪካልቸራል ፖርታል' ድረ ገጽ http://www.eap.gov.et/index.php?q=node/835 . እነዚህ ውሎች የሦስት ወሩ የጊዜ ገደብ አልፎባቸዋል።ሂዩማን ራይትስ ዎች ያነጋገራቸው የአካባቢው ነዋሪዎች የዚህ ዓይነት ግምገማ ስለመኖሩ ያዩትም የሰሙትም ነገር የለም።

[98] የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስትር ሽፈራው ተከለማርያም ለሂዩማን ራይትስ ዎች የጻፉት ደብዳቤ፣ ታህሳስ 9,2004

[99] ሂዩማን ራይትስ ዎች የታችኛውን ኦሞ አካባቢ ከጎበኘ ሰው ጋር ያደረገው የኢሜይል ግንኙነት፣ ታህሳስ 2004፤ከአካባቢው የተገኙ ሌሎች ምስክርነቶች እንደሚያሳዩት በስኳር ልማቱ ሃላፊዎችና በቦዲ ብሔረሰብ አባላት መካከል ስብሰባ ከተካሄደ በኋላ በአደጋው ሕይወታቸውን ያጡት ሰዎች ባላቤቶች 50000 ብር በካሳ መልክ እንዲከፈላቸው ተደርጓል። ሂዩማን ራይትስ ዎች ዘንድ በፋይል የሚገኙ ማስታወሻዎች።

ሰራተኞች እንዲሁም በቦዲዎቹና በጦር ሃይሉ መካከል የነበረው ውጥረት እንዲባባስ ምክንያት ሆነዋል። ከዚያም በኋላ በቦዲ ብሄረሰብ አባላት እና በጦር ሃይሉ መካከል በርካታ አነስተኛ ግጭቶች ተከስተዋል።[100]

በታህሳስ ወር 2004 በኦሞ ወንዝ ዳርቻ እያረሰ የሚኖር አንድ የክዌጉ ብሔረሰብ አባል ለልማት ስራው በመጡ ሰራተኞች የንብ ቀፎዎቹ ወድመውበታል።እሱንና እሱን መሰል ሰዎች ይህንን መሰሉን የመንግስት ድርጊት እንዳይቃወሙ ስላደረጓቸው የምክክር አለመኖርና የፍርሃት መስፈን ሲናገር እንዲህ ብሏል፡

> ሲመጡ አየኋቸው፣ግን ፈራሁ። ሄጄ ባናግራቸው ይደበድቡኝና ምናልባት እሞታለሁ።አንድ ተራ ክዌጉ ነኝ....እንዴት ብዬ ነው የማናግራቸው? ፈራሁ....ከተናደዱ ምናልባት እኔንም አንድ ትልቅ የንብ ቀፎ ውስጥ ይከቱኛል። እዚያ ውስጥ ይደብቁኛል። ምንም ማድረግ አልችልም።ምንድነው ማድረግ ያለብን?[101]

## በኢኮኖሚ፣በማሕበራዊና በባሕል መብቶች ላይ የተፈጸሙ ጥሰቶች

### *ተገዶ መፈናቀል፣ በአንድ አካባቢ ተወስኖ መኖር እና የታችኛው ኦሞ*

ሂዩማን ራይትስ ዎቸ በሰኔ ወር 2003 አካባቢውን በጎበኘበት ወቅት የታችኛው ኦሞ ተወላጅ ነዋሪዎችን ከመኖሪያቸው አስገድዶ ማፈናቀል በሙርሲ እና በቦዲ አካባቢዎች ገና መጀመሩ ነበር። በየስብሰባዎቹ የሚሰጡት የመንግስት መግለጫዎች ሰዎችን ወደ ሌሎች አካባቢዎች ወስዶ የማስፈሩ ስራ በሰፊው እንደሚካሄድ የሚያመለክቱ ቢሆንም የሰፈራ ቦታዎቹ የት እንደሚሆኑ ግልጽ አይደለም። ግልጽ የሆነ ነገር ቢኖር የሰፈራ ሂደቱ የሚካሄደው በፈቃደኝነት አለመሆኑ ብቻ ነው። አንድ የሙርሲ ተወላጅ እንደገለጹት ፣ "በግድ ነው፣ምንም ፈቃደኝነት የለበትም። ይህ የምንፈልገው ነገር አይደለም።"[102] በዚያ ጊዜ የመንገድ ግንባታ እና የመሬት ምንጣሮ ገና መጀመሩ ነበር።

ሊካሄድ ስለታሰበው ሰዎችን በሌሎች አካባቢዎች የማስፈር ስራ ተደጋግሞ የሚሰጠው ምክንያት ማስፈሩ ለስኳር ልማት ስራው አስፈላጊ በመሆኑ ነው የሚል የነበረ ቢሆንም መንግስት ብሔራዊ ፓርኮቹንም በምክንያትነት ያቀርብ ነበር። ሂዩማን ራይትስ ዎች በማጎ ብሔራዊ ፓርክ ውስጥ የተለቀቁ የሙርሲ መንደሮችን ለማየት የቻለ ሲሆን ነዋሪዎቹም ከማጎ ሸለቆ ከፍ ብሎ በሚገኘው ደረቅ እና በረሃማ ቦታ ከሳምንታት በፊት እንዲሰፍሩ ተደርጎ ነበር።[103] ባለስልጣናት ፓርኩ ለአራዊት ወይም ለቱሪስቶች እንጂ ለእነሱ እንዳልሆነ ነግረዋቸዋል። ፓርክ እንዴት በምክንያትነት እየቀረበ እንዳለ በማጎ ወንዝ አካባቢ በሚገኝ አንድ የሙርሲ መንደር የሚኖሩ እንድ ሰው ሲናገሩ፡

> 'ይህ ፓርክ ነው፤ከፍታው ቦታ ላይ ወዳለው መንደር መሄድ አለባችሁ።' ይሉናል። ለምን እንደሆነ አናውቅም።ይህ የሙርሲ መሬት ነው።ሁሌም ቢሆን የሙርሲ መሬት ነበር። አባቴም፣ አያት ቅድመ አያቶቼም እዚህ ነበሩ። ፖሊሶች ይመጡና ይነግሩናል፣ይመቱናል፣ወደጫካ ስንሸሽ ከመሃላችን አንዱ ላይ ጥይት ተኮሱበት።ጥይቱ ክንዱን ጨርፎታል።[104]

በማጎ እና በኦሞ ብሔራዊ ፓርኮች የሚገኝ ሰፊ መሬት ለስኳር ልማቱ ሊመነጠር ተከልሏል [በብሔራዊ ፓርኮቹ እና ለታቀደው የስኳር ልማት የታሰበው መሬት አንድ ቦታ ላይ የሚያርፉ መሆኑን ለማየት ካርታ 3ን ይመልከቱ]።[105] መንግስት በቅርቡ ነዋሪዎችን ከኦሞ እና ከማጎ ብሔራዊ ፓርኮች አስገድዶ አፈናቅሎአል።[106]

---

100 በታችኛው ኦሞ አካባቢ የሚኖሩ ተወላጅ ሕዝቦች "ደገኛ" የሚለውን ቃል ከደጋማው የሃገሪቱ ክፍሎች የሚመጡ ሰዎችን ለመግለጽ ይጠቀሙበታል።ቃሉ በተለይም የአማራ፣የትግራይ እና የኦሮሞ ብሔሮች አባላትን ለመግለጽ ይውላል።

101 በቪዲዮ የተቀረጸ ምስክርነት ቁጥር 24፣ ሂዩማን ራይትስ ዘንድ በፋይል የሚገኝ

102 ሂዩማን ራይትስ ዎች ከታችኛው ኦሞ ነዋሪ ጋር ያደረገው ቃለ ምልልስ ቁጥር 8፤ ግንቦት 24,2003

103 የማጎ ብሔራዊ ፓርክ አብዛኛው ክፍል የሚገኘው በሙርሲ እና በክዌጉ አካባቢዎች ከታችኛው የኦሞ ሸለቆ በስተምስራቅ ነው። ካርታ 2ን ይመልከቱ

104 ሂዩማን ራይትስ ዎች ከታችኛው ኦሞ ነዋሪ ጋር ያደረገው ቃለ ምልልስ ቁጥር 3፣ ግንቦት 24,2003

105 የኢትዮጵያ ዱር አራዊት ጥበቃ ባለስልጣን የስኳር ልማቱ የሚካሄድበትን አካባቢ ከፓርኮቹ ድንበር የመከለል ስራ የተሰራው በ2003 ነው በማለት ይገልጻል።ባለስልጣኑ እንደሚገልጸው የማጎ ብሔራዊ ፓርክ ስፋት በ30000 ሄክታር የተቀነሰ ሲሆን የኦሞ ብሔራዊ ፓርክ ደግሞ በ42885 ሄክታር ተቀንሷል። ቸሬ እናውጋው፣ደርቤ ደክሲዎስ እና ግርማ ቲመር፣ "Existing Challenges," የኢትዮጵያ ዱር አራዊት ጥበቃ ባለስልጣን፣ ሴፕቴምበር 2010

106 በኢትዮጵያ የታችኛው ኦሞ አከባቢ የሚካሄደው የማፈናቀል ተግባር ዓለማቀፍ ትኩረት ያገኘው በ1997 የአፍሪካን ፓርክስ ኔትዎርክ ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር የኦሞ ፓርክን ለማስተዳደር ስምምነት በፈረመበት ወቅት ነው።ዋናው ጉዳይ በስምምነቱ ውስጥ ለተወላጅ ሕዝቦች መብቶች ጥበቃ የሚያደርግ እና ማፈናቀል እንደማይፈጸም ዋስትና የሚሰጥ ድንጋጌ አለመኖሩ ነበር። (ከዚያ በፊት ኔትወርኩ አዚያወ አካባቢ የሚገኘውን የነጭ ሳር ብሔራዊ ፓርክ ለመረከብ ከመንግስት ጋር ስምምነት በፈረመበት ወቅት

ከማጎ ብሔራዊ ፓርክ ውጭ በሚገኙ ሌሎች ሁለት የተለያዩ የሙርሲ መንደሮች የሚኖሩ ሰዎች ለሂዩማን ራይትስ ዎች እንደገለጹት ከመኖሪያቸው እንደሚነሱ ከወራት በፊት የመንግስት ባለስልጣናት  ነግረዋቸዋል። ነገርግን የሚነሱበት ጊዜ እና ወዴት እንደሚወሰዱ አልተነገራቸውም። በሌሎች ሁለት መንደሮች የሚኖሩ የሙርሲ ማህበረሰቦች ግን ስለመነሳቱና በሌላ አካባቢ ስመስፈሩ የሰሙት ወታደሮች ወደ መንደሮቻቸው መጥተው በሃይለውሃ አካባቢ በቋሚነት እንደሚሰፍሩ በነገሯቸው ጊዜ ነው።(በአንድ አካባቢ ሰፍረው የሚኖሩት ማህበረሰቦች ግን ቀደም ብሎ ተነግሯቸዋል)።[107]
የታችኛው ኦሞ ነዋሪዎች እንደተነገራቸው ከሆነ በሌሎች አካባቢዎች ሲሰፍሩ የሚጠበቅባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች በአንድ አካባቢ በቋሚነት መስፈር እና የከብቶቻቸውን ቁጥር በከፍተኛ መጠን መቀነስ ነው።[108] ይህ ደግሞ ማህበረሰቦቹ ያላቸውን የኑሮ መሠረት እና ባሕላዊ እሴቶቻቸውን የሚጎዳ ሲሆን የምግብ ዋስትናቸውን አደጋ ላይ በመጣል በተለይ ህጻናት ተፈላጊውን የምግብ ንጥረ ነገር እንዳያገኙ ሊያደርግ ይችላል። ባለፈው አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ የመንግስት እና የጦር ሃይል ባለስልጣናት ይህንን መልእክት በተደጋጋሚ ጊዜ ለታችኛው ኦሞ ነዋሪዎች አስተላልፈዋል።[109]

ከአካባቢው የወጡ ዘገባዎች እንደሚያመለክቱት ለ 1700 የቦዲ ብሔረሰብ ቤተሰቦች መስፈሪያ የሚሆን 1700 ሄክታር (4200 ኤከር) መሬት ተመንጥሮ ተዘጋጅቷል።  ይህ ዝግጅት በአካባቢው ይገኝ የነበረን ማንኛውም ተክል ሙሉ በሙሉ ማውደምን እና ለእያንዳንዱ የቦዲ ቤተሰብ ቤት መስሪያ የሚሆን መሬት መከለልን የሚጨምር ነበር።ቃል ከተገቡት እንደ ቤት፣ክሊኒኮች እና ትምህርት ቤቶችን የመሳሰሉ የመሰረተ ልማት አውታሮች ውስጥ እስካሁን ድረስ አንዱም አልተሰራም። አዲሱ የመስፈሪያ ቦታ የመስኖ ውሃ የሚያገኝ ሲሆን ከኦሞ ወንዝ እና ከመስኖ መስመሮቹ በስተምስራቅ ይገኛል። ለቤቶቹ መስሪያ የሚሆን እንጨት ከጥቂት ዓመታት በፊት በቦዲ አካባቢዎች እንዲሰፍሩ በተደረጉት የኮንሶ ማህበረቦች ክፍያ ያልተደረገበት የጉልበት እርዳታ ተሰብስቧል።[110]

በርካታ ነዋሪዎች በአካባቢው ያለው የውሃ እጥረት በከብቶቻቸው እና በኑሮአቸው ላይ የሚያስከትለውን ተጽዕኖ በመፍራት ያላቸውን ስጋት ገልጸዋል።ከማጎ ወንዝ ሸለቆ እንዲነሱ ተደርገው በሜዳማው አካባቢ እንዲሰፍሩ የተደረጉ አንድ የመንደሩ ነዋሪ ሲናገሩ፡

> እዚህ ለመንደራችን የሚሆን ውሃ የለም። መንግስት ለእኛ እና ለከብቶቻችን የሚሆን ውሃ እንደሚያቀርብልን ነግሮናል።የትም እንዳንሄድ እዚሁ እንድንቆይ ነግረውናል።በየጫካው ያሳድዱናል፤ ከዚህ በኋላ ወደ ኦሞ ወንዝ ደለል መሄድ አትችሉም ብለውናል።[111]

ሌላ የሙርሲ መንደር ነዋሪ ሲናገሩ፡

> ወቅቱ ደረቅ በሚሆንበት ጊዜ ችግር ይፈጠራል። አሁን ውሃ አለ፣ነገር ግን ውሃ በማይኖርበት ወቅት ወደ ኦሞ ወንዝ የማንመለስ ከሆነ መንግስት ውሃ እንዲያቀርብልን እንፈልጋለን፤ የማያቀርብልን ከሆነ ግን እኛም ከብቶቻችንም እንሞታለን። ሆነም ቀረ ግን ወደ ኦሞ ወንዝ እንሄዳለን፤ አለዚያ እንሞታለን፣ ከፈለጉ እዚያ ሊገድሉን ይችላሉ።[112] ብለዋል።

ሂዩማን ራይትስ ዎች የጎበኛቸው ሁለት የሙርሲ እና ሁለት የቦዲ ማህበረሰቦች በስኳር ልማቶቹ እንደሚሰሩ በወታደሮቹ እንደተነገራቸው ተናግረዋል። ይህም የሚሰፍሩት ነዋሪዎች እንደመሬት አከራይ ሆነው እንደሚሰሩ የሚጠቁም ነው። አንድ የቦዲ አርብቶ አደር ሲናገሩ፡

---

ማፈናቀል ተፈጽሞ ነበር)።መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በዓለማቀፍ ደረጃ ባደረጉት ከፍተኛ ግፊት የአፍሪካ ፓርክስ ኔትዎርክ ፓርኮቹን ለማስተዳደር ከፈረመው ውል ውስጥ "በገንዘብ ምክንያት" በሚል ለመውጣት ወስኗል።ኔትወርኩ ከወጣ ጊዜ ጀምሮ ኦሞ እና ማጎ ብሔራዊ ፓርኮች አናሳ አስተዳደር እንዲኖራቸው የተደረገ ሲሆን በነጋሪት ጋዜጣ ባለመታወጁ ያላቸው ሕጋዊ አቋም በግልጽ የሚታወቅ አይደለም።

107 ሂዩማን ራይትስ ዎች ከታችኛው ኦሞ ነዋሪ ጋር ያደረገው ቃለ ምልልስ ቁጥር 3፣4እና8። ግንቦት 25፣26 እና 27 2003

108 ሂዩማን ራይትስ ዎች ከታችኛው ኦሞ ነዋሪ ጋር ያደረገው ቃለ ምልልስ ቁጥር 3፣4እና8። ግንቦት እና ሰኔ 2003

109 ሂዩማን ራይትስ ዎች ከታችኛው ኦሞ ነዋሪ ጋር ያደረገው ቃለ ምልልስ ቁጥር3፣4፣8እና16። ግንቦት እና ሰኔ 2003

110 ሂዩማን ራይትስ ዎች ከአባቢው ነዋሪ እና አካባቢውን ከጎበኘ ሰው ጋር ያደረጋቸው የኢሜይል ግንኙነቶች፣ የካቲት 2004

111 የሂዩማን ራይትስ ዎች ቃለ ምልልስ ቁጥር 4፣ ታችኛው ኦሞ፤ ግንቦት 26፣ 2003

112 የሂዩማን ራይትስ ዎች ቃለ ምልልስ ቁጥር 4፣ ታችኛው ኦሞ፤ ግንቦት 25/ 2003

> ከመንግስት የሚወጡ ሁለት መልእክቶች አሉ፡ በስኳር ልማቱ ተቀጥረን እንደምንሰራ እና በዶማ ሳይሆን በበሬ የሚታረሱ ትንንሽ እርሻዎች ማዘጋጀት እንደምንጀምር የሚገልጹ።[113] ብለዋል።

አንድ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ባለስልጣን "ሰዎች እንዲሰፍሩ እየተደረገ ያለው ለልማቶቹ ስራ የሚውል የሰው ጉልበት ለማቅረብ ነው፣" በማለት በብዙ የታችኛው ኦሞ የሚሰነዘረውን ፍርሃት ትክክለኝነት አረጋግጠዋል።[114] ባለስልጣኑ ጨምረው እንደገለጹት፡

> ይህ ለሕዝባችን አዲስ ጉዳይ ነው።በጣም መጥፎ እንደሆነ ይሰማኛል።ደገኞቹ (የመሃል ሀገር ሰዎች) የጉልበት ስራ ለመስራት ወደዚህ መጥተው የሚሰፍሩ ከሆነ፣ መጠጣት ይኖራል፣ከብቶቻችንን ቀስ በቀስ እንሸጣለን፣ የሚቀጥለው ነገር ወደ ልመና መግባት ነው። ራሳችንን ችለን መኖራችን ይቀራል።ደገኞቹ ሲመጡ ባሕላችን ይጠፋል። ይህ በደቡባዊ ኢትዮጵያ አርብቶ አደርነትን የሚያጠፋ ነው።[115]

ሂዩማን ራይትስ ዎች አካባቢውን ከጎበኘ በኋላ ከነዋሪዎችና አካባቢውን ከጎበኙ ሰዎች የሚወጡ ዘገባዎች እንደሚጠቁሙት የስኳር ልማቱ ሠራተኞቹ በሙርሲ፣በቦዲ እና በክዌጉ አካባቢዎች የሚያካሂዱት የመሬት ምንጣሮ በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሯል፤ ነዋሪዎቹ ከጎርፍ ለመሸሽ እና ለእርሻ የሚጠቀሙባቸው አካባቢዎችም ተመንጥረዋል።[116] የታችኛውን ኦሞ የጎበኙ አንድ ሰው እንደገለጹት በስኳር ልማቱ ላይ በከባድ ማሽኖች ላይ ከሚሰሩ ሠራተኞች ጋር ወታደሮች ብዙ ጊዜ ቁጭ ብለው ይታያሉ።[117]

የአካባቢው ነዋሪዎች ለምን ዓላማ እየተጠቀሙበት እንዳለ ከግምት ውስጥ ሳይገባ መሬቱ እየተመነጠረ ያለ ይመስላል።የኦሞ ወንዝን ይዞ የሚገኘው ጫካ በአካባቢው ለእርሻ የዋለው መሬት፣ ከንብ ቀፎዎች እና በባሕላዊ መንገድ ተክሎችን ለመሰብሰብ ከሚውለው መሬት ጋር አብሮ እየተመነጠረ መሆኑ ተዘግቧል።[118]

---

113 ሂዩማን ራይትስ ዎች ከታችኛው ኦሞ ነዋሪ ጋር ያደረገው ቃለ ምልልስ ቁጥር 11።ግንቦት 25/2003

114 ሂዩማን ራይትስ ዎች ከታችኛው ኦሞ ነዋሪ ጋር ያደረገው ቃለ ምልልስ ቁጥር 17። ግንቦት 2003

115 ሂዩማን ራይትስ ዎች ከታችኛው ኦሞ ነዋሪ ጋር ያደረገው ቃለ ምልልስ ቁጥር 16። ግንቦት 25/ 3003

116 ሂዩማን ራይትስ ዎች አካባቢውን ከጎበኘ ሰው ጋር ያደረጋቸው የኢሜይል ግንኙነቶች፣ ጥር-መጋቢት 2004

117 ሂዩማን ራይትስ ዎች አካባቢውን ከጎበኘ ሰው ጋር ያደረጋቸው የኢሜይል ግንኙነቶች፣ ጥር 2004

118 ሂዩማን ራይትስ ዎች አካባቢውን ከጎበኘ ሰው ጋር ያደረጋቸው የኢሜይል ግንኙነቶች፣ ጥር 2004 እና በቪዲዮ የተቀረጸ ምስክርነት ቁጥር 17 ሂዩማን ራይትስ ዎች ዘንድ የሚገኝ።

## በታችኛው የኦሞ ሸለቆ የተካሄደ የመሬት ምንጠራ



ከላይ የሚታየው ምስል በ 2003 የተነሳ ሲሆን ከታች ያለው ደግሞ በጥር ወር 2004 እዚያው ቦታ የተነሳ ምስል ነው።

©2011 ሰርቫይቫል ኢንተርናሽናል



# IV. የምግብ ዋስትና እና የኑሮ መሠረቶች

## በከፊል ግብርናና ከብት ርቢ የሚተዳደሩት የቦዲ እና የሙርሲ ብሔረሰቦች

የቦዲ እና የሙርሲ ብሔረሰብ አባላት የምግብ ዋስትና እና የኑሮ መሠረት የተመሰረተው በከብት ርቢ እና በኦሞ ወንዝ ዳርቻዎችና በሌሎች ለም አካባቢዎች በሚካሄድ እርሻ ላይ ነው።ኦሞ ወንዝን እና ገባሮቹን ተከትሎ ያለው ጎርፍ ባመጣው አፈር እና በዝናብ ወቅት ለግብርና የሚጠቀሙበት መሬት ለንግድ ግብርና ተብሎ መወሰዱ እና የከብቶቻቸውን ቁጥር በግዴታ እንዲቀንሱ መደረጉ የነዋሪዎቹን የምግብ ዋስትና የሚያዳክም ሲሆን የኑሮ መሠረታቸውንም የሚያጠፋ ነው።

ሂዩማን ራይትስ ዎች አካባቢውን በጎበኘበት ወቅት ይህ ሂደት ገና መጀመሩ የነበረ ሲሆን እስካሁንም ቀጥሎአል። ነዋሪዎች ለሂዩማን ራይትስ ዎች እንደገለጹት እስከ የካቲት 2004 ባለው ጊዜ ውስጥ የቦዲ ብሔረሰብ አባላት መኖሪያ የነበሩ ሰፋፊ መሬቶች ተመንጥረዋል።የመስኖ መስመሮች ግንባታ እየተካሄደ ነው መሬት ተቆፍሮ በተሰሩ ግድቦች አማካይነት ውሃ ከኦሞ ወንዝ ወደ መስኖ ቱቦዎቹ እንዲገባ እየተደረገ ነው።ሰዎች ከሚሰፍሩባቸው ጣቢያዎች አንዱም በመዘጋጀት ላይ ይገኛል።[119]ከግድቡ በታች ወደሚገኙ አካባቢዎች የሚፈሰው የውሃ መጠን በጣም ቀንሷል (ከታች ያሉትን ምስሎች ይመልከቱ)። ነዋሪዎች እንደገለጹት ከግድቡ የላይኛው አካባቢ በተከሰተ ድንገተኛ የወንዝ ውሃ ሙላት ቢያንስ 25 የቦዲ በሄረሰብ አባላት ማሳዎች ላይ የነበረ ለአጨዳ የደረሰ ማሽላ በጎርፍ ተጥለቅልቋል። አብዛኛው ሰብልም ወድሟል።[120]

---

[119] ሂዩማን ራይትስ ዎች ከታችኛው ኦሞ ነዋሪ ጋር ያደረገው የኢሜይል ግንኙነት፣ የካቲት 2004

[120] ሂዩማን ራይትስ ዎች አካባቢውን ከጎበኘ ሰው ጋር ያደረጋቸው የኢሜይል ግንኙነቶች፣ የካቲት 21/2004



የኦሞ ወንዝን ውሃ ወደመስኖ ማስተላለፊያዎቹ እንዲያስገባ ታስቦ ከመሬት ተቆፍሮ የተገነባው ግድብ። ይህ የኦሞ ወንዝን ውሃ ፍሰት የሚያሳይ በየካቲት ወር 2004 የተነሳ ምስል ነው። ©2012 ሰርቫይቫል ኢንተርናሽናል።



ይህ ደግሞ ከአንድ ዓመት በፊት በየካቲት ወር 2003 ከተለየ አቅጣጫ የተነሳ የዚያው ቦታ ምስል ነው። የቦዲ ብሔረሰብ ሴቶች በወንዙ በስተምዕራብ ከሚገኘው የማሽላ ማሳቸው በምስራቅ ወደ ኦሞ ወንዝ ሲያቋርጡ ይታያሉ።©2011 ሂዩማን ራይትስ ዎች

የታችኛውን ኦሞ አካባቢ ለጎበኘ አንድ ሰው አንዲት የኦሞ ሴት እንደነገሩት፡

> በቀደም ዕለት ወደ ኦሞ ወንዝ ሄጄ ነበር። መንግስት በሰራቸው አዲስ መንገዶች ነበር የሄድኩት....እህል ለማውጣት ወደ ጎተራዬ ስሄድ ጎተራው አልነበረም።ጎተራዬ በቡልዶዘር ታርሶ ጠፍቷል።ኦሞ ወንዝ ላይ የነበረን ቦታ ልጆቻችንን ለማሳደግ የምንመካበት ነበር። አሁን የት ልንኖር ነው? መንግስት ራሱ መንደር ሆኖ የራሱን ምግብ አይበላም?ለምን መጥቶ እዚህ የእኛ የሙርሲዎች ጫካ ውስጥ ይቀመጣል?ከዚህ በፊት አብረን ኖረናል?
>
> እያደረጉ ያሉት ነገር ደስ አይለኝም።የሄድኩ ጊዜ አለቀስኩ። ጎተራችን ጠፍቷል...እህል ይዘን መመለስ አንችልም፣ጎተራዎቻችን የነበሩበት ቦታ ጠፍቷል።ምናልባት እንሞት ይሆናል።ይኸው ነው።[121] ብለዋል።

ሌላ የቦዲ ብሔረሰብ አባል የሆኑ ሰው ሲናገሩ ደግሞ፡

> ቡልዶዘሩ ያጠፋው እህል የዘራንበትን መሬት ጭምር ነው። እህል ዘርተንበት የነበረውን ቦታ መንጥረው ሻይጊታን ወደተባለ ቦታ የሚወስድ ቀጥ ያለ መንገድ ሰርተዋል።[122] ብለዋል

አካባቢውን በቅርብ ጊዜ የጎበኙ ሰዎች እንደሚያረጋግጡት የመንገድ እና የካምፖች ግንባታ እንዲሁም የመሬት ምንጣሮው ተጠናክሮ ቀጥሏል።[123]

ለቦዲ እና ለሙርሲ ብሔረሰብ አባላት ማንነት፣የኑሮ መሠረት እና የምግብ ዋስትና ከብቶች ቁልፍ ሚና አላቸው። ከብቶቻቸውን መተው እንዳለባቸው በመንገር የመንግስት ሃይሎች የእነዚህን ሕዝቦች ኢኮኖሚያዊ ነጻነት እና ባሕላዊ ዕሴቶች ለማጥፋት እየሞከሩ ያሉ ይመስላል።

አንድ የሙርሲ ብሔረሰብ አባል ከብቶች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ስላላቸው ሚና ለሂዩማን ራይትስ ዎች ሲገልጹ፡

> ምን ልበላ ነው? ከብቶቼን በሙሉ ወስጄ እንድሸጥና አንድ ብቻ ከቤቴ እንዳስቀር ነገሩኝ። አንዱን ከብት ምን ላደርገው ነው? እኔ ሙርሲ ነኝ። ረሃብ ቢመጣ የላም አንገት ወግቼ ደም እጠጣለሁ። ከብቶቹን ሁሉ ለገንዘብ ከሸጥናቸው እንዴት ነው የምንበላው? ጋብቻ ስንፈጽም የምንሰጠው ከብት ነው። በምን እንጋባ? ምን እንብላ? ረሃብ ሲመጣ ልጆቻችንን ምን ልናበላቸው ነው? ዶሮ ብቻ ብናረባ መረቃቸውን እንጠጣለን ወይስ እናልባቸዋለን...? 'ይህ የኔ መሬት ነው [እናንተ] እንደ ዝንጀሮ ወደ ጫካ ሂዱ።'ይላሉ ደገኞቹ ኢትዮጵያውያን።[124]

አንድ የቦዲ ብሔረሰብ አባል ደግሞ የከብቶችን አስፈላጊነት ሲያጠናክሩ፣ "የምናመርተው ምግብ ሁሉ ከከብቶች የሚገኝ ነው።ተጨማሪ ምግብ ስንፈልግ ይህንኑ እንሸጣለን። ስለዚህ፣ የከብቶቻችን ቁጥር ቀነሰ ማለት ደኸየን ማለት ነው።" ብለዋል።[125]

በርካታ የመንደሮቹ ነዋሪዎች ወታደሮች ከብቶቻቸውን እንደሚሰርቋቸው እና በአዳዲሶቹ የሰፈራ ጣቢያዎች ከብቶች እንደማያስፈልጓቸው እንደሚነግሯቸው ገልጸዋል። አንድ የሙርሲ ብሔረሰብ አባል ወታደሮች ስምንት ላሞችን ከመንደራቸው እንደወሰዱ ተናግረዋል።[126] አንድ ሌላ ሰው ደግሞ በሙርሲ ከሚገኙ አካባቢዎች የተወሰዱትን "10 ከማኪ፣ 10 ከማጌንቶ፣ 10 ከሙጊጂ፣ 10 ከጎንጉሎቢቢ፣ 7ከአሪሆሊ እና 10 ከቢዮጎልካሬ" ጨምሮ መንግስት ከብቶቻቸውን እንደወሰደ ተናግረዋል።[127]

---

121 በቪዲዮ የተሰጠ ምስክርነት ቁጥር 10፣ ሂዩማን ራይትስ ዎች ዘንድ በፋይል የሚገኝ

122 በቪዲዮ የተሰጠ ምስክርነት ቁጥር 2፣ ሂዩማን ራይትስ ዎች ዘንድ በፋይል የሚገኝ

123 በቪዲዮ የተሰጡ ምስክርነቶችና ከታችኛው ኦሞ ነዋሪዎች ጋር የተደረጉ የኢሜይል ግንኙነቶች፣ ነሃሴ 2003-መጋቢት 2004

124 በቪዲዮ የተሰጠ ምስክርነት ቁጥር 11፣ ሂዩማን ራይትስ ዎች ዘንድ በፋይል የሚገኝ

125 በቪዲዮ የተሰጠ ምስክርነት ቁጥር 10፣ ሂዩማን ራይትስ ዎች ዘንድ በፋይል የሚገኝ

126 ሂዩማን ራይትስ ዎች ከታችኛው ኦሞ ነዋሪ ጋር ያደረገው ቃለ ምልልስ ቁጥር 15፣ ግንቦት 27/2003

127 ሂዩማን ራይትስ ዎች ከታችኛው ኦሞ ነዋሪ ጋር ያደረገው የኢሜይል ግንኙነት፣ ነሃሴ 29/2003

በርካታ የአካባቢው ነዋሪዎች ከሰጡት ምስክርነት መረዳት እንደሚቻለው በቅርቡ የመንግስት ባለስልጣናት እና የጦር ሃይሉ አባላት የቦዲ እና የሙርሲ ብሔረሰብ አባላት የከብቶቻቸውን ቁጥር በከፍተኛ መጠን ቀንሰው አንድ ቤተሰብ ጥሩ የስጋ ምርት የሚሰጡትን ሁለት ወይም ሦስት የቦረና ከብቶች እንዲዝዙ ነግረዋቸዋል።[128]
በአካባቢው የሰፈነውን ስጋት አንድ የቦዲ ብሔረሰብ አባል በታህሳስ ወር 2004 ሲያጠቃልሉ እንደተናገሩት፡

> ጫካ እና ደኖቻችንን እየቆረጡ፣ማሳችንን በቡልዶዘር እያወደሙ ነው። ከብቶቻንን በሙሉ እንድንሸጥ ይፈልጋሉ።ማንም ከብቱን አይሸጥም።እነሱ ከዚህ መሄድ አለባቸው።ደናችንን እኛው በእጃችን እንድናለማው ሊተዉልን ይገባል።[129]

## የክዌጉ (ሙጉጂ) ብሔረሰብ

ክዌጉዎች የኦሞ ወንዝን ዳርቻዎች ይዘው ከቦታ ቦታ ሳይዘዋወሩ በአንድ አካባቢ ሰፍሮ የመኖር ልማድ ያላቸው ማህበረሰቦች ናቸው። በወንዙ ሁለቱም ዳርቻዎች ማሽላ የሚያበቅሉ ሲሆን ዓሳም ከዚያው ያጠምዳሉ።ከጥር ወር 2004 ጀምሮ ባለው ጊዜ በሁለቱም የወንዙ ዳርቻዎች የሚገኘው የክዌጉዎቹ መሬት ተመንጥሯል።በዚህ ምክንያት በጠፋባቸው ሰብል ምክንያት በማህበረሰቡ አባላት ላይ የሚስተዋለውን ስጋት አንድ የብሔረሰቡ ተወላጅ "ክዌጉዎች አሁን ተርበዋል።ከብቶችም ወተትም የላቸውም።ቡልዶዘሩም ሰብላቸውን በሙሉ አውድሞታል።"[130] በማለት አጠቃለውታል።ሌላ የክዌጉ ተወላጅ በኦሞ ወንዝ ዓሳ እንዳያጠምዱ ሊከለከሉ እንደሚችሉ ያደረባቸውን ስጋት አስመልክቶ በታህሳስ ወር 2004 ሲገልጹ፡ "የእኔ ውሃ ነው። ዓሳ እበላለሁ። የእኛ ምግብ ነው።"[131] ብለዋል።

በየካቲት ወር 2004 በኦሞ ወንዝ ላይ የተሰራው ውሃ ማስቀየሻ ግድብ የኦሞ ወንዝን ፍሰት ወደ ጠብታ መጠን ቀንሶታል። ነዋሪዎቹ እንደሚገልጹትም በታችኛው የተፋሰሱ ክፍል የሚኖሩት ክዌጉዎች የሚያጠምዱት ዓሳ መጠንም ወዲያውኑ ቀንሷል።[132] ይህ በዓሳዎች የመኖሪያ ስፍራ እና በሚጠመዱት ዓሳዎች የታየው መቀነስ በክዌጉዎች የኑሮ መሠረት ላይ ጎጂ የሆነ ተጽዕኖ ይኖረዋል።[133]

አንድ የሙርሲ ብሔረሰብ አባል የክዌጉ እና የሙርሲ ማህበረሰቦች ሲጠቀሙባቸው የነበሩ የእርሻ መሬቶች መመንጠራቸውን አስመልክቶ በታህሳስ ወር 2004 ሲናገሩ፡

> የመንግስት ባለስልጣናት የክዌጉ እና የቦዲ ብሔረሰብ አባላትን ማሳ መነጠሩ። ሰፊ ቦታ መንጥረው ማሽላቸውን ነቃቀሉባቸው። ማሽላው እየደረሰ ነበር፤ተሽከርካሪ አምጥተው ማሳውን ከገለበጡ በኋላ ማሽላውን ወረወሩት። የክዌጉዎቹ ማሳዎች ተገልብጠዋል። አንዳንድ ክዌጉዎች አሁን ምንም የላቸውም። ማሽላቸው ከተገለበጠ ምን ሊበሉ ነው? ለልጆቻቸውስ ምን ይሰጧቸዋል?[134] ብለዋል።

## ወደፊት የሚኖረው ሁኔታ

መንግስት ዜጎችን ያለፈቃዳቸው ወደሌላ አካባቢ ለማስፈር እና የኑሮ መሠረታቸውን እንዲለውጡ ለማድረግ እያደረገ ያለው ጥረት በአካባቢው ልዩ ልዩ ማህበረሰቦች መካካል እና በማህበረሰቦቹ እና በመንግስት መካከል ግጭቶች ሊከሰቱ የሚችሉበትን እድል ይጨምረዋል። አንድ ሰው በሰኔ ወር 2003 እንዳስጠነቀቁት "የከብቶቻችንን ቁጥር ለመቀነስ የሚሞክሩ ከሆነ ከአርብቶ አደሮች ጋር ወደፊት ችግር ሊከሰት ይችላል።"[135]

መንግስት የኑሮ መሠረት እና የአኗኗር ዘይቤን አስገድዶ ለማስቀየር እየሞከረ ነው የሚለው ስጋት የጦር ሃይል አባላቱ በሚናገሯቸው ንግግሮች እየተጠናከረ ነው።አንድ ነዋሪ አንድ የመንግስት ወታደር እንዲህ ብሎ እንደነገረው ይገልጻል፡

128 በቪዲዮ የተሰጠ ምስክርነት ቁጥር 1፣ ሂዩማን ራይትስ ዎች ዘንድ በፋይል የሚገኝ

129 በቪዲዮ የተሰጠ ምስክርነት ቁጥር 2፣ ሂዩማን ራይትስ ዎች ዘንድ በፋይል የሚገኝ

130 በቪዲዮ የተሰጠ ምስክርነት ቁጥር 6፣ ሂዩማን ራይትስ ዎች ዘንድ በፋይል የሚገኝ

131 በቪዲዮ የተሰጠ ምስክርነት ቁጥር 22፣ ሂዩማን ራይትስ ዎች ዘንድ በፋይል የሚገኝ

132 ሂዩማን ራይትስ ዎች ከታችኛው ኦሞ ነዋሪ ጋር ያደረገው የኢሜይል ግንኙነት፣ የካቲት 22/2004

133 ሂዩማን ራይትስ ዎች አካባቢውን ከጎበኘ ሰው ጋር ያደረጋቸው የኢሜይል ግንኙነቶች፣ የካቲት 21/2004

134 በቪዲዮ የተሰጠ ምስክርነት ቁጥር 20፣ ሂዩማን ራይትስ ዎች ዘንድ በፋይል የሚገኝ

135 የሂዩማን ራይትስ ዎች ቃለ ምልልስ ቁጥር 9፣ ታችኛው ኦሞ፤ ግንቦት 26/ 2003

“ምናልባት ማሰብ ያለባችሁ ስለከብቶቻችሁ ነው።ከብቶቻችሁ የሚበሉት ነገር አይኖራቸውም። ሳር አይኖርም።ብዙም ሳይቆይ ስለከብቶቻችሁ ማሰብ ትጀምራላችሁ፣ከብቶቻችሁን መሸጥ ይኖርባችኋል።”[136]

የማህበረሰቦቹ አባላትም ወደሰፈራ ጣቢያዎች ከተወሰዳችሁ በኋላ መንግስት በሚያቀርብላችሁ ምግብ ብቻ ትኖራላችሁ በማለት የመንግስት ባለስልጣናት ነግረውናል በማለት በፍርሃት ተውጠዋል። የሙርሲ ብሔረሰብ ተወላጆች ለሂዩማን ራይትስ ዎች እንደገለጹት መንግስት የሚያቀርበውን የምግብ ዕርዳታ በአንድ ቦታ ሰፍረው እንዲኖሩ እንደማበረታቻ እየተጠቀመበት ነው። አንድ የሙርሲ አርብቶ አደር እንዳሉት፡

> በሚቀጥሉት ዓመታት የከፋ ረሃብ ሊከሰት ይችላል።ምን እንደሚፈጠር አናውቅም።እየተራብን ስለሆነ ካሁኑ ላሞቻችንን [እርደን] መብላት ጀምረናል።መንግስት በዚህ መንደር ማሽላ የሚሰጠው በአንድ አካባቢ ሰፍረን እንድንኖር እንደ ማበረታቻ ነው።[137]

ወደፊት ሊከሰት የሚችለውን የምግብ ዋስትና ስጋት አስመልክቶ አንድ የሙርሲ ተወላጅ ሲያጠቃልሉ፡

> ከብቶቹ በሙሉ ለመንግስት ከተሰጡ በአካባቢዎቹ ትልቅ ችግር ይፈጠራል። ድርቅ የአፍሪካን ቀንድ አካባቢ እንዲህ ክፉኛ በመታበት በአሁኑ ወቅት እነዚህ ሰዎች ምን ይበላሉ? አሁን ግድቡ ተገንብቷል፣ ወንዙ ምንም ውሃ የለውም፣መሬቱ ተወስዷል፣ከብቱ ለመንግስት ተሰጥቶ እነዚህ ምስኪን ሰዎች በችጋር ጊዜ ምን ይሆናሉ? ከብት አርቢዎችን ለማጥፋት የሚፈልጉት ሰዎች በቀን ሦስት ጊዜ የሚበሉ ናቸው። ረሃብ ቢመጣ ምን ይኮናል?[138] ብለዋል።

---

136 የሂዩማን ራይትስ ዎች ቃለ ምልልስ ቁጥር 15፣ ታችኛው ኦሞ፤ ግንቦት 25/ 2003

137 የሂዩማን ራይትስ ዎች ቃለ ምልልስ ቁጥር 4፣ ታችኛው ኦሞ፤ ግንቦት 25/ 2003

138 ሂዩማን ራይትስ ዎች ከታችኛው ኦሞ ነዋሪ ጋር ያደረገው የኢሜይል ግንኙነት፣ ነሃሴ 2003

# V. ከኢትዮጵያ መንግስት እና ከለጋሾች የተሰጡ ምላሾች

ከላይ እንደተገለጸው የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስትሩ ለቃለ መጠይቅ እንዲገኙ ለቀረበላቸው ጥያቄ ምላሽ አልሰጡም። የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ሚኒስትሩ በረከት ስምኦን ደግሞ የሂዩማን ራይትስ ዎች መርማሪ ሀገሪቱን ከለቀቀ ከአንድ ሳምንት በኋላ ለቃለ መጠይቅ መስማማታቸውን ገልጸዋል።የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ባለስልጣናት የመርማሪዎቹን ጥያቄዎች በልማት ዕቅዶቹ ላይ እና በታችኛው ኦሞ ስለሚፈጸሙ የመብቶች ጥሰቶች ምንም መረጃ ወደሌላቸው የሕዝብ ግንኙነት ሠራተኞች በማስተላለፍ ምንም አስተያየት ሳይሰጡ ቀርተዋል።

ስማቸው እንዳይገለጽ በመጠየቅ ከሂዩማን ራይትስ ዎች ጋር የተነጋገሩ አንድ የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል ባለስልጣን በታችኛው ኦሞ የሚኖሩ ተወላጅ ማህበረሰቦችን ወደሌሎች አካባቢዎች ማስፈር ያስፈለገው ለስኳር ልማቱ መሬት በማስፈለጉ ነው ብለዋል። በሰፈራው ምክንያት የሚፈጠረው መከፋት ወደ ግጭት ሊያመራ እንደሚችል ስጋት እንዳላቸው ባለስልጣኑ ጨምረው ገልጸዋል።[139]

ሂዩማን ራይትስ ዎች በዚህ ሪፖርት የተደረሰባቸውን ዋና ዋና ነጥቦች የያዘ ማጠቃለያ ለኢትዮጵያ መንግስት በህዳር ወር 2004 አቅርቦ ነበር።መንግስትም የምርመራውን ውጤቶች ሁሉ በማጣጣል "ፕሮጀክቱ የሚካሄድበት አካባቢ ሰዎች ከሚኖሩበት አካባቢ የራቀ በመሆኑ ምንም የሚያውከው የኑሮ ዘይቤ የለም።"[140] በማለት በአጽንኦት ገልጾአል።

ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪነት በተያያዘው ምላሹ የኢትዮጵያ መንግስት ለሂዩማን ራይትስ ዎች እንደገለጸው ለ2050 ቤተሰቦች 0.75 ሄክታር በመስኖ የሚለማ መሬት፣ "በተሻሻሉ የግብርና ዘዴዎች፣የቴክኖሎጂ ግብአቶች እንዲሁም በከብቶች አያያዝ ላይ (የተከለለ መሬትን ጨምሮ) ላይ ስልጠና ይሰጣል።" በተጨማሪም በስኳር ልማቱ ላይ መሬት የማከራየት እድሎች እና "የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንዲሁም የመሰረተልማት ተቋማት አቅርቦቶች"[141] እንደሚኖሩ መንግስት በምላሹ ገልጿል።

የኢትዮጵያ መንግስት ጨምሮ እንደገለጸው እነዚህ የሪፖርቱ ድምዳሜዎች "የመነጬት ወደኢትዮጵያ የመጣው የሂዩማን ራይትስ ዎች የምርመራ ቡድን የኢትዮጵያ የጸጥታ ሃይሎች ያላቸውን ዲሲፕሊን ሆን ብሎ ላለማወቅ በመምረጡ ነው።"[142] ሂዩማን ራይትስ ዎች በኢትዮጵያ የጸጥታ ሃይሎች አባላት ሬከርድ ላይ ያለው ስጋት በኦሞ ሸለቆ ባሳዩት ጸባይ ላይ ብቻ የተመሰረተ አይደለም። ሂዩማን ራይትስ ዎች በሌሎች የኢትዮጵያ አካባቢዎች እና ሶማሊያ ውስጥ ያካሄዳቸው ምርመራዎች ዓለማቀፍ የሰብአዊ መብቶችና የሰብአዊነት ሕጎችን የሚጥሱ ግልጽ ጥሰቶች መፈጸማቸውን፣ የጦር ወንጀሎች እና በሰብአዊ ፍጡር ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች የተፈጸሙባቸው ሁኔታዎችም እንዳሉ የሚያሳዩ ናቸው።[143] የተባበሩት መንግስታትን ጨምሮ ሌሎች ድርጅቶችና ተቋማትም የኢትዮጵያ ጦር ሃይል በሰላማዊ ሰዎች ላይ የሚፈጽመው መንደሮችን ማቃጠል፣ ሕገወጥ እስር፣ ማሰቃየት እና ርሸና ያሳሰባቸው መሆኑን በመግለጽ መግለጫ አውጥተዋል።[144] ኢትዮጵያ እነዚህን ስጋቶች ለመቀበል ወይም ለመመርመር ፈቃደኛ ሳትሆን ቀርታለች።[145]

ከሂዩማን ራይትስ ዎች ጋር በተደረጉ ስብሰባዎች በልማት አጋሮች ቡድን (ዳግ) ውስጥ የሚገኙ ለጋሾች በታችኛው ኦሞ ሊካሄድ ስለታቀደው ልማት ወይም በዚህ ሪፖርት ላይ ስለተገለጹት የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ያላቸው ዕውቀት አናሳ ሆኖ

---

139 ሂዩማን ራይትስ ዎች ከደቡብ ክልል ባለስልጣን ጋር ያደረገው ቃለ ምልልስ

140 የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስትር ሽፈራው ተክለማርያም ለሂዩማን ራይትስ ዎች የጻፉት ደብዳቤ፣ ታህሳስ 9,2004

141 ዝኒ ከማሁ

142 ዝኒ ከማሁ

143 የሂዩማን ራይትስ ዎችን "Collective Punishment; Shell-Shocked: Civilians Under Siege in Mogadishu, August 2007" http://www.hrw.org/reports/2007/08/12/shell-shocked እና Targeting the Anuak: Human Rights Violations and Crimes against Humanity in Ethiopia's Gambella Region, March 2005, http://www.hrw.org/reports/2005/03/23/targeting-anuak ሪፖርቶች ይመልከቱ

144 ዓለማቀፉን የጸረ ስቃይ ስምምነት አፈጻጸም የሚከታተለው የተባበሩት መንግስታት ኮሚቴ በህዳር ወር 2003 እንዳለው፡"በፖሊስ፣በወህኒ ቤቶች ሃላፊዎች፣በሌሎች የጸጥታ ሃይሎች አባላት እና በመከላከያ ሰራዊቱ የተቃውሞ ሃሳባቸውን የሚሰነዝሩና ተቃዋሚ ፓርቲዎች አባላት የሆኑ ሰዎችን፣ታመሪዎችን፣የሽብር ወንጀል ተጠርጣሪዎችን እና ሽምቅ ተዋጊዎችን ይደግፋሉ የሚባሉ ሰዎችን ኢላማ ያደረገ የማሰቃየት ድርጊት በስፋት የሚፈጸም መሆኑን የሚገልጹ በርካታ፣በየጊዜው የሚወጡና ተደጋጋፊነት ያላቸው ክሶች መኖር ኮሚቴውን በእጅጉ ያሳስቡታል...." UN Committee Against Torture (CAT), List of issues prepared prior to the submission of Ethiopia's periodic report (CAT/C/TCD/2): Committee Against Torture, 45th Session 1-19 November 2010, 15 February 2011, CAT/C/TCD/Q/2, http://unhcr.org/refworld/docid/4f2133312.html

145 የሂዩማን ራይትስ ዎችን Collective Punishment,Shell-Shocked; Targeting the Anuak ሪፖርቶች ይመልከቱ

ታይቷል።[146]በደቡብ ኦሞ ዞን በቀጥታ የለጋሾች ድጋፍ የሚካሄዱ ፕሮግራሞች በጣም ጥቂት ናቸው፤ እናም ስለሚፈጸሙት ጥሰቶች መረጃ የሚያገኙበት መንገድ የለም። በጥር ወር 2004 በዩናይትድ ስቴትስ ዓለማቀፍ የልማት ድርጅት (ዩኤስኤይድ) እና በእንግሊዝ ዓለማቀፍ የልማት ድርጅት (ዲኤፍአይዲ) የተመራ የለጋሾች ቡድን በታችኛው ኦሞ ግምገማ ማድረጉ አበረታች ቢሆንም፣ የዚህ ግምገማ ውጤት ግን እስካሁን ይፋ አልሆነም።[147]

በዓለም ባንክ፣በአውሮፓ ህብረት፣በብሪታንያ እና በሌሎች ለጋሾች ከሚደገፈው እና የመሠረታዊ አገልግሎቶች ጥበቃ (ፒቢኤስ) በመባል ከሚታወቀው በኢትዮጵያ ትልቁ የለጋሾች የእርዳታ ፕሮግራም የሚገኝ ገንዘብ በተዘዋዋሪ በታችኛው ኦሞ በመካሄድ ላይ ያለውን የሰፈራ እና የልማት እንቅስቃሴዎች ሊደግፍ የሚችልበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል። ይህም ሊሆን የሚችለው ፒቢኤስ እና ተከታዩ ፒቢኤስ ሁለት በኢትዮጵያ ሁሉም ወረዳዎች ለሚቀርቡ መሠረታዊ አግልግሎቶች የገንዘብ ድጋፍ ስለሚያደርጉ ነው።[148] ስለሆነም ሰላማጎ ወረዳን ጨምሮ በታችኛው ኦሞ በሚገኙ ወረዳዎች የፒቢኤስ ፕሮግራም ቁልፍ ዘርፎች በሆኑት በጤና፣ትምህርት፣ውሃ፣ መንገዶች እና የግብርና ልማት በወረዳ ደረጃ ለሚከናወኑ ትግበራዎች የሆነ ድጋፍ እንደሚያደርግ ርግጠኛ ሆኖ መናገር ይቻላል።[149] በመስከረም ወር 2005 ፒቢኤስ ሦስት የዓለም ባንክ ቦርድ እንዲወያይበት እንደሚቀርብ ይጠበቃል።ሂዩማን ራይትስ ዎች በፒቢኤስ የሚደገፉት ፕሮግራሞች ግልጽነት እና ተጠያቂነት የጎደላቸው መሆኑን በመግለጽ በተደጋጋሚ ጊዜ ስጋቱን ለለጋሾች አሳውቆአል፤ነገር ግን ከእነዚህ ስጋቶች ውስጥ አንዱም እንኳ ለፒቢኤስ ሦስት በተዘጋጀው የፕሮጀክት መረጃ ሰነድ ውስጥ ምላሽ አላገኘም።[150]

ከፒቢኤስ የሚገኘው ገንዘብ ለወረዳዎች የሚደርሰው በፌደራል ገንዘብ ሚኒስቴር እና በክልል መንግስታት በኩል በጥቅል እርዳታ መልክ ነው።[151] የኢትዮጵያ መንግስት ለሂዩማን ራይትስ ዎች በጻፈው ደብዳቤ እና በተደጋጋሚ በይፋ በወጡ መግለጫዎቹ እንደሚገልጸው በዚህ ዘርፍ መሠረታዊ አግልገሎቶችን ማቅረብ ግድቡ እና ተያይዘው የሚካሄዱት የግብርና ልማቶች ዋነኛ አካል ነው፤እንዲያውም የፕሮጀክቱን መካሄድ በመደገፍ ከሚቀርቡት ቁልፍ መከራከሪያዎች አንደኛው ነው።[152] የአካባቢው እማኞች ለሂዩማን ራይትስ ዎች እንደገለጹት የስኳር ልማቱን እና የሰፈራ ፕሮግራሙን አስመልክቶ በሚደረጉት ሁሉም ስብሰባዎችና ምክክሮች ላይ የወረዳ ባለስልጣናት ይገኛሉ።[153] የፒቢኤስ ፕሮጀክት ሰነዶች እንደሚያሳዩት መንግስት በወረዳዎች ለሚያቀርባቸው መሰረታዊ አገልግሎቶች ከሚያስፈልገው ገንዘብ ውስጥ አንድ ሦስተኛው ከፒቢኤስ

---

146 ዳግ በኢትየጵያ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ 26 ለጋሽ ድርጅቶች ስብስብ ነው። www.dagethiopia.org ሂዩማን ራይትስ ዎች በመስከረም ወር 2004 ከእነዚህ ለጋሽ ድርጅቶች ውስጥ የአስሩን ሃላፊዎች አግኝቶ አነጋግሯል።

147 አንድ የዐይን እማኝ እንደተናገሩት ገምጋሚ ቡድኑ በሙርሲ እና ቦዲ አካባቢዎች የቆየው ለአንድ ቀን ብቻ ነው።

148 ፒቢኤስ በብዙ ለጋሾች ከሚደገፉ የዓለማችን ትልልቅ የእርዳታ ፕሮግራሞች አንዱ ሲሆን ለኢትዮጵያ ሁሉም ወረዳዎች በጤና፣በትምህርት፣በመንገዶች፣በግብርና እና በውሃ ዘርፎች የበጀት ድጋፍ ያደርጋል። የዓለም ባንክን "Protection of Basic Srvices, Project Information Document, February 17, 2006, http://www.dagethiopia.org/index.php?option=com_content&view=section&layout=blog&id=14&itemid=16 (ኤፕሪል 4/2012 የታየ) እና Protection of Basic Services 11, Project Information Document, March 8, 2009, http://www.google.ca/url?sa=t&rct=j&q=%22pbs%20ii%22%20project%20information%20document&source=web&cd=1&ved=0CE8QFjAA&url=http%3A%2F%2Fwww-wds.worldbank.org%2Fexternal%2Fdefault%2FWDSContentServer%2FWDSP%2FIB%2F2009%2F03%2F11%2F000104615_20090312140745%2FOriginal%2FPIDoAppraisaloStage1Macho802009.doc&ei=JM_MT-mmKOTi2AWq_tCoCw&usg=AFQjCNF7ejt3RdwcsCCYCt2ZRh7zPVu_ow&cad=rja (ጁን 4/2012 የታየ)

149 የፒቢኤስ ፕሮጀክት ሰነዱ እንደሚለው "ለፒቢኤስ ዓላማ መሰረታዊ አገልግሎቶች የሚባሉት ከብሔራዊ ደረጃ ዝቅ ብሎ የሚሰጡ አገልግሎቶች ሆነው ለድህነት ቅነሳ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ወይም በጎ ማህበራዊ ተጽዕኖ ያላቸውን እንደ የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት፣ጤና፣የውሃ አቅርቦት እና የጤና አጠባበቅ፣የገጠር መንገዶች፣ የግብርና ኤክስቴንሽን፣ የሥራ እና የማህበራዊ ዋስትና ያሉትን እንዲያካትት ተደርጎ ሰፊ ትርጓሜ ተሰጥቷቸዋል።" የዓለም ባንክ፣ Protection of Basic Srvices, Project Information Document, February 17, 2006, ገጽ 3

150 ፒቢኤስ ላይ የሚነሱ ትችቶችን ለማየት ሂዩማን ራይትስ ዎች Development Without Freedom: How Aid Underwrites Repression in Ethiopia, October 2010, http://www.hrw.org/reports/2010/10/19/development-without-freedom-0 ይመልከቱ። PBS 111 Project Information Document, http://www.google.ca/url?sa=t&rct=j&q=%22pbs%20iii%22%20project%20information%20document&source=web&cd=1&ved=0CE8QFjAA&url=http%3A%2F%2Fwww-wds.worldbank.org%2Fexternal%2Fdefault%2FWDSContentServer%2FWDSP%2FAFR%2F2012%2F04%2F03%2F6ED2AA6FD2B4EC38852579D5001CD070%2F1_0%2FRendered%2FPDF%2FPIDoPrintoP12889100403201201333430083402.pdf&ei=s9PMT-fAG8W42wWHh6ieCw&usg=AFQjCNEDHVPCGVwFzatHK6yplUR7Ck7XEg&cad=rja.

151 የዓለም ባንክ፣ Protection of Basic Sevices, Project Information Document, ገጽ 5

152 የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስትር ሽፈራው ተክለማርያም ለሂዩማን ራይትስ ዎች የጻፉት ደብዳቤ፣ ታህሳስ 9,2004። የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርም ለአካባቢው ይገኛል ተብሎ የሚጠበቀውን የክሊኒኮች፣ የትምህርት ቤቶች፣የመሠረተ ልማት አውታሮች እንዲሁም የወንዙን ፍሰት መቆጣጠር፣ አውዳሚ ጎርፍንና በ1970ዎቹ አጋማሽ ላይ ተከስቶ የነበረውን ዓይነት ችጋር ማስቀረት፣የኢኮ ቱሪዝም ልማት፣የአካባቢ ጥበቃ ትምህርት፣የስራ እድሎች እና ዋስትና ያለው በተመጠነ ጎርፍ የሚሰራ ግብርና የመሳሰሉትን ይጠቅሳል። "UNESCO's World Heritage Committee and Gilgel Gibe 111", A Week in the Horn, የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ሴፕቴምበር 2/2011

153 የሂዩማን ራይትስ ዎች የኢሜይል ግንኙነቶች፣ህዳር 8/2004

የሚገኝ ነው።[154] በልማቱ ስራ የሚነኩት በደቡብ ኦሞ ዞን የሚገኙት ወረዳዎች ከፒቢኤስ የሚገኘውን ገንዘብ የማይቀበሉ ካልሆነ በስተቀር የለጋሾቹ ገንዘብ ከስኳር ልማቱ ጋር ተያይዞ የሚካሄደውን የሰፈራ ፕሮግራም እየደገፈ አይደለም ለማለት አስቸጋሪ ነው።

ዳግ እና ለፒቢኤስ ድጋፍ የሚያደርጉ ሁሉም ለጋሾች በታችኛው ኦሞ በግዴታ ሊካሄድ የሚችለው የሰፈራ እንቅስቃሴ ሊያሳስባቸው ይገባል። የዓለም ባንክ የባንኩን ገንዘብ ሰፈራን ለሚያካትቱ ፕሮጀክቶች የሚጠቀሙ የልማት አጋሮቹ (እዚህ ላይ ኢትዮጵያ) የግድ ሊከተሏቸው የሚገባ መስፈርቶችን የሚዘረዝር አስገድዶ ማስፈርን የሚመለከት መመሪያ አለው።[155] ኢትዮጵያ ውስጥ ሰፈራው መቀጠሉን፣ ማስተባበሩም በወረዳ ደረጃ የሚካሄድ መሆኑንና ቢያንስ በይፋ ባንኩ ድጋፍ የሚያደርግላቸውን የአምስቱን መሠረታዊ አገልግሎቶች አቅርቦት የሚያካትት መሆኑን በመመልከት ባንኩ እና ሌሎች የፒቢኤስ ለጋሾች የሚሰጡት ገንዘብ የተወላጅ ሕዝቦችን መሬት ከሕግ ውጭ ለመውረስ እና አስገድዶ ለማስፈር አለመዋሉን ለማረጋገጥ ሚና መጫወት ያለባቸው መሆኑ ግልጽ ነው።

ለጋሾች በግዳጅ የማፈናቀሉን ድርጊት በጥልቀት መመርመር፣ የኢትዮጵያ መንግስት ለዓለማቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሕጎች ተገዢ እንዲሆንና የሰፈራ ፕሮግራም በሚያካሂድበት ጊዜ ዓለማቀፋዊ በጎ ተሞክሮዎችን እንዲተገብር ግፊት ማድረግ እንዲሁም በታችኛው ኦሞ አስገድዶ ከማፈናቀል ጋር ለተያያዙ ማናቸውም እንቅስቃሴዎች ምንም ድጋፍ አለመስጠቱን ማረጋገጥ አለባቸው። በታችኛው ኦሞ ለሚካሄድ ማናቸውም ፕሮግራም ድጋፍ ከማድረግ በፊት ለጋሾች ትርጉም ያለው ምክክር መደረጉን፣ተገቢው የአካባቢና የማህበራዊ ተጽዕኖ ግምገማ መደረጉንና ለሕዝብ ውይይት በይፋ መቅረቡን እንዲሁም ከታችኛው ኦሞ ተወላጅ ሕዝቦች ጋር አማራጭ የኑሮ መሠረቶችን አስመልክቶ ውይይት መደረጉን ማረጋገጥ አለባቸው። በተገቢና ግልጽነት ባለው መንገድ እንዲሁም ከኢትዮጵያ ሕጎችና ሀገሪቱ በዓለማቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሕጎች መሠረት ካሉባት ግዴታዎች ጋር በተጣጣመ መልኩ መካሄድ እስኪችሉ ድረስ የሰፈራ ፕሮግራሞቹን እንዲያቆም ለጋሾች ለኢትየጵያ መንግስት ጥሪ ማቅረብ አለባቸው።

---

154 የዓለም ባንክ፣ "Additional Financing for the Second Phase of the Protection of Basic Services Project," Project Information Document, October 6/2010, http://www-wds.worldbank.org/external/default/WDSContentServer/WDSP/IB/2010/12/16/000020953_20101216105936/Rendered/PDF/585030PID0ETH0protection0of0basicorev.pdf

155 የዓለም ባንክ፣ "OP 4.12 – Operational Policy on Involuntary Resettlement," December 2001 (revised February 2011), http://web.worldbank.org/WBSITE/EXTERNAL/PROJECTS/EXTPOLICIES/EXTOPMANUAL/0,,contentMDK:20064610~menuPK:64701637~pagePK:64709096~piPK:64709108~theSitePK:502184,00.html (ፌብሯሪ 28/2012 የታየ)

# VI. አርብቶ አደርነት፣የመሬት ይዞታ እና የታችኛው ኦሞ ተወላጅ ሕዝቦች መብቶች

በኦሞ ሸለቆ የሚካሄደው የልማት እንቅስቃሴ ተጠናክሮ እየቀጠለ በመሆኑ የኢትዮጵያ መንግስት በሸለቆው የሚኖሩ ተወላጅ ነዋሪዎች መብቶች መከበራቸውን እና ነዋሪዎችን ከመኖሪያቸው የማፈናቀል ስራ መሰራት ያለበት ከዓለማቀፍና ከኢትዮጵያ ሕጎች ጋር በተጣጣመ መልኩ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።

የኢትየጵያ ሕገ መንግስት፣ዓለማቀፍ ስምምነቶች እንዲሁም በየጊዜው እየጨመሩ የመጡት በፍርድ ቤቶችና በልዩ ልዩ ተቋማት የሚሰጡ ውሳኔዎች ተወላጅ ማህበረሰቦች ለዘመናት ከኖሩባቸው መሬቶች ተገደው እንዳይፈናቀሉ የሚያስችሏቸውን መብቶች መጠበቅ አስፈላጊ መሆኑን የሚያረጋግጡ ናቸው። በእነዚህ መርሆች መሰረት ተወላጅ የመሬት ባለይዞታዎች በመሬታቸው ላይ የባለቤትነት መብት ያላቸው ሲሆን ከመሬታቸው ሊነሱ የሚችሉትም ጉዳዩን በተገቢው ሁኔታ ተረድተው ስምምነታቸውን ተጠይቀው ሲስማሙ ብቻ ነው። ለሚያጡት መሬትም ተመጣጣኝ የካሳ ክፍያ ሊከፈላቸው ይገባል። መሬትን መውረስ (የካሳ ክፍያ ፈጽሞም ቢሆን) የመጨረሻ አማራጭ መሆን ያለበት ሲሆን መፈጸም ያለበትም ሕጉን ተከትሎ ብቻ መሆን ይኖርበታል።

## የመሬት እና ንብረት የመያዝ መብት

በታችኛው ኦሞ የሚኖሩት ተወላጅ ሕዝቦች የየራሳቸው ቋንቋ፣ማንነት እና ድንበሮች ያሏቸው ሕዝቦች ናቸው።ከላይ በካርታ 2 እንደተመለከተው ነዋሪዎቹ እነዚህን አካባቢዎች ይዘው ሲጠቀሙባቸው የነበሩ መሆኑ በሥነ ሰብዕ አጥኚዎች ተረጋግጧል።[156]

የኢትዮጵያ ሕገ መንግሰት ሁሉም መሬት የመንግስት መሆኑን ይገልጻል።[157] ይሁንና መሬቱ ከጥንት ጊዜ ጀምሮ የተያዘ በመሆኑ በዓለማቀፍ ሕግ መሠረት ባለይዞታዎቹ መሬቱን በንብረትነት የመያዝ መብት አላቸው። ምንም ዓይነት ልማትና የማፈናቀል ተግባር ከመፈጸሙ በፊት የመሬቱን ነባር ባለቤቶች ሳያማክሩ እና ባለቤቶቹም በበቂ መረጃ ላይ የተመሰረተ ነጻ ስምምነታቸውን ሳይሰጡ እንዲሁም የካሳ ክፍያ ሳይፈጸም የመሬቱን አጠቃቀም መቀየር ወይም መሬቱን መውሰድ ሕገወጥ ድርጊት ነው።ተለዋጭ መሬት እና የኑሮ መሠረቶችን አስመልክቶም ግልጽ ምርጫዎች ሊቀርቡላቸው ይገባል።

በዓለማቀፍ ደረጃ በተወላጅ መብቶች ሕዝቦች ላይ የተሰጡ የተቋማት እና የፍርድ ቤቶች ውሳኔዎች ለተወላጅ ሕዝቦች መብቶች እና የኑሮ መሠረቶች የሚደረገው ጥበቃ እንዲሰፋና እንዲጠናከር አድርገዋል። ለምሳሌ ያህል የበይነ አሜሪካ የሰብአዊ መብቶች ፍርድ ቤት እና የአፍሪካ የሰብአዊና የሕዝቦች መብቶች ኮሚሽን ተወላጅ ሕዝቦች በመሬቶቻቸው ላይ ያላቸው ነባር ይዞታ በመሬቱ ላይ የባለቤትነት መብት እንዳላቸው ተደርገው እንዲቆጠሩ ያደርጋቸዋል ብለው ያምናሉ። እ.ኤ.አ በየካቲት ወር 2010 የአፍሪካ የሰብአዊና የሕዝቦች መብቶች ኮሚሽን የኬንያን ኢንዶሮይ ሕዝቦች በሚመለከት የሰጠው ውሳኔ በአፍሪካ የሚገኙ ተወላጅ ሕዝቦች በነባር መሬቶቻቸው ላይ የሚኖራቸውን መብቶች ለማጠናከር የተወሰደ ወሳኝ ርምጃ ነው።[158]

የኢንዶሮዮች ጉዳይ በኬንያ የሚገኙ አርብቶ አደር ተወላጅ ሕዝቦች ለብሔራዊ ፓርክ ተብሎ ከመሬታቸው እንዲፈናቀሉ የተደረገበትን ሁኔታ የሚመለከት ነው። ይህ ጉዳይ አፍሪካ ውስጥ ተወላጅ ማህበረሰብ የሚባሉት የትኞቹ እንደሆኑ ለመወሰን

---

156 “ተወላጅ ሕዝቦች” የትኞቹ እንደሆኑ የተደረሰበት ሕጋዊ ትርጓሜ የለም።ይሁንና የተባበሩት መንግስታት የተወላጅ ጉዳዮች ቋሚ መድረክ የሚከተለውን ማብራሪያ አውጥቷል፡በግለሰብ ደረጃ ራስን እንደ ተወላጅ መቁጠር እና በማህበረሰቡም እንደአባል ተቀባይነት ማግኘት፣ከቅድመ ቅኝ ግዛትና ከቅድመ ሰፋሪ ማህበረሰቦች ጋር ቀጣይ የሆነ ግንኙነት፣ከግዛትና በአካባቢው ካለ የተፈጥሮ ሃብት ጋር ጠንካራ ቁርኝት፣ መለያ የሆነ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ወይም ፖለቲካዊ ስርዓት፤የራስ የሆነ ቋንቋ፣ባህልና እምነት፣ የበላይ ያልሆነ ማህበረሰብ መፍጠር፣ የአያት ቅድመ አያት ተደርገው የሚወሰዱ አካባቢዎችንና ስርዓቶችን በቁርጠኝነት መጠበቅ መለያ ባሕሪያት ናቸው።የተባበሩት መንግስታት ድርጅት እንደሚለው የበለጠ ውጤታማው ዘዴ ተወላጅ ሕዝቦችን ትርጉም ለመስጠት መሞከር ሳይሆን መለያ ባሕሪያቱን መዘርዘር ነው።ይህም ራስን በተወሰነ መልክ ማየት የሚለውን መሠረታዊ መስፈርት መሰረት ያደረገ ነው። UN Permanent Forum on Indigenous Issues, Factsheet: Who are Indigenous Peoples," http://www.un.org/esa/socdev/unpfii/documents/5session_factsheet1.pdf (ማርች 25/2012 የታየ)

157 የኢፌዲሪ ሕገ መንግስት፣ አዋጅ ቁጥር 1/1987፣ አንቀጽ 40(3)

158 የበይነ አሜሪካ የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን፣ “Indigenous and Tribal Peoples' Rights over their Ancestral Lands and Natural Resources," 2009, http://www.cidh.org/countryrep/Indigenous-Lands09/Chap.VI.htm (ኦገስት 30/2011 የታየ)፣ እና “Kenya: Landmark Ruling on Indigenous Land Rights," Human Rights Watch news release, February 4, 2010, http://www.hrw.org/en/news/2010/02/04/kenya-landmark-ruling-indigenous-land-rights

ከመርዳቱም በላይ ለልማዳዊ የመሬት ይዞታ እውቅና ሰጥቷል፤ከዚህም በላይ የልማት ስራዎች በተለይም ብሔራዊ ፓርኮችን የማስፋፋት ስራ ተወላጅ ሕዝቦችን በጅምላ ለማፈናቀል በቂ ምክንያት ሊሆን እንደማይችል አረጋግጦአል።[159]

ኮሚሽኑ በውሳኔው እንደገለጸው አንድን አርብቶ አደር ተወላጅ ማህበረሰብ ከአያት ቅድመ አያቶቹ መኖሪያ እና የመቃብር ቦታ ማፈናቀል እና ይህም በአርብቶአደርነት የሕይወት ዘይቤ ላይ የሚያስከትለው ተጽዕኖ የባሕል እና የሃይማኖት መብቶችን መጣስ ነው። በተጨማሪም ማፈናቀሉ ለራሳቸው እና ለከብቶቻቸው በመድሃኒትነት የሚጠቀሙባቸውን ተክሎች እንዲያጡ ስለሚያደርጋቸው የጤና መብታቸውን የሚጥስ ሲሆን በአፍሪካ የሰብአዊና የሕዝቦች መብቶች ቻርተር የተረጋገጠውን በተፈጥሮ ሃብቶች [የመጠቀም] መብታቸውንም የሚጥስ ነው።

ውሳኔው የልማት መብት ላይ የተሰጠ የመጀመሪያው ዓለማቀፍ ሕጋዊ ውሳኔ ነው።ኬንያ የማህበረሰቡን መብቶች ጥሳለች ሲል የወሰነው ኮሚሽኑ መብት ሁለት ክፍሎች እንዳሉት ገልጾ እነሱም የመልማት እና የኑሮ ሁኔታን የማሻሻል ናቸው ብሏል። ማፈናቀሉ በኢንዶሮዮቹ ላይ ባስከተለው አሉታዊ ተጽዕኖ፣ለልማት ተብሎ ከተወሰደው መሬታቸው ላይ ምንም ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ሳይሰጣቸው በመቅረቱ እንዲሁም መሬታቸውን እና መፈናቀላቸውን አስመልክቶ በተሰጠው ውሳኔ ላይ እነሱን ያሳተፈ በቂ ምክክር ባለመደረጉ ሳቢያ እነዚህ መብቶች ተጥሰዋል።

የኢትዮጵያ ሕገ መንግስትም ለአርብቶ አደር ሕዝቦች እውቅና የሚሰጥ ጠንካራ መሠረት ያለው ሲሆን ይህም ለኦሞ ሸለቆ ሕዝቦች ተፈጻሚ ሊሆን ይችላል። የሕገ መንግስቱ አንቀጽ 40(5) "የኢትዮጵያ አርብቶ አደሮች ለግጦሽም ሆነ ለእርሻ የሚጠቀሙበት መሬት በነፃ የማግኘት፣ የመጠቀም እና ከመሬታቸው ያለመፈናቀል መብት አላቸው። ዝርዝር አፈጻጸሙ በሕግ ይወሰናል።"[160] በማለት ይገልጻል።መንግስት ለልማት ግቦቹ በሚስማማ መልክ ሕገ መንግስቱን አላሻሻለም።እስካሁንም የአርብቶ አደር ሕዝቦቹን መብቶች አላከበረም።

በአብዛኛው የሃገሪቱ ክፍል የሚታየው የመሬት ይዞታ ስርዓት እጅግ አናሳ ነው። ከዘጠኙ ክልሎች የሚታወቅ የመሬት ይዞታ ስርዓት ያላቸው አራቱ (አማራ፣ትግራይ፣ኦሮሚያ እና ደቡብ ሕዝቦች) ብቻ ናቸው።[161] እንደሌሎች ክልሎች ሁሉ በደቡብ ክልልም ያለው የመሬት ይዞታ ስርዓት በአንድ ቦታ ሰፍሮ በሚሰራ ግብርና ላይ ያተኮረ ነው።የታችኛው ኦሞ ተወላጅ ማህበረሰቦችን የመሬት ይዞታ ዋስትና የሚያጠናክር የመሬት ምዝገባ ሂደት በታችኛው ኦሞ ተካሂዶ አያውቅም።

